# የቤተ ክርስቲያን አባላት መመሪያ

የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን የአባላት መመሪያ

**የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን አባላት መመሪያ**

**የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን 2009-2013 መመሪያ ቀለል ባለ እና አጭር ሆኖ የቀረበ። በኔቪሌ ባርትሌ**

© ግሎባል ፐብኬሽን ኦፍ ዚይ ቸርርች ኦፍ ዚይ ናዛሪን

አሳታሚ
የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን
P.O. Box 16973
Suva, Fiji

Printed and updated with permission by
Africa Nazarene Publications
P.O. Box 1288
Florida
1710
Republic of South Africa

ISBN -978-0-7977-1131-0
,-,

**ማውጫ**

**ማዕከላዊ ዕሴቶች** ............................................................................

**መግቢያ** ..........................................................................

**የእምነት አንቀጾች** .........................................................................

**የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን አባላት መምሪያ/ደንብ** .............................

**የክርስቲያናዊ ባሕርይ ቃል ኪዳን** ...................................................

**የቤተ ክርስቲያን አደረጃጀት** ..................................................

**አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት**...........................................................

**የቀጠና ጉባኤ** ........................................................................

**አጠቃላይ ጉባኤ** .......................................................................

**አገልጋይ** ..........................................................................

**የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ማዕከላዊ እሴቶች**

ማዕከላዊ እሴቶች የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ዋና ዋና የሚባሉ እምነቶች እጣሬ ነው፡፡

**እኛ ክርስቲያኖች ነን፡፡** የኢየሱስን ጌትነት ከሚመሰክሩ እውነተኛ አማኞች ጋር አንድ ነው፡፡ እግዚአብሔር እኛን በጣም ከመውደዱ የተነሳ አንድያ ልጁን፣ ኢየሱስ አዳኛችን እንዲሆን እንደሰጠን እናምናለን፡፡ በኢየሱስም የመስዋዕትነት ሞት የተነሳ ሁሉም ሰው የኃጢአት ይቅርታን ማግኛ እንዳገኘና ከእግዚብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት መመሥረት እንደሚችል እናምናለን፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ከተታረቅን በኋላ በመካከላችንም እርቅ እንደሆነ እናምናለን፡፡ እግዚአብሔር እኛ በወደደን መጠን እርሱ በእርሳችን ልንዋደድ ይገባል፡፡ እንዲሁም እግዚአብሔር እኛን ይቀር ባለው ልክ እኛም ሰዎችን ይቅር ልንል ይገባል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የእውነት ሁሉ ምንጭ እንደሆነ እናምናለን፡፡ በዌዝልያን የቅድስና ተውፊት ውስጥ የምንገኝ ሲሆን የክርስቲና እምነት ታሪካዊ የእምነት መግለጫዎችን እንቀበላለን፡፡

እኛ የቅድስና ሕዝቦች ነን፡፡ እግዚአብሔርን ለማመልክ እና እግዚብሔርን በሙሉ ልባችን፣ ነፍሳችን፣ አእምሮአችን እና ኃይላችን ለመውደድ እንዲሁም ባለንጀራችንን እንደራሳችን ለመውደድ በመጸሐፍ ቅዱስ እና በእርሱ ጸጋ የተጠራን ሰዎች ነን፡፡ በምንሰጠው ከእመነት የሆነ ምለሻ የተነሳ መንፈስ ቅዱስ ቀን በቀን የፍቅር እና መንፈሳዊ ባሕርይ ያለን፣ ሥነ ምግባራዊ የሆንን እና ግብረገባዊ ንጽህናችን የጠበቅን፣ ርኅሩሆች እና ፍትህን የምንሻ ዓይነት ሰው እንዲንሆን ይለውጠናል፡፡ በውስጣችን የእግዚብሔር መልክ የሚያድሰው እና በውስጣችን የክርስቶስን ባሕርይ የሚፈጥረው መንፈስ ቅዱስን ነው፡፡ በአማኞች ውስጥ የሚታየው ቅድስና በግልጽ ክርስቶስን መመስለን ነው፡፡

**እኛ ተልዕኮ ያለን ሕዝቦች ነን፣ ተልዕኮአችንም ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድ ክርስቶስን የሚመስሉ ደቀ መዛሙርትን ማፍራት ነው፡፡** ተልዕኮአችን የሚቸምረወረ ለአምልኮ በአንድ ላይ ስንሰባሰብ እና ወደ ዓለም ሁሉ ስንሄድ ነው፡፡

ተልዕኮአችን አዳደስ አማኞችን ወደ ህብረታችን መቀበልና አዳዲስ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን መጀመር ነው፡፡

ተልዕኮአችን የእግዚአብሔር ፍቅር ጌታን ለማያውቁ ሰዎች ማካፈል እና ለድሆች የእርሱን ርኅራሄ ማሳየት እና ለተጎዱ ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር በማድግ የእግዚአብሔርን ርኅራሄ ማሳየት ነው፡፡ ሰዎችን ወደ ጌታ ለማምጣ፣ ፍላጎታችን ለማሟሟላት እንዲሁም የጌታን ስም የሚጠሩ ሰዎችን ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማካተት የተሰጠን ነን፡፡

እግዚብሔር እንድንሰራው የሰጠንን ተልዕኮ መወጣት እንድንችል መሪዎችን ለማፍራት ለማሰልጠንና ለማስተማር የተሰጠንን ነን፡፡

**የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን የአባላት መመሪያ**

***መግቢያ***

ይህ ትንሽ ነጽሐፍ የተዘጋጀው የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን አባላት የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሥራዋን እንደሚታከናውን በቂ መረጃ ለመስጠት ነው። ኦፌሴላዊው የቤተ ክርስቲያኗ መመሪያ የቤተ ክርስቲያን መመሪያ ተብሎ የሚታወቀው ነው። የቤተ ክርስቲያን መመሪያው በጣም ሕጋዊ ሥርዓቶች የበዙበትን እና በጥም ጥልቅ የሆነ ነው። ብዙ ሰዎች፣ በተለይምየእንግልዘኛ ቋንቋ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ሰዎች በመመሪያው ውስጥ ያሉት ቃላት በጣም አስቸጋር እንደሆነ ይናገራሉ። ይህች ትንሽ መጽሐፍ ግን ቀላል እንግልዘኛን በመጠቀም ከአጥያ ቤተ ክርስቲያናትና ከቀጠናዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ነገሮች በአንድት አጣምራ ይዛለች። በቅንፍ ውስጥ ያለው ቁጥር የሚያመለክተው በቤተ ክርስቲያኗ መመሪያ (2009-2011) የሚገኝት ክፍል ነው። ስለዚህም ሰዎአ እስፈላጊ ሆኖ ካገኙት ከመምሪያው ጋር ማነጻጸር ይችላሉ።

**ተልዕኮአችን**

የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ተግባር ክርስቶስ በሚሰጠው የልብ መንፃትና የኃጢአት ይቅርታ አማካኝነት የሚፈጸመውን የእግዚአብሔርን የሚለውጥ ጸጋ ለሰዎች ሁሉ ማሳወቅ ነው። ቀዳማዊ ተልዕኮአችን ሰዎችን ‹‹ደቀ መዛሙርት ማድረግ››፣ አማኞችና በህብረትና በአባልነት (ማህበረ ምእመንነት) ማደራጀትና የእምነት ምላሽ የሚሰጡትን ሁሉ ለአገልግሎት ማስታጠቅ (ማስተማር) ነው። ‹‹የእምነት ማህበረሰብ›› ዋንኛ ዓላማ በመጨረሻው ቀን ሰዎችን ሁሉ በክርስቶስ ፍጹም አድርጎ ማቅረብ ነው።

ደህንነት፣ ፍጹም ማድረግ፣ ማስተማርና መላክ የሚካሄደው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። የክርስቶስ አካል የሆነችው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የእምነት የተልዕኮ መገልጫ ነች። እነዚህ አብያተክርስቲናት በአስተዳደራዊ አሠራር ቀጠናዎችና ክልሎች ተደርገው ይዋቀራሉ።

የእምነት አንቀጾች[1]

I. አሀዱ-ሥሉስ አምላክ[2]

1. ለዘላለም ህልው ሆኖ በሚኖር፣ መጨረሻ በሌለውና ሉኣላዊ ፈጣሪና የዓለማት ገዥ በሆነው፤ እርሱ ብቻ ገዥ፣ [ፈጣሪና አስተዳዳሪ]፣ በማንነቱ፣ በባሕርያቱና በዓላማው ቅዱስ፤ ቅዱስ ፍቅር እና ብርሃን የሆነ አምላክ በመሠረታዊ ማንነቱ አሀዱ-ሥሉስ የሆነ፣ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እንደተገለጠ እናምናለን።

---

[1] የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻዎቹ የእምነት አንቀጹ ደጋፊዎች ሲሆኑ፣ እንዲሁም በ1976 የጠቅላላ ጉባኤ ውሳነተ መሠረት በዚህ ስፍራ እንዲገቡ ተደርገዋል። ነገር ግን የመተዳደሪያ ደንቡ አካላት ተደርገው ሊወሰዱ አይገባም።

[2]

(ዘፍ 1፤ ዘለዋ 19፡2፤ ዘዳ 6፡4-5፤ ኢሳ 5፡16፤ 6፡1-6፤ 40፡18-31፤ ማቴ 3፡16-17፤ 28፡19-20፤ ዮሐ 14፡6-27፤ 1ቆሮ 8፡6፤ 2ቆሮ 13፡14፤ ገላ 4፡4-6፤ ኤፌ 2፡13-18፤ 1ዮሐ 1፡5፣ 4፡8)

II. ኢየሱስ ክርስቶስ

2. የአሀዱ - ሥሉስ ሁለተኛ አካል የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘላለም ከአብ ጋር እንደነበር፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝተነት ትስብእት እንደሆነና ከደንግል ማሪያም እንደተወለደ፣ ከዚህም የተነሣ ክርስቶስ የፍጹም መለኮትና የፍጹም ትስብእ ውሁድ፣ እውነተኛ አምላክና እውነተኛ ሰው፣ አምላክ-ሰው እንደሆነ እናምናለን፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአታችን እንደሞተ፣ በእውነት ከሞት ተነሥቶ ሥጋው ዳግም እንደለበሰ፣ በሁለንተናው የፍጹም ሰውን ባህርይ እንደያዘ፣ ወደ ሰማይ እንዳረገና በዚያም እንደሚማልድልን እናምናለን፡፡

(ማቴ 1፡20-25፣ 16፡15-16፤ ሉቃ 1፡26-35፤ ዮሐ 1፡1-18፤ ሐዋ 2፡22-36፤ ሮሜ 8፡3፣ 32-34፤ ገላ 4፡4-5፤ ፊል 2፡5-11፤ ቆላ 1፡12-22፤ 1ጢሞ 6፡14-16፤ ዕብ 1፡1-5፣ 7፡22-28፤ 9፡24-28፤ 1ዮሐ 1፡1-3፤ 4፡2-4፣ 15)

III.መንፈስ ቅዱስ

3. የአሃዱ-ሥሉስ ሦስተኛ አካል የሆነው መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜም እንደሚኖርና በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንና ውስጥ በትጋት እንደሚሠራ፣ ዓለምን ስለ ኃጢአት እንደሚወቅስ፣ ንሰሐ ገብተው ለሚያምኑት አዲስ ልደትን እንደሚሰጣቸው፣ አማኞችን እንደሞቀድስና በክርስቶስ ወዳለው እውነት ሁሉ እንደሚመራቸው እናምናለን፡፡

(ዮሐ 7፡39፣ 14፡15-18፣ 26፤ 16፡7-15፤ ሐዋ 2፡33፣ 15፡9፤ ሮሜ 8፡1-27፤ ገላ 3፡1-14፣ 4-6፤ ኤፌ 3፡14-21፤ 1ተሰ 4፡7-8፤ 2ተ 2፡13፤ 1ጴየጥ 1፡2፤ 1ዮሐ 3፡24፤ 4፡13)

IV. ቅዱሳት መጽሐፍት

4. ስድሳ ስድስቱ የብሉይ እና የአዲስ ቅዱሳት መጻሕፍት በመለኮታዊ እስትንፋሰ - እግዚአብሔር እንደተጻፉ ለደህንነታችን አስፈላጊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ፍቃድ እንደሚገልጹ እናምናለን፡፡ ስለሆነም፣ በቅዱሳ መጻሕፍት ውስት ያልታተተ አሳብ እንደ እምነት አንቀጽ አይወሰድም፡፡

(ሉቃ 24፡44-47፣ ዮሐ 10፡35፤ 1ቆሮ 15፡3-4፤ 2ጢሞ 3፡15-17፤ 1ጴጥ 1፡10-12፤ 2ጴጥ 1፡20-21)

V. የመጀመሪያው ኃጢአት እና ግለሰባዊ ኃጢአት

5. የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን አለመታዘዝ ኃጢአትን እንዳስከተለና ኃጢአትም ሞትን እንዳመጣ እናምናለን። ኃጢአት ሁለት መልኮች እንዳሉት እናምናለን፡ የመጀመሪያው ወይም የውድቀትና ግብራዊ ወይም ግለሰባዊ ኃጢአት ናቸው።

5.1. የመጀመሪያው ወይም የውድቀት ኃጢአት በአዳም ልጆች ሁሉ ላይ የደረሰ የባሕርይ መበላሸት እንደሆነ እናምናለን። ይህም ሰዎች ሁሉ ከመጀመሪያው ጽድቅ ወይም የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን በተፈጠሩ ጊዜ ከያዙት ንጽሕና እንዲርቁ፣ የእግዚአብሔር ጠላቶች እንዲሆኑ፣ መንፈሳዊ ሕይወትን እንዲያጡ፣ ወደ ክፋት እንዲያዘነብሉና ባለማቋረጥ ይህንኑ አቅጣጫ እንዲከተሉ አድርጓቸዋል። በተጨማሪም፣ የአማኝ ልብ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሙሉ በሙሉ ስካልነጻ ድረስ የመጀመሪያው ኃጢአት አዲስ በተወለደ ክርስቲያን ህይወት ውስጥ ሊኖር እንደሚችል እናምናለን።

5.2. የመጀመሪያው ኃጢአት ከግብራዊ ኃጢአት የውርስ መሠረት የሚጥል በመሆኑ መለኮታዊ መፍትሔው ተቀባይነት እስካጣ ድረስ የማንንም ተጠያቂነት የማያስከተል መሆኑን እናምናለን።

5.3. ግብራዊ ወይም የግል ኃጢአት ሥነ-ምግባራዊ ተጠያቂነት ያላቸው ሰዎች የታወቀውን የእግዚአብሔርን ሕግ ሆን ብለው በፈቃደኝነት የሚጥስበት እንደሆነ እናምናለን። ስለሆነም፣ የዚህ ዓይቱ ኃጢአት ፈቃደኛ ሳይሆኑ በዓቅም ማነስ ምክንያት ከሚጸሙት ጉድለቶች፣ ድክመቶች፣ ስህተቶች፣ ውድቀቶች ወይም ከሌሎች በወድቀት ምክንያት ከሚከሰቱ የፍጹማዊነት መመዘኛ መስናክሎች የተለየ ነው። ይሁንና፣ እነዚህ ነገሮች ከክርስቶስ መንፈስ ጋር የሚቃረኑትንና የመንፈስ ኃጢአቶች ተብለው ሊጠሩ የሚችሉትን አመለካቶች ወይም ተግባራት አያጠቃልሉም። ግላዊ ኃጢአት በቀዳሚነትና በዋናነት የፍቅርን ሕግ ማፍረስ እንደሆነ እናምናለን። ከክርስቶስ ጋር በተያያዘ ኃጢአት አለማመን ነው ልፈረጅ ይችላል።

(የመጀመሪያ ኃጢአት፡ ዘፍ 3፣ 6፡5፤ ኢዮ 15፡13፤ መዝ 51፡5፤ ኤር 17፡9-10፤ ማር 7፡21-23፤ ሮሜ 1፡18-25፤ 5፡12-14፤ 7፡1-8፡9፤ 1ቆሮ 3፡1-4፤ ገላ 5፡16-25፤ 1ዮሐ 1፡7-8)
ግብራዊ ኃጢአት፡ ማቴ 22፡36-40 (ከ1ዮሐ 3፡4 ጋር)፤ ዮሐ 8፡34-36፣ 16፡8-9፤ ሮሜ 3፡23፣ 6፡15-23፣ 8፡18-24፣ 14፡23፤ 1ኛ ዮሐ 1፡9-2፡4፣ 3፡7-10)

## VI. ስርየት[3]

[3] በ2009 ጠቅላላ ጉባኤ የተደረጉት የመተዳደሪያ ደንብ ለውጦች ይህ መጽሐፍ በሚዘጋጅበት ወቅት በመጽደቅ ላይ ነበሩ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አግድም

6. ኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበለው መከራ፣ ባፈሰሰው ደምና የመስቀል ላይ ሞቱ አማካኝነት ለሰው ልጆች ሁሉ ሙሉ ስርየትን እንዳስገኘ፣ ይም ስርየት ብቻውን የደህንነት መሠረት ከመሆኑም በላይ ለአዳም ዘር በሙሉ እንደሚበቃ እናምናለን። ስርይቱ በእግዚአብሔር ጸጋ አማካኝነት [በተለያየ ምክንያት ተጠያቂ ልሆኑ ለማይችሉ] ግብረገባዊ ኃላፊነትን ለመቀበል የማይችሉትንና ንጹሓንን ልጆችን ለማዳን ስ,ሲችል፣ ከኃላፊነት ዘመን የደረሱት ንሰሐ ገብተው በማመን ይድናሉ።

(ኢሰ 53፡5-6፣ 11፤ ማር 10፡45፣ ሉቃ 24፡46-48፤ ዮሐ 1፡29፣ 3፡14-17፤ ሐዋ 4፡10-12፤ ሮሜ 3፡21-26፣ 4፡17-25፣ 5፡6-21፤ 1ቆሮ 6፡20፤ 2ቆሮ 5፡14-21፤ ገላ 1፡3-4፣ 3፡13-14፤ ቆላ 1፡19-23፤ 1ጢሞ 2፡3-6፤ ቲቶ 2፡11-14፤ ዕብ 2፡9፣ 9፡11-14፣ 13፡12፤ 1ኛ ጴጥ 1፡18-21፣ 2፡19-25፤ 1ኛ ዮሐ 2፡1-2)

VII. ቅድመ ድነት ጸጋ

7. የሰው ልጆች በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠራቸው ትክክለኛ ትክክል ባልሆነው ነገር መካከል ያለውን ልዩነት ተረድቶ መምረጥን እንደሚያካትት እናምናለን። ይህም የሰው ልጆች ለሚፈጽሙት ሥነ ምግባራዊ ተግባር ተጠያቂዎች እንደሚሆኑ ያሳያል። በአዳም ኃጢአት ምክንያት ሰዎች ለወድቀት በመዳረጋቸው በተፈጥሯዊ ጥንካሩያቸውና እምነታቸው ወደ እግዚአብሔር ሊመለሱና ራሳቸውን ሊያዘጋጁ አይችሉም። ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ለሰዎች ሁሉ በመድረስ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ የሚመለሱ ሁሉ አምነው እንዲድኑና በእግዚአብሔር ጸጋ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ለሰዎች ሁሉ በመድረስ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ የሚመለሱ ሁሉ አምነው እንዲድኑ በእግዚአብሔር ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኘውን ተግባር እንደሚፈጽሙ ያስችላቸዋል ብለን እናምናለን።

ሰዎች ሁሉ ዳግም ልደትንና ቅድስና ካገኙ በኋላ ከእግዚአብሔር ጸጋ ወድቀው ክኀደጽን ሊፈጽሙና ከኃጢአታቸው በንሰሐ እስካተመለሱ ድረስ ለዘላለም ጥፋት ሊዳረጉ እንደሚችሉ እናምናለን።

(የእግዚአብሔር መልክና ሥነ ምግባራዊ ኃላፊነት፡ ዘፍ 1፡26-27፣ 2፡16-17፤ ዘዳ 28፡1-2፣ 30፡19፤ ኢያ 24፡15፤ ዘም 8፡3-5፤ ኢሳ 1፡8-10፤ ኤር 31፡ 9-30፤ ሕዝ 18፡1-4፤ ሚክ 6፡8፤ ሮሜ 1፡19-20፣ 2፡1-16፤ 14፡7-12፤ ገላ 6፡7-8

ተፈጥሯዊ የብቃት ማነስ፡ ኢዮ 14፡4፣ 15፡14፤ መዝ 14፡1-14፣ 51፡5፤ ዮሐ 3፡6፤ ሮሜ 3፡10-12፤ 5፡12-14፣ 20፣ 7፡14-25

ቅድመ ድነት ጸጋና የእምነት ተግባራት፡ ሕዝ 18፡25-26፤ ዮሐ 1፡12-

---

(*italics*) የተጻፉት አዳዲሶቹ ቃላት ሲሆኑ፣ በብራኬት [ ] የተቀመጡት ቃላት ግን የተሰረዙት ናቸው።

13፣ 3:6፤ ሐዋ 5:31፤ ሮሜ 5:6-8፣ 18፣ 6:15-16፣ 23፣ 10:6-8፣ 11:22፤ 1ቆሮ 2:9-14፣ 10:1-12፤ 2ቆሮ 5:18-19፤ ገላ 5:6፤ ኤፌ 2:8-10፤ ፊል 2:12-13፤ ቆላ 1:21-23፤ 2ጢሞ 4:10፤ ቲቶ 2:11-14፤ ዕብ 2:1-3፣ 3:12-15፣ :4,6፣ 10:26-31፤ ያዕ 2:18-22፣ 2ጴጥ 1:10-11፣ 2:20-22)

VIII. ንስሓ

8. የራስን በደል ተገንዝቦ በእውነተኛ ልብ ሙሉ ለሙሉ ከኃጢአት መመለስን የሚያካትተው ንስሐ ግላዊ ኃጢአትን እና ሆን ብለውም በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአተን በዓላማ ወይም በተግባር ከፈጸሙ ሰዎች ሁሉ የሚፈለግ ተግባር እንደሆነ እናምናለን፡፡ ንስሐ የሚገቡ ሰዎች ሁሉ ይቅርታ እንደተደረገላቸው አምነው ዘላለማዊ ሕይወትን ይቀበሉ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ የምህረት ተስፋ ይሰጣቸዋል፡፡

(2ዜና 7:14፤ መዝ 32:5-6፤ 51:1-17፤ ኢሳ 55: 6-7፤ ኤር 3:12-14፤ ሕዝ 18:30-32፤ 33:14-16፤ ማር 1:14-15፤ ሉቃ 3:1-14፤ 18:9-14፤ የሐዋ 2:38፤ 3:19፤ 5:31፤ 17:30-31፤ 26:16-18፤ ሮሜ 2:4፤ 2ቆሮ 7:8-11፤ 1ተሰ 1:9፤ 2ጴጥ 3:9)

IX. ጽድቅ፣ ዳግም ልደትና የልጅነት ሥልጣን

9. ጽድቅ የእግዚአብሔር የቸርነትና የዳኝነት ተግባር እንደሆነ እናምናለን፡፡ እግዚአብሔር ክርስቶስን እንደ አዳኛቸውና ጌታቸው ላመኑት ሁሉ ኃጢአትን ይቅርታ በመስጠት እንደ ጻድቃን ይቀበላቸዋል፡፡

10. ዳግም ወይም አዲስ ልደት እግዚአብሔር ንስሐ የሚገባውን ኃጢአተኛ ሥነ ምግባር ባሕርይ በማንቃት ማመን፣ ማፍቀርና መታዘዝ ሚችል መንፈሳዊ ሕይወት የሚሰጥበት የቸርነት ተግባር እንደሆነ እናምናለን፡፡

11. ልጅ መሆን የጸደቀውና ዳግም የተወለደው አማኝ የእግዚአብሔር ልጅነት ሥልጣን የሚያገኝበት እነደሆነ እናምናለን፡፡

12. መጽደቅ፣ ዳግም ልደት የልጅት ሥልጣን እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ያላቸው ሰዎች ሁሉ በተመሳሳይ ጊዜ የሚያገኟቸው በረከቶች ሲሆኑ፣ ሰዎች እነዚህን ነገሮች የሚቀበሉት ንስሐን ተከትሎ በሚመጣው እምነት አማካኝነት እንደሆነ እናምናለን፡፡ ለዚህ ሠራና የጸጋ ደረጃ መንፈስ ቅዱስ ምስክርነቱን ይሰጣል፡፡

(ሉቃ 18:14፤ ዮሐ 1:1-12-13፤ 3:3-8፤ 5:24፤ ሐዋ 13:39፤ሮሜ 1:17፣ 3:21-26፣ 28፣ 4:5-9፣ 17-25፣ 5:1፣ 16-19፣ 6:4፣ 7:6፣ 8:1፣ 15-17፤ 1ቆሮ 1:30፣ 6:11፣ 2ቆሮ 5:17-21፣ ገላ 2:16-21፣ 3:1-14፣ 26፣ 4:4-7፣ ኤፌ 1:6-7፣ 2:1፣ 4-5፤ ፊል 3:3-9፤ ቆላ 2:13፣ ቲቶ 3:4-7፤ 1ጴጥ 1:23፤ 1ዮሐ 1:9፣ 3:1-2፣ 9፣ 4:7፣ 5:1፣ 9-13፣ 18)

## X. ክርስቲያናዊ ቅድስና እና ሁለንተናዊ መቀደስ[4]

13. [ሁለንተናዊ] ቅድስና ከዳግም ልደት በኋላ አማኞች ክርስቶስ መልክ ይመስሉ [ዘንድ] [የሚደረግ] እግዚአብሔር ሥራ እንደሆነ እናምናለን፡፡ በእግዚአብሔርን ጸጋ ይኸውም በመጀመሪያው ቅድስና ወይም በዳግም ልደት (ከመጽደቅ ጋር በአንድ ወቅት በሚፈጸም)፣ በሁለንተናዊ ቅድስና እና ቀጣይነት ባለው በመክበር የሚጠናቀቅ ፍጹም የሚያደረግ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ይፈጸማል፡፡ በመክበር ወደ ልጁን መልክ ሙሉ ለሙሉ እንለወጣለን፡፡

ሁለንተናዊ ቅድስና ከዳግም ውልደት በኋላ አማኙ ከመጀመሪያው ኃጢአት ወይም ከኃጢአታዊ ተፈጥሮ ነጻ የሚሆንበት እና ለእግዚአብሔር ፈጽሞ ራሱን ወደ መስጠት የሚመጣበትና በፍቅር የሚሆን ቅዱስ መታዘዝ ፍጹም ወደ መሆነ የሚመጣበት እንደሆነ እናምናለን፡፡

በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ወይም ሙላት የሚፈጸምና ልብ ከኃጢአት የሚነጻበት በአንድ ልምምድ እና አማኞችን ለኑሮ እና አገልግሎት በሚያስችል በውስጣችን በሚኖር መንፈስ ቅዱስ የሚፈጸም ነው፡፡

ሁለንተናዊ ቅድስና ከክርስቶስ ደም የተገኘ ሲሆን፣ አማኙ ባመነ ጊዜ ወዲያውኑ በጸጋው በእምነት የሚፈጸም ሆኖ፣ ከዚህ የሚቀድመው ነገር ፍጹም መሰጠት ነው፡፡ ለዞህም የጸጋ ሥራና ደረጃ መንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ይሰጣል፡፡

ይህ ልምምድ ‹‹ክርስቲያናዊ ፍጽምና››፣ ‹‹ፍጹም ፍቅር››፣ ‹‹የልብ ንጽሕና››፣ ‹‹የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት››፣ ‹‹የበረከት ሙላት›› ፣ ብሎም ‹‹ክርስቲያናዊ ቅድስና›› በሚሉ ሀረጎች ይገለጻል፡፡

14. ንጹሕ ልብ ከበሰለ ባሕርይ እንደሚለይ እናምናለን፡፡ የመጀመሪያው ከመቅጽበት የምታገኘው የሁለንተናዊ ቅድስና ውጤት ሲሆን፣ የኋላኛው በጸጋ የማደግ ውጤት ነው፡፡

ሁለንተናዊ ቅድስ እንደ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር በጸጋ የማደግ ፍላጎተን ያካትታል፡፡ ይሁንና ይህንን ፍላጎት ሆን ብሎ ማሳደግ፣ ክርስቶስን የመምሰልን ባሕርይና ስብእና ለመላበስ ለሚያስችል መንፈሳዊ ዕድገት መሻሻል ቅደመ ሁኔታዎችና ሂደት ጥንቃቄ የታከለበት ትኩረት መስጠት ያሻል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ጥረት ሳይደረግ የአማኙ ምስክርነት ሊበለሽ፣ ጸጋውም ራሱ ሊጎዳና ልጠፋ ይችላል፡፡

(ኤር 31፡31-34፣ ህዝ 36፡25-27፣ ሚል 3፡2-3፣ ማቴ 3፡11-12፤ ሉቃ 3፡16-17፤ ዮሐ 7፡37-39፣ 14፡15-23፣ 17፡6-20፣

---

[4] በ2009 በጠቅላላ ጉባኤው የተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ ይህ መጽሕፍ በሚወጣት ጊዜ በመጽደቅ ሂደት ውስጥ ነበር፡፡ ለውጥ የተደረገባቸው ቃላት ተንጋደው የተቀመጡ ሲሆኑ በብራኬት ውስጥ ያሉት ቃላት ግን የተወገዱት ናቸው፡፡

ሐዋ 1፡5፣ 2፡1-4፣ 15፡8-9፣ ሮሜ 6፡11-13፣ 19፣ 8፡1-4፣ 8-14፣ 12፡1-2፣ 2ቆሮ 6፡14-7፡1፤ ገላ 2፡20፤ 5፡16-25፤ ኤፌ 3፡14-21፤ 5፡17-18፣ 25-27፤ ፊል 3፡10-15፤ ቆላ 3፡1-17፤ 1ተሰ 5፡23-24፤ ዕብ 4፡9-11፤ 10፡10-17፣ 12፡1-2፤ 1ዮሐ 1፡7፣ 9)

(‹‹ክርስቲናዊ ፍጽምና፣›› ‹‹ፍጹም ፍቅር››፡ ዘዳ 30፡6፣ ማቴ 5፡43-48፣ 22፡37-40፤ ሮሜ 12፡9-21፤ 13፡8-10፤ 1ቆሮ 13፤ ፊል 3፡10-15፤ ዕብ 6፡1፤ 1ዮሐ 4፡17-18

‹‹የልብ ንጽሕና››፡፡ ማቴ 5፡8፤ ሐዋ 15፡8,9፤ 1ጴጥ 1፡22፤ 1ዮሐ 3፡3

‹‹የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት›› ኤር 31፡31-34፤ ህዝ 36፡25-27፤ ሚል 3፡2-3፣ ማቴ 3፡11-12፤ ፤ቃ 3፡16-17፤ ሐዋ 1፡5፤ 2፡1-4፤ 15፡8-9፣

‹‹የበረከት ሙላት›› ሮሜ 15፡29

‹‹ክርስቲያናዊ ቅድስና›› ማቴ 5፡1-7፡29፤ ዮሐ 15፡1-11፤ ሮሜ 12፡1-15፡3፤ 2ቆሮ 7፡1፤ ኤፌ 4፡17-5፡20፤ ፊል 1፡9-11፣ 12-15፤ ቆላ 2፡20-3፡17፤ 1ተሰ 3፡13፣ 4፡7-8፤ 5፡23፤ 2ጢሞ 2፡19-22፣ ዕብ 10፡19-25፣ 12፡14፣ 12፡20-21፤ 1ጴጥ 1፡15-16፤ 2ጴጥ 1፡1-11፣ 3፡18፣ ይሁዳ 20-21)

## XI. ቤተ ክርስቲያን[5]

15. በኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነት የሚያምን ማህበረሰብ፣ በክርስቶስ አዲስ ቃል ኪዳን የተደረገለት ሕዝብ፣ በቃልና በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በአንድት የተጠራ የክርስቶስ አካል በሚገለጽባት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን፡፡

እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ህብረትና አንድነት ሕይወቷን እንድትገለጽ ጠርቷታል፡፡ ይህም የቃል ስብከት የሚገኝበትን አምልኮ፣ የቅዱስ ቁርባንና የጥምቀት ሥርዓት፣ ለክርስቶስ በመታዘዝ፣ ቅዱስ አኗኗርና በጋራ ተጠያቂነት በስሙ የሚካሄደውን አገልግሎት ያጠቃልላል፡፡

በዓለም ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ [በተቀደሰ አኗኗር፣ የወንጌል ስርጭት፣ ደቀ መዝሙርነትና አገልግሎት] በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የክርስቶስን የማዳን ሥራ መቀጠል ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ተልዕኮዋን የሚትፈጽመው በወንጌል ስርጭት፣ በትምህርት፣ ርህራሄን በማሳየት፣ ለፍትሕ በመሥራት እና ለእግዚአብሔር መንግስት ምስክር በመሆን ደቀ መዛሙርትን በማፍራት ነው፡፡

---

[5] በ2009 በጠቅላላ ጉባኤው የተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ ይህ መጽሐፍ በሚወጣት ጊዜ በመጽደቅ ሂደት ውስጥ ነበር፡፡ ለውጥ የተደረገባቸው ቃላት ተንጋደው የተቀመጡ ሲሆኑ በብራኬት ውስጥ ያሉት ቃላት ግን የተወገዱት ናቸው፡፡

ቤተ ክርስቲያን ለአከባበዋ ባህል በሚስማማ መንገድ ራሷን የምታደራጅ ታሪካዊ ተቋም ስትሆን፣ እንደ አከባቢያዊ ማህበረ ምእመንና እንደ አጽናፈ አቀፋዊ አካል ህልውናዋን ጠብቃ ትኖራለች። ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ለተወሰነ አገልግሎት የጠራቸው ሰዎች ላይታ ትሾማለች። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ምጽአት የሚጠቃለለውን ዘመን እየተጠባበቀች በአገዛዙ ሥር እንድትኖር ይጠራታል።

(ዘጸ 19፡3፤ ኤር 31፡33፤ማቴ 8፡11፣ 10፡7፣ 16፡13-19፣ 24፣ 18፡15-20፣ 28፡19-20፤ ዮሐ 17፡14-26፤ 20፡ 21-23፤ *ሀዋ* 1፡7-8፣ 2፡32-47፣ 6፡1-2፣ 13፡1፣ 14፡23፣ ሮሜ 8፡28-29፣ 4፡16፣ 10፡9-15፣ 11፡13-32፣ 12፡1-8፣ 15፡1-3፤ 1ቆሮ 3፡5-9፣ 7፡17፣ 11፡1፣ 17-33፣ 12፡3፣ 12፡3፣ 12-31፣ 14፡26-40፤ 2ቆሮ 5፡11-6፡1፤ ገላ 5፡6፣ 13-14፣ 6፡1-5፣ 14፤ ኤፌ 4፡1-17፣ 5፡25-27፤ ፊል 2፡1-16፣ 1ተሰ 4፡1-12፤ 1ጢሞ 4፡13፤ ዕብ 10፡19-25፤ 1ጴጥ 1፡1-2፣ 13፤ 2፡4-12፣ 21፤ 4፡1-2፣ 10-11፤ 1ዮሐ 4፡17፣ ይሁዳ 24፤ ራዕ 5፡9-10)

## XII. ጥምቀት

16. ጌታችን እንድንፈጽም ያዘዘን ክርስቲያናዊ ጥምቀት የኢየሱስ ክርስቶስ የስርየት በረከቶች ለማግኘት የሚያስችል የቁርባን በመፈጸም የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት፣ እንዲሁም የቅድስናንና የጽድቅናን ሙሉ የመታዘዝ ዓላማ ሊመሰክሩ እንደሚገባ እናምናለን።

ጥምቀት የአዲስ ኪዳን ምልክት ስለሆነ፣ ትናንሽ ልጆች ሊጠመቁ ይችላሉ። ይህም የሚሆነው ተገቢውን ክርስቲያናዊ ትምህርት የሚሰጧቸው ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ለማስጠመቅ ሲጠይቁ ነው። የጥምቀት ሥነ ሥረዓቱ እንደ ጠያቂው ፍላጎት ውሃን በመርጨት፣ በማፍሰስ ወይም በመድፈቅ ሊካሄድ ይችላል።

(ማቴ 3፡1-7፣ 28፡16-20፤ ሐዋ 2፡37-41፣ 8፡35-39፣ 10፡44-48፣ 16፡29-34፤ ሮሜ 6፡3-4፤ ገላ 3፡26-28፤ ቆላ 2:12; 1ጴጥ 3፡18-22)

## XIII. ቅዱስ ቁርባን (የጌታ እራት)

17. ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የመሠረተው የመታሰቢያና የጌታ እራት የመሥዋዕትነት ሞቱን የሚያውጁ ወሳኝ አዲስ ኪዳን ሥርዓት እንደሆነ እናምናለን። ይህም አማኞች ሕይወትንና ደህንነትን፣ ብሎም በክርስቶስ አማካኝነት የመንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ ተከፋዮች እንዲሆን የሚያደርግ ነው። ቅዱስ ቁርባን የሚሰጠው በተለይ ጠቀሜታውን ለመገንዘብ ለተዘጁት ሲሆን፣ እነርሱም ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ለመመስከር ይጠቀሚበታል። ይህ አማኞች የህብረት ግብዣ ስለሆነ፣ መጋበዝ ያለባቸው በክርስቶስ የሚያምኑና ለቅዱሳን ፍቀር ያላቸው ብቻ ናቸው።

(ዘጻ 12፡1-14፤ ማቴ 26፡26-29፤ ማር 14፡22-25፤ ሉቃ

22፡17-20፤ ዮሐ 6፡28-58፤ 1ቆሮ 10፡14-21፤ 11፡23-32)

## XIV. መለኮታዊ ፈውስ

18. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መለኮታዊ ፈውስ የሚያስተምረውን እውነት በማመን አባሎቻችን ለበሽተኞች የእምነ ጸሎት እንዲያደረጉ እናደፋፈራለን። በተጨማሪም፣ እግዚአብሔር በሐኪሞች አማካኝነት ሰዎችን እንደሚፈውስ እናምናለን።

(2ነገ 5፡1-19፣ መዝ 103፡1-፤ ማቴ 4፡23-24፣ 9፡18-35፤ ዮሐ 4፡46-54፣ ሐዋ 5፡12-16፣ 9፡32-4፣ 14፡8-15፤ 1ቆሮ 12፡4-11፤ 2ቆሮ 12፡7-10፤ ያዕ 5፡13-16)

## XV. የክርስቶስ ዳግም ምጸአት

19. የጌታችን ኢሱስ ክርስቶስ ዳግም እንደሚመጣ እናምናለን። በዚያን ጊዜም በሕይወት የምኖረው ሞተው የቆዩትን አንቀድማቸውም፡፤ ነገር ግን በርሱ ከጸናን ከሞት ከሚነሡት ቅዱሳን ጋር ሆነን ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል እንነጠቃለን። ከዚያም ለዘላለም ጌታ ጋር እንኖራለን።

(ማቴ 25፡31-46፤ ዮሐ 14፡1-3፤ ዮሐ 1፡9-11፤ ፊል 3፡20-21፤ 1ቆሮ 4፡13-18፤ ቲቶ 2፡11-14፤ ዕብ 9፡26-28፤ 2ጴት 3፡3-15፤ ራዕ 1፡7-8፣ 22፡7-20)

## XVI. የሙታን ትንሣኤ፣ ፍርድና የዘላለም ሕይወት

20. ኃጢአተኞችም ሆኑ ጻድቃን ከሞት ተነሥተው ከመንፈሳቸው ጋር እንደሚገናኙ እናምናለን። ‹‹መልካም ያደረጉ ለሕይወት ይነሣሉ። ክፉም ያደረጉ ለኩነኔ ይነሣሉ።››

21. ወደ ፊት እያንዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ቀርቦ ፍርድን እንደሚቀበል። ክፉም ያደረጉ ፤ኩነኔ ይነሣሉ።››

22. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ያመኑትና በታዛዥነት የተከተሉት ሁሉ የከበረ ዘላለማዊ ሕይወት እንደሚገኙ እናምናለን። እስከ መጨረሳ ንሰሓ ያለገቡት ደግሞ በሲኦል ውስጥ ይሠቃያሉ።

(ዘፍ 18፡25፤ 1 ሳሙ 2፡10፤ መዝ 50፡6፤ ኢሳ 26፡19፤ ዳን 12፡2-3፤ ማቴ 25፡31-46፤ ማር 9፡43-48፤ ሉቃ 16፡19-31፣ 20፡27-38፤ ዮሐ 3፡16-18፤ 5፡25-29፤ 11፡21-27፣፣ ሐዋ 17፡30-31፤ ሮሜ 2፡1-16፤ 14፡7-12፤ 1ቆሮ 15፡12-58፤ 2ቆሮ 5፡10፤ 2ቆሮ 5፡10፤ 2ተሰ 1፡5-10፤ ራዕ 20፡11-15፤ 22፡1-15)

### ለቤተ ክርስቲያን አባላት የተሰጠ መመሪያ

ኢየሱስ እንደ ግል አዳኛቸው ተቀብለው፤ ከናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ጋር ለመወሃድ ህብረት ለማድረግ የሚፈልጉ ሁሉ በመንፈሳዊ አኗኗራቸውና በተቀደሰ

አካሄዳቸው መደናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል። የእግዚአብሔር ቃልም እንዴት መኖር እንዳለብን መመሪያ ይሰጠናል።

**የቤተ ክርስቲያን አባላት እነዚህን ነገሮች ማድረግ ይጠበቅባቸዋል (27.1)**

(1) የእግዚአብሔር በሙሉ ልባችን፣ ነፍሳችን፣ አሳባችንና ጉልበታችን መውደድ ባልንጀራችንን እንደ ራሳችን መውደድ (ዘጸ 20፡3-6፣ ዘሌ 19፡17-18፣ ዘዳ 5፡7-10፣ 6፡4-5፤ ማር 12፡28-31፣ ሮሜ 13፡8-10)።

(2) ላልዳኑት ወንጌሉን መመስከር፣ ወደ ጌታ ቤት መጋበዝና የክርስቶስን አዳኝነት እንዲቀበሉ ማበረታታት (ማቴ 28፡19-20፤ ሐዋ 1፡8፤ ሮሜ 1፡14-16፤ 2ቆሮ 5፡18-20)

(3) ለሰዎች ሁሉ ትሑትና ማድረግና እርስ በርስ መረዳዳት (ኤፌ 4፡32፣ ቲቶ 3፡2፤ 1ጴየጥ 2፡17፤ 1ዮሐ 3፡18)።

(4) ለአማኞችም መልካም ማድረግና እርስ በርስ መረዳዳት (ሮሜ 12፡13፣ ገላ 6፡2፣ 10፤ ቆላ 3፡12-14)።

(5) በተቻለ መጠን የተራቡትን መመገብ፣ የተራቆቱትን በማልበስ፣ የታመሙትንና የታሠሩትን በመጎብኘት፣ ድሆችን በመርዳት ለሰዎች ነፍስና ሥጋ መልካምን ለማድረግ መጣር (ማቴ 25፡35-36፤ 2ቆሮ 9፡8-10፤ ገላ 2፡10፤ ያዕ 2፡15-16፤ 1ዮሐ 3፡17-18)።

(6) በአሥራትና በምጽዋት የቤተ ክርስቲያንን ሥራን አገልግሎት መደገፍ (ሚል 3፡10፤ ሉቃ 6፡38፤1ቆሮ 9፡14፤ 16፡2፤ 2ቆሮ 9፡6-10፤ ፊል 4፡15-19)።

(7) የጉባኤ አምልኮን (ዕብ 10፡25)፣ የቃሉን አገልግሎት (የሐዋ 2፡42)፣ የጌታ ራት (1ቆሮ 11፡23-30)፣ ቅድሳት መጽሕፋትን ማጥናትንና ማሰላሰልን (ሐዋ 17፡11፤ 2ጢሞ 2፡15፣ 3፡14-16)፣ የግልና የቤተሰብ የጽሞና ጊዜያትና (ዘዳ 6፡6-7፣ ማቴ 6፡6) ጨምሮ የእግዚአብሔርን ትእዛዝትና የጸጋ ተግባራትብ ማከናወን።

የቤተ ክርስቲያን አባላት እነዚህን ነገሮች ማድረግ አይጠበቅባቸውም (27.2)

(1) የእግዚአብሔር ስም በክንቱ መጥራት (ዘጸ 20፡7፤ ዘላ 19፡12፤ ያዕ 5፡12)።

(2) አላስፈላጊ በሁነ ዓለማዊ ተግባራት ላይ በመስተፍ የጌታ ቀን ማርከስ (ዘጸ 20፡8-11፣ ኢሳ 58፡13-14፣ ማር 2፡27-28)፣ ሐዋ 20፡7፤ ራዕ 1፡10)።

(3) ከጋብቻ በፊት ሆነ በጋብቻ ውጭ የሚፈጸሙ የትኞቹም ወሲባዊ እርኩስቶች፣ ወይም የባሕርይ ብልሽቶች (ዘጸ 20፡14፤ ማቴ 5፡27-32፤ 1ቆሮ 6፡9-11፤ ገላ 5፡19፤ 1ቆሮ 4፡3-7)።

(4) ሥጋዊና አእምሯ ጤንነትን የሚጎዱ ልማዶችና ተግባራት (ምሳ 20፡1፣ 23፡1-3፤ 1ቆሮ 6፡17-20፤ 2ቆሮ 7፡1፤ ኤፌ 5፡18)።

(5) መጣለት፣ በክፉ ፈንታ ክፉ መመለስ፣ማማት፣ መሳደብ፣ የሰዎችን መልካም ስም የሚያበላሹ ወሬዎችን መዛመት (2ቆሮ 12፡20፤ ገላ 5፡15፤ ኤፌ 4፡30-32፤ ያዕ 3፡5-18፤ 1ቆሮ 3፡9-10)፡፤

(6) አማኝ አለመሆን፣ በግዥ ሽያጭ ላይ ማጭበርበር፣ በሐሰት መመስከርና የጨለማን ሥራዎች መውደድ (ዘላ 19፡10-11፤ ሮሜ 12፡17፤ 1ቆሮ 6፡7-10)።

(7) በአለባበስም ሆነ በባሕርይ መኩራራት። ምእመኖቻችን ቅድስናን የሚሳይ ተገቢውን ክርስቲያናዊ አለባበስ ሊከተሉ ይገባል (ምሳ 29 29፡23፤ 1ጢሞ 2፡8-10፤ ያዐ 4፡6፤ 1ጴጥ 3፡3-4፤ 1ዮሐ 2፡15-17)።

(8) የእግዚአብሔር ስም የማያስከብር ሙዚቃ፣ ሥነ ጽሑፍና መዝናኛ (1ቆሮ 10፡31፤ 2ቆሮ 6፡14-17፤ ያዕ 4፡4)።

**ሁል ጊዜ፡**

**ከቤተ ክርስቲያን ጋ በሙሉ ልብ ህብረት ለማድረግ የተዘጋጀህ ሁን። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመቃወም ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያኗ አስተምህሮ እና ደንቦች የተገዛህ በመሆን በቤተ ክርስቲያኗ የወንጌል ስርጭት ውስጥ አስፈላጊውን ተሳትፎ አድርግ (ኤፌ** 2:18-22; 4:1-3, 11-16; ፊል 2:1-8; I ጴጥ 2:9-10)
**የክርስቲያናዊ አካሄድ ቃል ኪዳን**

*(This is a shortened and simplified version of the Covenant of Christian Conduct. You may refer to the Manual (pages 46-60) for the official text and fuller details)*

## ሀ. የክርስቲያን ሕይወት

33. ቤተ ክርስቲያን ከኃጢአት ሁሉ በክርስቶስ ወደሚገኝ አዲስ ሕይወት ልንሻገር እንደሚችንች በደስታ ትሰብካለች። እኛ ክርስቲኖች በእግዚአብሔር ጸጋ ‹‹አሮጌውን ሰው››፣ ማለትም የቀድሞውን ባሕርይና አስተሳሰብ ልናስወግድና ‹‹አዲሱን ሰው››፣ ማትም አዲሱንና የተቀደሰውን ሕይወት፣ እንዲሁም የክርስቶስን አስተሳሰብ ልንለብስ እንችላለን።

(ኤፌ. 4፡17-24)

33.1. የናዛሬን ቤተ ክርስቲያን ዘመን የማይሽራቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ መርሆች ለአሁኑ ዘመን ማህረሰብ ለማቅረብ አልማለች። ይህም የቤተ ክርስቲያንኒቱን አስተምህሮዎችና ደንቦች በብዙ አገሮችና በተለያዩ ባሕሎች ውስጥ እንዲታወቁ ያደርጋል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተደግመው የቀረቡት አሥት እዛዛት የክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር መሠረቶች እንደሆኑና በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ ልንታዘዛቸው እንደሚገባ እናምናለን።

33.2. እንደዚሁም የክርስቲያኖች የጋራ ሕሊናዊ ሚዛን በመንፈስ ቅዱስ ብርሃንና ምርት በሚገዛበት ጊዜ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደረግ እንገነዘባለን። የናዛሬን ቤተ ክርስቲያን እንደ ዓለም አቀፋዊ የክርስቶስ አካል መግለጫ ክርስቲያኖችን ወደ ቅድስና ሥነ ምግባር የመምራት ኃላፊበት እንዳላት ትገነዘባለች። የቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪካዊ የሥነ ምግባር መመዘኛዎች በከፊል እንደሚከተለው ተገልጸዋል። እነዚህን መመዘኛዎች ወደ ተቀደሰ አኗኗር እንደሚያመሩና እገዛዎች ልብ ብለን ልናጤናቸውና ልንከተላቸው ይገባል። የቤተ ክርስቲያኒቱን የሕሊና ሚዛን የማይከተሉ ሰዎች ራሳቸውንና የቤተ ክርስቲያኒቱን ምስክርነት ይጎዳሉ። ባሕላዊ ልምዶች ከበላይ አካላት ቦርድ ቀርበው ሊጸድቁ ይገባል።

33.3. የናዛሬን ቤተ ክርስቲያን ይህ አዲስ እና ቅዱስ የሆነው የአኗኗር ዘይቤ በጎረቤቶቻችን ላይ በነፍስ፣ በአእምሮ እና አካል ልናደረግ የማይገባቸውን ተግባራት እና ልንፈጽማቸው የሚገቡ ከፍቅር የሚመነጩ የድነት ተግባራትን ያካትታል። አንዱ ከፍቅር የሚነሣ የድነት ተግባር ኢየሱስ ከዚህች ዓለም ድሆች ጋር የነበረው ልዩ ግንኙነትና የእርሱ ደቀ መዛሙርትም እንዲኖራቸው ያዘዘው ነው። በዚህም የእርሱ ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ ቀላል እና ለሀብት ትኩረት እና የተጋነነ ትኩረት ከመስጠት እንድትወጣ ነው፤ ሁለተኛ ራሷን ድሆችን እና የተገለሉትን መንከባከብ፣ መመገብ፣ ማልበስ እና መጠልያ መስጠት እንድትችል ነው። በመጸሐፍ ቅዱስ ውስጥ እና በኢየሱስ ሕይወት እና ምሳሌን በመከተል እግዚአብሔር ከድሆችን፣ የተጨቆኑትን እና በማህበረሰቡ ውስጥ ለራሳቸው መናገር ከማችሉ ሰዎችን ጋር እንደሚቆም እና እነርሱን እንደሚረዳ ያሳያል። በተመሳሳይ መልኩ ከድሆች ጋር መቆም እና እነርሱን መደገፍ አለብን። ለድሆች የሚደረግ የርህራሄ አገልግሎት ለልግስናን እንዲሁም ለድሆች የሚደረግ የእኩልነት እና የፍትሕ እድልንም እንደሚያካትት እናምናለን። ከዚህ በተጨማር ክርስቲያኖች ለድሆች ያለባቸው ኃላፊነት እምነቱ በፍቅር በውስጡ እንዲሠራ የሚፈልግ እያንዳንዱ አማኝ

የሕይወቱ ዋና ክፍል እንደሆነ እናምናለን። ክርስቲያናዊ ቅድስና ለድሆች ከሚደረግ አገልግሎት እንደማይለይ፤ ይህም ክርስቲያኖች ከግላዊ ፍጽምና ልምምድ በላይ በመሄድ ይበልጥ ፍትሕ እንድሠፍንና እኩልነት የሠፈነበት ማህበረሰብ እና ዓለም እንዲኖር የሚያደርግ መሆኑን እናምናለን።

(ዘጸ 23:11፤ ዘዳ 15:7፤ ዘም 41:1፣ 82:3፤ ምሳ 19:17፣ 21:13፣ 22:9፤ ኤር 22:16፤ ማቴ 19:21፤ ሉቃ 12:33፤ ሐዋ 20:35፣ 2ቆሮ 9:6፤ ገላ 2:10)

33.4. *መወገድ የሚገባቸውን ልምዶች የምንዘረዝረው በዓለም ውስጥ የሚገኙ የክፋት ሥራዎች ዘርዝሮ መጨረስ እንደማይቻል ሳንገዘን ቀርተን አይደለም። ስለሆነም፣ ምእመኖቻችን ‹‹ሁሉን መርምሩ። መልካሙን ያዙ። ከክፉ ራቁ››*(1 ተሰለ 5:21-22) *የሚለውን የመጸሐፍ ቅዱስ ቃል ያስታውሱና የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ እያደመጡ ከዚግ የፊደል ሕግ ያፈነገጡትን ነገሮች መከታተል ይኖርባቸዋል።*

33.5. *መሪዎቻችንና መጋቢዎቻችን በመጽሔሮቻችንም ሆኑ በመድረኮች ላይ ክፉውን ከመልካሙ ለመለየት በሚያስችሉት መሠረታዊ እውነቶች ላይ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል።*

33.6. *ትምህርት ለማህበረሰቡ ማህበራዊና መንፈሳዊ ደህንነት ወሳኝ ነው። የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሰዎችን ሁሉ የማስተማር ኃላፊነት አለባቸው። ነገር ግን በመጠነከር ላይ ያሉት የተወሠኑት ሲሆኑ፣ የመንግሥት ደንብም የክርስትና ትምህርቶችን እንዲያስተምሩ አይፈቅዱላቸውም። እንደ ሰንበት ትምህርት ቤት፣ የቀን ትምህርት ቤት፣ የልጆች እንክባኬ ማዕከል፣ የአዋቂዎች እንክብካቤ ማዕከል፣ ኮሌጆችና ሰሚናሪዎች ያሉት የናዛሪን የትምህርት ተቋማትና ድርጅቶች ለልጆች፣ ለወጣቶችና ለአዋቂዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆችን በማስተማር አስተምህሮቻችንን ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል። ይህም ብዙውን ዓለማዊ ሰብአዊነትን ያስተማሩ የተቀደሰ አኗኗርን መርሆች ለማስተማር ባልቻሉት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ምትክ ወይም ከዚያ በተጨማሪ ሊሰጥ የሚገባ ነው። የሕዝባዊ ትምህርት ቤቶች በቤት ውስጥ ትምህርት መተካት ያሻል። በተጨማሪም፣ ክርስቲያኖች ለሕዝብ ትምህርት ቤቶች በመመስከር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊመልሷቸው ይገባል።*

*ማቴዎስ 5:13-14*

*34.* በተለይ ክርስቲያኖች የሚከተሉትን ነገሮች ከማድረግ እንዲቆጠቡ እንጠይቃለን።

**34.1. ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን የሚያበላሹ መዝናኛዎች።**

ምእመኖቻችን እንደ ክርስቲያን ግለሰቦችም ሆነ በክርስቲያናዊ ቤተሰብ ውስጥ በሦስት መርሆች ራሳቸውን ሊያስተዳድሩ ይገባል። አንደኛው የመዝናኛ ጊዜ ክርስቲያናዊ መጋቢነት ነው። ሁለተኛው ከሁሉም የላቀውን ሥነ መግባራዊ የክርስትና አኗኗር መመዘኛ መከተል እንደሚያስፈልግ የሚያስረዳውን ክርስቲያናዊ ግዴታ ማስታወስ ነው። ሥነ ምግባራዊ አኗኗር በጣም ግራ በሚያጋባበት በአሁኑ ዘመን እንደ ወቅታዊ ሠነ ጽሑፍ፣ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ኮፕፒዩተሮችና ኢንተርኔትን በመሳሰሉ ነገሮች አማካኝነት ክፉ ወደ ተቀደሰው ክርስቲያናዊ ቤት ሾልኮ ሊገባ ስለሚችል፣ ቤታችን ዓለማዊ እንዳይሆን ከፍተኛ ጥረት ማደረግ አለብን። ነገር ግን ለተቀደሰው አኗኗርና ለመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ትኩረት የሚሰጥ መዝናኛ ሊበረታታ ይገባዋል። በተለይ ወጣቶቻችን የሥነ ጥበብና የብዙኃን መገናኛ ስጦታዎቻቸውን በመጠቀም የህንን የተበላሸ ባሕል በመልካም አመለካከት እንዲለውጡት እናበረታታለን። ሦስተኛው መርህ የእግዚአብሔርን ስም ከሚያሰድብ ወይም ዝቅ ከሚያደረግ፣ ብሎም እንደ ጭካኔ፣ ስሜታዊ እርካታ፣ ወሲባዊ ሥነ ጽሑፎች፣ የተቀደሱ ሃይማኖታዊ ነገሮችን ከሚያረክሱና ከምትሕ መራቅ እንደሚያስፈልግ ያስረዳል። እንደዚሁም የዚህ ዓይነት መዝናኛዎችን በማቅረብ የንግድ ተግባራቸውን የሚያከናውኑትን ድርጅቶች ለማወደም መጣር ያሻል። ይህም ጭካኔን፣ ስሜታዊነትን፣ ወሲባዊነትን፣ የተቀደሱ ሃይማኖታዊ ነገሮችን ማርከስንና ምትሐትን፣ የእግዚአብሔርን የልብና የሕይወት ቅድስና መመዘኛን ያንቋሸሹ የዓለምን የዓማዊነት ፍልስፍና ከሚሰብኩ፣ ከሚያመርቱ ወይም ከሚያስተዋውቁ የመዝናኛና የመገናኛ ብዙሃን ሙሉ በሙሉ መራቅን ያካትታል።

ይህም የነዚህን የክርስቲያናዊ አኗኗር ሥነ ምግባራዊ መመዘኛዎችን ስብከትና ማስተማር ወሳኝነት ከማመልከቱም በላይ ምእመኖቻችን የቅድስናን ‹‹የላቀ መንገድ›› ለመከተል በጸሎት ላይ የተመረኮዘ ምርመራ እንዲያካሂዱ ይረዳል። ስለሆነም መሪዎቻችንና መጋቢወፐቻችን በመጽሔቶቻችንና በምስባኮቻችን ለነዚህ መሠረታዊ እውነቶች ከፍተኛ አጽኖት እንዲሰጡና በመልካምና በክፉ መካከል የመለየትን ነርህ እንዲያዳብሩ እንጠይቃለን።

‹‹ምክንያትህን የሚያደክም፣ የሕሊናህን አፍቃሪነት የሚጎዳ፣ ስለ እግዚአብሔር ያለህ አመለካከት የሚያደበዝዝ ወይም መንፈሳዊ ነገሮችህን የሚቀማ ነገር ሁሉ ለአንተ ኃጢአት ነው›› በማለት እናቱ ለጆን ዌስሊ የሰጡት መመዘና የዚህ የመለየት ትምህርት መሠረት ነው። (33.2 — 33.4፣ 903.12 — 3.14)

(ሮሜ 14፡7-13፣ 1ቆሮ 10፡31-33፤ ኤፌ 5፡1-18፤ ፊል 4፡8-9፤ 1ጴጥ 1፡13-17፤ 2ጴጥ 1፡3-11)

*34.2.* *ሕጋዊም ሆኑ ሕጋዊ ያልሆኑ ሎተሪዎችና ማናቸውም የቁማር ተግባራት። ቤተ ክርስቲያናችን የነዚህን ልመምዶች የኋላ ኋላ ውጤት ለግለሰቡም ሆነ ለማህበረሰቡ ጎጂ እንሆነ ታምናለች።*

(ማቴ 6፡24-34፤ 2ተሰ 3፡6-13፤ 1ጢሞ 6፡6-11፤ ዕብ 13፡5-6፤ 1ዮሐ 2፡15-17)

*34.3.* *በመሃላ የተገደበ የምሥጥር አባልነት ወይም የምሥጥራዊ የሆነ ማህበራት አባልነት። የነዚህ ድርጅቶች የሐሰት ሃይማኖታዊ ባሕርይ የክርስቲያኑን መሰጠት የሚያለሳልስ ሲሆን፣ ምሥጢራዊነታቸው ደግሞ ክርስቲያም በግልጽ እንዳይመሰክር ይከላከላል። ይህ ጉዳይ ስለ ቤተ ክርስቲያን አባልነት ከአንቀጽ* 112.1 *ጋር በአንድነት ልታይ ይገባዋል።*

(1ቆሮ 1፡26-31፣ 2ቆሮ 6፡14-7፡1፤ ኤፌ 5፡11-16፤ *ያዕ* 4፡4፤ 1ዮሐ 2፡15-17)

*34.4.* *መንፈሳዊ ዕድገትን የሚያደናቅፉና ተገቢውን ሥነ ምግባራዊ ባሕርይ የሚያፋልስ የትኛውም ዓይነት ዳንስ።*

(ማቴ 22፡36-39፤ ሮሜ 12፡1-2፤ 1ቆሮ 10፡31-33፤ *ፊል* 1፡9-11፤ *ቆላ* 3፡1-17)

*34.5.* *አስካሪ መጠጦችን፣ ሱስ አስያዥ ዕፆችን፣ የትኛውንም ዓነት ሲጋራ መግዛት፣ ማስተላለፍ፣ መደገፍ፣ መሸጫ ስፍራዎችን ማከራየት።*

*የአልኮል መጠጥ ጎጂነት በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በሰው ልጆች ልምምድና በሕክምና ሳይንስ የተረጋገጠ ስለሆነ፣ ለተቀደሰ ሕይወት ራሳችንን የሰጠን የእምት ማህበረሰብ የሆንን ምእመናን ከአልኮል መጠጦች ሙሉ በሙሉ መራቅ ይኖርብናል። መጽሐፍ ቅዱስ ሰውነታችን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆነ ይነግረናል። ስለሆነም ለራሳችንና ለሌሎች ፍቀርን ለመግለጽ ምእመኖቻችን ሙሉ ለሙሙ ከሱስ አስያዥ ነገሮች እንዲቆጠቡ እንጠቃለን።*
*በተጨማሪም፣ የአልኮልንና የሲጋራን ስርጭት ለመቀነስ ሕጋዊ መስመሮችን ተከትለን እንድንሠራ ክርስቲያናዊ ማህበራዊ ኃላፊበታችን ያስገድደናል። በዓለማችን ውስጥ የሚታየው አልኮልን አላግባብ የመጠቀም ሁኔታ ለሌሎች ምስክሮች የመሆን ሚናችንን እንድንጫወት ያሳስበናል* (903.1፣ 904.14- 4.16)
(*ምሳ* 20፡፣ 23፡29-24፡2፤ *ሆሴ* 4፡10-11፤ *ዕን* 2፡5፤ ሮሜ 13ለ8፣ 14፡15-21፣ 15፡1-2፤ 1ቆሮ 3፡16፣ 6፡9-12፣ 19-20፣ 10፡31-33፤ *ገላ* 5፡13-14፤ ኤፌ 5፡18) (413.11፣ 427.7-27.8፣ 428.2፣ 429.1፣ 802)

34.6. በሐኪም ያልታዘዘ የቅዠት መድሃኒት፣ የአእምሮ ማነቃቂያ መውሰድና የታዘዙትን የሕክምና መድሃኒቶች በአግባቡ አለመውሰድ ። እንዲህ ያሉ መዳሃኒቶችን መውሰድ የሚገባው በሐክም ትእዛዝና በሕክምና ባለሞያ ቁጥጥር ሥር ብቻ በመሆን ነው።

### ለ. ጋብቻና ፍቺ እና/ወይም የቃል ኪዳን መፍረስ[6]

35. በክርስቶስ ኢየሱስ የጋራ ሰንሰለት የተያያዘው ክርስቲያም ቤተሰብ የፍቅር፣ የህብረትና የአምልኮ ጉልላት ሲሆን፣ የቤተሰብ ትስስሮች በቀላሉ በሚበጡበት በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። እንዲህ ዓይነት ትምህርቶችና ልምምዶች የቤተሰብ ግንኙቶችን እንደሚጠናክሩ ለቤተ ክርስቲያናችንና ለጉባኤዎችን ለማሳሰብ እንደወዳለን፡፤ በተለይም የመጽሐፍ ቅዱስን የዘላቂ ጋብቻ አሳብ በግልጽ ማስተማርና መሰበክ አስፈላጊ መሆኑን ለአገልጋዮቻችን ለማሳሰብ እንሻለን።

እግዚአብሔር ጋብቻን የመሠረተው የሙሴ ሕግ ከመሰጠቱ በፊት ሲሆን፣ ይህም በሐዋርያት ሥልጣን ‹‹ክቡር›› መሆኑ ተገልጸአል። ይህ አንዱ ወንድና እንዲት ሴት ለህረት፣ ለመረዳዳትና ትውልድን ለመቀጠል የሚወስኑበት የጋራ እርምጃ ነው። ምእመኖቻችን ይህንን ታላቅ ጋብቻ በአክብሮት እንዲመለከቱትና የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ምሪት እንዲሹ፣ የታሰበው ጋብቻ የመጽሐፍ ቅዱስን መመዘኛዎች ካሟላ ብቻ ተግባራዊ እንዲያደርጉት ይሁን። እግዚአብሔር በጋብቻ ውስጥ ያስቀመጣቸውን በረከቶች ማለትም የተቀደሰ አጋርነትን፣ ወላጅነትንና ፍቅርን አጥብቀው ሊሹ ይገባል። እነዚህም የቤተሰብ ግንባታ ንጥረተ ነገሮች ናቸው። የጋብቻ ቃል ኪዳን ሁለቱም በሕይወት እስካሉ ድረስ ሊላላ የማይችል ሰንሰለት ስለሆነ፣ ይህን ቃል ኪዳን ማፍረሱ መለኮታዊውን የትዳር ዘለቄታዊነት ዕቅድ መተላለፍ ይሆናል።
(ዘፍ 1፡26-28፣ 31፣ 2፡21-24፣ ሚል 2፡13-16፤ ማቴ 19፡3-9፤ ዮሐ 2፡1-11፤ ኤፌ 5፡21-6፡4፤ 1ተሰ 4፡3-8፤ ዕብ 13፡4)።

35.1. በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት፣ ጋብቻ ወንድና ሴት ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ያሳየውን ፍቅር በሚያንጸባርቅ መልኩ ዕድሜ ልካቸውን አብረው ለመኖር ቃል ኪዳን የሚገቡበት ነው። ጋብቻ ዘላቂ እንዲሆን እንደ መታቀዱ መጠን ፍቺ የክርስቶስን ግልጽ ትምህርት ያፋልሳል። ይሁንና፣ በንሰሓ፣ በእምነትና በትሕትና ወደ እግዚአብሔር ፊት ከቀረብን እንዲህ ኣይነት የመተላለፍ ተግባራን ይቅር የማለት ጸጋ አለው። አንዳንድ ሰዎች

[6] በዚህ ቃል ኪዳን ውስጥ የጋብቻ ፍቺ ትርጉም የሕግ ቋንቋ የሆነውን ፍቺ ለመተካት ‹‹የጋብቻ መፍረስ›› የሚለውን ቃል ያካትታል።

ከፈቃዳቸው ውጭ ከሕጋዊ ወይም አካላዊ ችግሮች የተነሣ ለመፋታት ይገደዳሉ።

(ዘፍ 2፡21-24፣ ማር 10፡2-12፤ ሉቃ 7፡36-50፤ 16፡18፤ ዮሐ 7፡53-8፡11፤ 1ቆሮ 6፡9-11፤ 7፡10-16፤ ኤፌ 5፡25-33)

35.2. የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ለጋብቻ ቃል ኪዳኖች ከፍተኛ ትንቃቄዎችን እንዲያደረጉ ይመክራል። በተቻላቸው ዓቅም ሁሉ ለማህበረ ምእመናቻቸው የጋብቻብ ቅዱስነት ማስተማርአለባቸው። በሚቻሉው መንገድ ቅድመ ጋብቻ ምክሮችን ሊሰጡና ለተፋቱትም ተገቢውን ምሪት ሊሰጧቸው ይገባል። ለመጋባት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያላቸው ግለሰቦች ብቻ ማግባት ይኖርባቸዋል። (107 — 7.1)

35.3. የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ጋብቻቸው አስደሳች ሳይሆን በሚቀርበት ጊዜ ከቃል ኪዳናቸውና ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር በሚዛመድ መልኩ ትዳራቸውን ለማዳን መጣር ይኖርባቸዋል። ይህንንም በሚያደርጉበት ጊዜ ዋና ዓላማቸው ትዳራቸው ከመፍረስ ማትረፍ፣ መልካሙን የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ስም ከመሰደብ መታደግ ሊሆን ይገባል። ከፍተኛ የጋቻ ችግሮች ያሉባቸው ሰዎች ከመጋቢዎቻቸውና ከሌሎች መንፈሳዊ መሪዎች ምክሮችን መቀበል ይኖርባቸዋል። ባለትዳሮቹ ይህንን ክርስቲያናዊ መፍትሔ በጥሩ እምነት ሳይከተሉ ቀርተው ቢፋቱና ዳግም ቢገቡ በአንቀጽ 504- 4.2 በተደነገገው መሠረት አንዳቸው ወይም ሁለቱም ይቀጣሉ።

35.4. ካለማወቅ፣ ከኃጢአትና ከሰበአዊ የፍጹምነት ጉድለት የተነሣ ብዙ ሰዎች የተቀደሰውን መለከታዊ ዕቅድ ይጥሳሉ። ክርስቶስ የሰማርያዊቷን ሴት እንዳዳናት ሁሉ እነዚህን ሰዎች ሊያድን እንደሚችልና በእግዚአብሔር የጋብቻ ዕቅድ ላይ የሚፈጸም ኃጢአት ሰውን ከወንጌሉ ይቅርታ ሊያገል የማይችል መሆኑን እናምናለን። ባለትዳሮች ተፋተው ሌላ ትዳር ከመሠረቱ የእግዚአብሔር ጸጋ ሊሹና በጋብቻ ግንኙነታቸው የሚያድን እገዛውን ሊፈልጉ ይገባል። እንዲህ ዓይነት ሰዎች ዳግም ለመወለዳቸውና በክርስቲያናዊ ጋብቻ ቅዱስነት ለማመናቸው መረጃ ካቀረቡ የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን በአባልነት ልትቀበላቸው ትችላለች። (27፣ 107.1)

### ሐ. የሰው ልጅ ሕይወት ክቡርነት

36. የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን በሰው ልጅ ነፍስ ክቡርነት ታምናለች እንዲሁም ከውርጃ፣ በማህፀን ውስጥ ከሚደረግ ጥናት፣ በማደንዘዥ መግደል እና የአካል ጎዳተኞች ወይም የእድሜ ባለጠጎች ሕክምና እንዳይከለከሉ ለመጠበቅ ጥረተ ታደርጋለች።

**ውርጃን መከላከል፡፡** የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን በፈጣሪ አምላክ እንደተደነገገው የሰው ልጅ ሕይወት ቅዱስ እንደሆነና ይህም ገና ያልተወለደን ሕፃን እንደሚጨመር ታምናለች፡፡ ስለሆነም ለራስ ምቾትም ሆነ ለሥነ ሕዝብ ቁጥጥር ሲባል የሚካሄደውም ማንኛውን ዓይነት ውርጃ እንቃወማለን፡፡ ውርጃ የሚፈቅትን ሕጎች እንቃወማለን፡፡ እናት፣ ሕፃኑ ወይም ሁለቱም ለአደጋ የሚጋለጡባቸው ሁኔታዎች አልፎ አልፎ እንደሚገጥሙ በመረዳት ክርስቲያን እናቶች ከሐኪሞችና ከክርስቲያን አማካሪዎች ጋር ከተወያዩ በኋላ ብቻ ፅንስ ሊቋረጥ እንደሚገባ እናምናለን፡፡

ውርጃን ስንቃወም ለእናቶችና ልጆች እንክብካቤ የሚያግዙትን መርሐ ግንሮች መጀመርና መደገፍ ይኖርበታል፡፡ ያልተፈለገ እርግዝና የሚያስከትለው ቀውስ አማኝ ማህበረሰቦች ፍቅርን፣ ጸሎትንና ምክርን በመስጠት እንዲነሣሡ ይጠራል፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ምክር መስጫ ማዕከላትን፣ ሊወልዱ ለደረሱት እናቶች የመጠለያ ስፍራዎችን በማዘጋጀትና ክርስቲያን የማደጎ ወላችን በማዘጋጀት አገልግሎት መስጠት ይቻላል፡፡

የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ያልተፈለገ እርግዝናን ማጨናገፍ እንደ አማራጭ የሚወስዱ ሰዎች ክርስቲያናዊ ወሲባዊ ሃላፊነቶችን ቸል በማለታቸው ምክንያት መሆኑን ትገነዘባለች፡፡ ስለሆነም ቤተ ክርስቲያኒቱ ሰዎች የአዲስ ኪዳን ሥነ ምግባር ተግባራዊ እንዲያደረጉና ለሥነ ምግባራዊ ውሳኔ ሰጭነት ምሪት የሚሰጠውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አቀጣጫ እንዲከተሉ ጥሩዋን ታቀርባለች፡፡

> (ዘጸ 20፡13፣ 21፡12-16፤ ኢዮ 31፡15፣ መዝ 22፡9፤ 139፡3-16፤ ኢሳ 44፡2፣ 24፤ 49፡5፤ ሉቃ 1፡23-25፤ 36-45፤ ሮሜ 12፡1-2፤ 1ቆሮ 6፡16፣ 7፤ 1ተሰ 4፡3-6)

የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን በዚህ የውርጃ ጉዳይ ብዙ ሰዎች እንደሚጠቁ ትገነዘባለች፡፡ እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እና አማኝ ልጅ ላስወረዱ እያንዳንዱ ሰዎች የእግዚአብሔር የይቅርታ መልዕክት እንድያደርሱ ይገደዳሉ፡፡ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን የድነት ማህበረሰብ መሆን እና በፍቃዳቸው ውርጃን በማካሄዳቸው ምክንያት አካላዊ፣ ስነ ልቦናዊ እና መንፈሳዊ ስቃይ ለደረሰባቸው ተስፋ መሆን ይጠበቅባታል፡፡

(ሮሜ 3፡22-24፤ ገላ 6፡1)

**ዘረመላዊ ምህንድስና እና የዘረመል ሕክምና፡** የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ለዘረመል ሕክምና የሚውል የዘረመላዊ ምህንድስናን ትደግፋለች፡፡ የዘረመል ሕክምናን በመጠቀም በሽታን ለመከላከል እና ለመፈወስ ጥቅም ላይ ልውል እንደሚችል እንዲሁም አናቶሚካል እና የአእምሮ መዛባትን ለመከላከል እና ለመፈወስ እንደሚቻል እናውቃለን፡፡ በማህበረሰብ ውስጥ ኢ-ፍትሐዊነትን ለማስፈን፣ የሰዎችን ስብእና ለማርከስ ወይም የዘር፣ የአእምሮ ወይም የህብረተሰብ የበላይነተን ለመቀዳጀት የሚውል የዘረመላዊ ምንድስናን እንቃወማለን (ኢዩጄኔቲክ)፡፡ የሚወለደውል ልጅ ሕይወት ማቋረጥን እንደ አማራጭ በማቅረብ የሚያበረታታ ወይም የሚደገፍ የዘረህዋስጥ ጥንታ ጅማሬን እንቃወማለን፡፡ በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ ውስጥ ትህትና፣ ለሰው ልጆች ምትክ የሌለው ክብር፣ የሰው ልጆች በእግዚአብሔር ፍት ያላቸው እኩልነት እና ለርህራሄ እና ፍትሕ መሰጠት የዘረመላዊ ምንድስና እና የዘረመል ሕክምና የሚመሩ ነገሮች ልሆኑ

ይገባል፡፡
(ሚክ 6፡8)
**በሴት ልጅ ማህጸን ውስጥ የሚደረግ ምርምር እና ሌሎች ሕክምናዊ/ ጽንስ ከተፈጠረ በኂላ የሚደረጉ ማናቸውንም ሰውን ለማጥፋት የሚደረጉ ጥረቶች፡፡**
የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ሳይንሳዊ ጥናቶችን የሚደርጉ ሰዎች ከአዋቂዎች ጡንቻ ላይ፣ ፒላሴንታ፣ ከእትብት ደም፣ ከእንስሳት እና ከሌሎች ሰው ካልሆኑ እንስሳት ማህጸን በሚገኝ ስቲም ሴል ቴክኖሎጂ አማካኝነት የሚደረግ ይበልጥ ለማስፋፋት የሚደረግ ጥረትን ታበረታታለች፡፡ ይህ የሰው ልጅን ሕይወት ክቡርነት ሳይጋፉ ለብዙዎች ፈውስን ለማምጣት የሚደረግ የተቀደሰ ጥረት ነው፡፡ በሰው ልጆች ማህጸን ውስጥ ስለሚደረገው የስቲም ሴል ጥናታዊ ምርምር ላይ ያለን አቋም ምንጩ የሰው ልጅ ማህጸን በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው የሰው ልጅ መፈጠሪያ ቦታ መሆኑ ላይ ካለን የጸና እምነት ነው፡፡ ስለዚህ ከሰው ልጅ ማህጸን ተወስዶ ለማንኛውም ዓላማ የሚደረግ የስቲም ሴል ምርምርን እንቃወማለን፡፡
ለወደፊት የቴክኖሎጂ እድገት የተሻለ ነገር ስኖር የሰው ልጅን ሕይወት ክቡርነት ወይም ሌሎች ግብረገባዊ የሆኑ ነገሮችን ምርምሩ የማይጥስበት ሁኔታ የተፈጠረ እንደሆነ ያኔ እንዲህ ያሉ ምርምሮችን በአጽኖት እንደግፋለን፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ ማህጸን ለማንኛውም አላማ የሚያጠፋ ነገር እንቃወማለን እንዲሁ ልጅ ከተጸነሰ በኂላ የሚደርግ የሰው ልጅ ሕይወት የማጥፋት ህደትን እንቃወማለን፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ ከሰው ልጅ ማህጸን በሚወጣ ጽንስ የሚሠራ ማናቸውንም ነገር እንቃወማለን፡፡

**በላብራቶሪይ ሰውን መፍጠር፡፡** ግለሰቦችን በላብራቶሪይ የመፍጠር ሂደትን እንቃወማለን፡፡ የሰው ልጆች በእግዚአብሔር ዘንድ፣ በራሱ አምሳል በፈጠረን ፊት ከበረ ዋጋ አላቸው ነገር ግን የሰው ልጅን በላብራቶሪይ ውስጥ መፍጠር የሰው ልጆችን ቁሳቁስ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ ለሰው ልጆች በፈጣሪ የተሰጠውን የሰው ልጅ ስብእና እና ጠቃሚነት የሚቃወምነው፡፡
(ዘፍ 1፡27)

**ዩታናሲያ (ይህ በሕክምና የታገዘ ነፍስ ማጥፋትን ያካትታል)፡፡** በዩታናሲያ (በጣም የታመመ ሰው ወይም ለብዙ ጊዜ በሰመመን የቆየ ሰው እና በማይፈወስ በሽታ የታመመ ሰው የሚደርስበትን ስቃይ ለማቆም ሆን ተብሎ በሚደረግ ነፍስ ማጥፋት) ከክርስቲና እምነት ጋር የማይስማማ መሆኑን እናምናለን፡፡
**መ. ወሲብ**
37. የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ወሲብ እግዚአብሔር አምላክ ለፍጥረቱ ካቀዳቸው የቅድስና መገለጫዎች አንዱ እንደሆነ ታምናለች፡፡ ይህ በባልና ሚስት መካከል የሚደረገው ቃል ኪዳን ከሚታተምባውና ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡ ክርስቲያኖች በጋብቻ ውስጥ ወሲብ እግዚአብሔር የቀደሰው ተግባር መሆኑን መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ ወሲብ ተገቢውን ስፍራ ሊይዝ የሚችሉው ጥልቅ ፍቅርና እማኝነት የታከለበት እንሆነ ብቻ ነው፡፡ ክርስቲያን ባለትዳች ወሲብን ለእርስ በርሳቸው የሕይወት ትርጉም ምንጭ ለሆነው ክርስቶስ የገቡት ሰፊ ቃል ኪዳን አድርገው ሊመለከቱት ይገባል፡፡

ክርስቲያናዊ ቤተሰብ ልጆች ስለ ሰበአዊ የወሰብ ባህርይ ቅዱስነት የሚማሩበትና በፍቅር፣ ታማኝነትና ትዕግሥት ትርጉም እንዴት ምልዕ እንደሚሆን የሚረዱበት ዓውድ ሊሆን ይገባል፡፡

አገልጋዮቻችንና ክርስቲያን የትምህርት ባለሙያዎች ክርስቲያናዊ የወሲብ ግንዛቤ ሁቤታ የተቀቡ በፍጹም ይዘቱ ላይ እንዲያተኩሩ ማበረታታት ይኖርባቸዋል፡፡

ወሲብ በራሱ እንደ ግብ ከተወደሰ ወይም ብልሹ የሴሰኝነት ፍላጎቶችን ለማርካት ሲባል የትዳር ጓደኛ ክለሆነ ሰው ጋር ግንኙነት በመፈጸም ከረከሰ፣ ዓላማውን ይስታል፡፡ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ከሚፈጽሙት የጋብቻ ቃል ኪዳን ውጭ የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ወሲባዊ ግንኙነት እግዚአብሔር ለወሲብ ከወጠነው ቅድስናና ውበት የጎደለ ኃጢአት እንደሆነ እናምናለን፡፡

ወሲብን ከሚያረክሱት ነገሮች አንዱ ግብረ ሰዶማዊነት ነው፡፡ ወደ ግብረሰዶማዊነት የሚያመራውን ሁኔታ ብንገነዘብም፣ እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ኃጢአትና የእግዚአብሐየር ቁጣ እንደሚያስከትል የሚያስራውን የመጽሐፍ ቅዱስን አቋም እንይዛለን፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ ግብረሰዶማዊነትን ለማሸነፍ ብቁ እንደሆነ እናምናለን (1ቆሮ 6:9-11)፡፡ ክርስቶያናዊ ሥነ- ምግባራዊነትን ከንግረሰዶማዊነት ጋር የሚያጣጥመውን የትኛውን ዓይነት አሳብ ወይም ተግባር አንደግፍም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ወሲብ የሚናገረውን መመዘኛ በግልጽ ማስተማርና መስበክ አስፈላጊ መሆኑን እናምናለን፡፡

(ዘፍ 1:27፤ 19:1-25፤ዘለ 20:13፤ ሮሜ 1:26-27፤ 1ኛ ቆሮ 6:9-11፤ 1ጢሞ 1:8-10)

***ሠ. ክርስቲያናዊ መጋቢነት***

38. ***የመጋቢነት ፍች፡፡*** *መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉም ሰዎችና ሁሉም ነገሮች የእግዚአብሔት መሆናቸውም ያስተማራል፡፡ ስለሆነም፣ እኛም በሕይወትም ሆነ በንብረት ረገድ የእግዚአብሔር የንብረት አስተዳዳሪዎችን ነን፡፡ ስለ መጋቢነት ተግባራችን ለእግዚአብሔር መልስ የምንሰጥ መሆናችንን መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚናገር፣ የእግዚአብሔርን ባለቤትነትና የራሳችንን መጋቢነት አጥርተን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ እግዚአብሔር በመንገዶቹ ሁሉ የሥርዓትና የአገባብ አምላክ ስለሆነ፣ የርሱ ባለቤትነትና የሰዎችን መጋቢነት የሚያስረዳ የመስጠት ሥርዓት መሥርቷል፡፡ ይህንንም ትግባራዊ ለማድረግ ልጆቹ በሙሉ አሥራታቸውን ሊከፍሉና ለወንጌሉ መስፋፋት የሚያግዙ መጽዋቶች ሊሰጡ ይገባል፡፡* (140)

(ሚል 3:9-12፤ ማቴ 6:24-34፤ ማር 10:17-31፤ ሉቃስ 12:13-24፣ 19:11-27፤ ዮሐ 15: 1-17፤ ሮሜ 12:1-13፤ 1ቆሮ 9:7-14፤ 2ቆሮ 8:1-15፤ ዕብ 7:8፤ ያዕ 1:27፤ 1ዮሐ 3:16-18)

38.1. ***አሥራ መስጠት፡*** *ይህ አንድ ክርስቲያን አባል ለሆነባት ቤተ ክርስቲያን በመደበኝነትና በዋነኝነት ገንዘብ የሚሰጥበት*

መጽሐፍ ቅዱሳዊና ተግባራዊ መንገድ ነው፡፡ ስለሆነም፣ የቤ ክርስቲያ የገንዘብ ዕቅድ በአሥራት ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ የናዛሪን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የአሥራት መዝገብ እንሆነች ምእመኖቿ ሁሉ ሉገነዘቡ ይችላሉ፡፡ የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ሁሉ ከገቢያቸው አንድ አሥረኛውን በታማኝነት መክፈልና በተጨማሮም እግዚአብሔት ባበለጸጋቸው መጠንለጠቅላላይቱ ቤተ ክርስቲያን፣ ለአጥቢያ፣ ለቀጠናና ለአጠቃላይ ተግባራት ምጽዋት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

38.2. **ገንዘብን መሰብሰብና ማከፋፈል፡፡** ለቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ግንባታና ለወንጌል ስርጭት አሥራትና መባ ስለ መሰብሰብ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው አንጻር፣ የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ከእነዚህ መርሆች ካፈነገጠ፣ የወንጌሉን መልእክት ከሚያደናቅፍ፣ የቤተ ክርስቲያንን ስም ከሚያስነቅፍ፣ ድሆችን ከሚያገል ወይም ሰዎች ወንጌሉን የሚያስፋፉበት ጉልበት ወደተሳሳተ አቅጣጫ ከሚመራ ተግባር ጋር መተባበር አይኖርበትም፡፡

የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን የአጥቢያ፣ የቀጠና፣ የትምህርትና የናዛሪን ቤተ ክርስቲያንን አጠቃላይ ፕሮግራሞች ለማስፈጸም አጥቢያ አብያተክርስቲያናት ለአጠቃላይ፣ ለትምህርትና ለቀጠና በየወሩ ገንዘብ ማዋጣት ይኖርባቸዋል ፡፡ (130፣ 154፣ 155፣ 55.2፣ 413.21)

38.3. **የአገልግሎት ድጋፍ፡፡** ‹‹እንዲሁ ደግሞ ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲቀበሉ ጌታ ደንግጎአል፡፡›› (1ቆሮ 9፡14) ቤተ ክርስቲያቱ በእግዚአብሔር የተተጠሩትንና በቤተ ክርስያኒቱ ምሪት ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለአገልግሎት የሰጡትን አገልጋዮች የመደገፍ ግዴታ አለባት፡፡ ስለሆነም፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ ምእመናን ለዚህ የተቀደሰ ተግባር በየሳምንቱ ገንዘብ በበማሰባሰብ የመጋቢያንን ደሞዝ እንዲከፍሉ እንጠይቃለን፡፡ (115.4)

38.4. **ስጦታዎች፡፡** እግዚአብሔር በዚህ ሕይወት አደራ የሰጠንን ንብረትና ገቢ እንዴት ማስተናገድ እንዳለብን መረዳቱ ጠቃሚ ነው፡፡ ሕዝባዊ ህግጋት ሀብት እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ መከፋፈል እንዳለበት አይደነግጉም፡፡ እያንዳንዱ ክርስቲያን የመጨረሻ ኑዛዜን በሚገባ አስቦበት ሊሰጥ ይገባል፡፡ የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን በአጥቢያ፣ ቀጠና፣ ክልልና አጠቃላይ መልኩ ለሚታካሂዳቸው እንደ ሚሲዮናዊነት፣ የወንጌል ስርጭት እንዲህ ዓይት ኑዛዜዎች ቢደረጉላት መልካም ነው፡፡

38.5. **ማከፋፈል፡፡** የናዝሬን ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በውክልና ነው፡፡ እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በጠቅላላ ጉባኤ በተወሰነውና በጠቅላላ ኃለፊዎች መሪነት በዓለም አቀፍ የወንጌል ስርጭት፣ ትምህርት፣ የአገልግሎ እገዛና ቀጠና አገልግሎቶች በሚተገበረው መሠረት አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያኒቱን ተልእኮ የሚደግፉ ይደግፋሉ፡፡

የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ፣ ከአጠቃላይ ቦርድ ጋር በመሆን የዓለም አቀፍ የወንጌል ስርጭት ልገሳ ለተለያዩ ቀጠናዎች እንድከፋፈል ያደርጋሉ፡፡ (317.2)

በቤተ ክርስቲያኒቱ መመሪያ አንቀጽ 337.1 መሠረት ብሔራዊ ቦርዶች እና/ወይም ክልላዊ አማካር ካውንስሎች በአከባቢያቸው የጡረታ እቅድ እንዲያወጡ ፍቃድ እና ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ እንዲህ ያለውን እቅድ የማሳወቅያ መንገድ በቤተ ክርስቲያኒቱ መመሪያ አንቀጽ 337.2 ላይ ተገልጸዋል፡፡ አንቀጽ 38.5 ከቦርድነት ለለቀቁ እና በዩኤስኤ ውስጥ ያሉትን አይመለከትም፡፡

ብሔራዊ ቦርድ እና/ወይም አከባቢ አማካሪ ካውንስሎች በአከባቢያቸው ያሉትን ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መደገፍ እንዲችሉ ፍቃድ እና ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ (344፣ 345.3)

እያንዳንዱ ቀጠና በቀጠናው ውስጥ ለሚካሄዱትን አገልግሎቶች በቀጠና የገንዘብ ኮሚቴ አማካኝነት ገንዘብ ማከፋፈል እንዲችል ስልጣን እና ፍቃድ ተሰጥቶታል፡፡ (235.1)

**ረ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች**

39. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖቻችን በሁለንተናዊ ቅድስና የሚያምኑትንና ጸጋ ምስክሮች የሚሆኑትን ሰዎች ብቻ ለመሪነት እንዲመጧቸው እንጠይቃለን፡፡ እነዚህ ለመሪነት የሚመረጡት ሰዎች ከናዝሬን ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ፣ ደንብና ልምምድ ጋር የሚስማሙ፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን በአምልኮ፣ በአሥራትና በምጽዋት የሚደግፉዋት መሆን ይኖርባቸዋል (113.11፣ 127፣ 145-147)

**ሰ. የሥርዓት ደንቦች**

40. በሀገርቱ ውስጥ በሚተገበሩ ሕጎች፣ በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በሚገኙ አንቀጾች፣ ስብሰባዎችና የናዝሬን ቤተ ክርስቲያን የአጥቢያ፣ የቀጠና ምእመናን ተግባራት የሚዳኙበት በሮበርት (አዲሱ እትም) የፓርላሜንት ደንቦች መሠረት ነው፡፡ (113፣ 203፣ 300.3)

**ሸ. የክርስቲያናዊ ባሕርይ ቃል ኪዳን ማሻሻያ**

41. የክርስቲያን ባሕርይ ቃል ኪዳን ሊሰረዝ ወይም ሊሻሻል የሚችለው በጠቅላላ ጉባኤ ላይ ከተገኙት ተሳታፊዎች የሁለት ሦስተኛውን ድጋፍ ከገኘ ነው፡፡

## የቤተ ክርስቲያና አወቃቀር

ቤተ ክርስቲያን ማዋቀርያ ሦስት መንገዶች አሉ፡

1. አንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት መሪዎቻቸው በጣም ብዙ ስልጣን አላቸው፡፡
2. ሌሎች ደግሞ ለማህበረ ምእመኑ በጣም ብዙ ስልጣን ይሰጣሉ፡፡ በእንዲህ ያለው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ስልጣን ያለው መሪ ወይም ግለሰብ አይኖርም፡፡ ከዚያ ይልቅ መሪነቱን የሚይዙት ከጉባኤው የተመረጡ ሽማግሌዎች ናቸው፡፡
3. የውክልና አስተዳደራዊ መዋቅን በሚከተሉት ዘንድ ሥልጣን በአገልጋዮችና በማህበረ ምእመኑ ይጋሩታል፡፡

የናዛሬን ቤተ ክርስቲያን የሚትከተለው የአደረጃጀት የውክልና አስተዳደራዊ መንገድን ነው፡፡ በዚህም መጋውና የቤተ ክርስቲያንቷ ቦርድ ቤተ ክርስያኗን በመምራትና በማስተዳደር ረገድ ስልጣን ይጋራሉ፡፡

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ተልዕኮአቸውን እና ዒላማቸውን በአግባቡ እንድወጡ የሚቆጣጥ የቀጠና መሪ መኖር እንዳለበት እናምናለን፡፡ የቀጠና መሪው የሥራ ድርሻ ሙሉ በሙሉ የተደራጀች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጣልቃ መግባን አይፈቅድለትም፡፡ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የራሱን መጋቢ የመምረጥ፣ ያለውን መዋዕለ ነዋይ የማስተዳደር እንዲሁም ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ነገሮች የመፈጸም ሙሉ መብት አለው፡፡ (28-28.2)

## የናዛሬን ቤተ ክርስቲያን አወቃቀርና አስተዳደር

የናዛሬን ቤተ ክርስቲያን ጀማሪ በሆኑትና የሜቶዲስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለረጅም ዓመታት አገልጋይ በሆኑት ዶ/ር ብሬስ ነው የተመሠረተችው፡፡ እርሱም ቤተ ክርስቲያን የሚያበረታታትና የሚቆጣጠራት መሪ እንደሚያስልጋት ያስባል፡፡ ጳጳስ የሚለውን ቃል አይጠቀምም ነበር ነገር ግን እነዚህም መሪዎች የቀጠና ኃላፊዎች ብሎ ጠራቸው ነበር፡፡ የቀጠና ኃላፊ የቡድን አስተባባር ወይም በስፖርት ሜዳ ውስጥ ተጫዋቾቹን የሚያበረታታ አሰልጣኝ እንደሆነ ልትቆጥሩ ትችላላችሁ፡፡

በምስራቃዊ የአሜርካ ግዛት ውስጥ ክርስቲያኖች የቅድስና ሕይወት እንደሚያስፈልጋቸው የሚያምኑ ቤተ ክርስቲያናት ይኖሩ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጳጳሳት በአጥያ ቤተ ክርስቲያናት ጉዳይ ላይ ከሚገባው በላይ ጣልቀ እንደሚገቡ ይሰማቸው ነበር፡፡ ስለዚህም የአጥቢያ ቤ ክርስቲያንን ጉዳይ የሚያስተናግድ ሙሉ ስልጣልን ያለው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቦርድ እንደሚያስፈልግ አጽኖት ሰጡ፡፡

ሁለት ቡድኖች በአንድነት በመጣመር የናዛሬን ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት ስስማሙ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አመራሪ ሀሳቦችን ለማጣመር ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን የሚያበረታታ፣ ምክር የሚሰጥ እና የሚመራ የቀጠና አስፈላጊ እንደሆነ ተስማምተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማር የአጥያ ቤተ ክርስቲያናት የራሳቸውን መጋቢ የመምረጥ እና አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ሁሉ መከናወን እንድችሉ ተስማምተዋል፡፡ መጋቢውነ ከአጥቢያ

ቤተ ክርስቲያን ቦርድ ጋር በመስማማት መስራት ይኖርበታ።

በቀጠና ደረጃ የቀጠና ኃላፊው አጥያ ቤተ ክርስቲያናትን አቅጣጫ ለመስጠት እና ለመማራት ከቀጠና መማክር ቦርድ ጋር አብሮ ይሠራል። በዓለም አቀፍ ደረጃ አጠቃላይ ኃላፊው ቤተ ክርስያኒቱን ለመምራት ከአጠቃለይ ቦርድ ጋር ይሠራል። በናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሦስት ዓይነት አስተዳደራዊ ደረጃዎች አሉ። እርሱም፡-

1. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን
2. የቀጠና ጉባኤ
3. አጠቃላይ ጉባኤ

አጠቃለይ ቤተ ክርስቲያኗ እንዴት ሥራዋን እንደሚታከናውን ለመረዳት የእያንዳንዱ ደረጃ ሥራ ምን እንደሆነ መረዳት አስፈላጊ ነው።

**አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን**

በናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጅግ ወሳኝ ምና ያለው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነው። ሰዎች ለማምለክ የሚመጡት፣ አዳዲስ ሰዎች ክርስቲያን የሚሆኑበት እና በክርስትና ሕይወታቸው የሚያድጉት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያ ውስጥ ነው። ሰዎች የቤተ ክርስቲያን አባል የሚሆኑበት በዚህ ሥፍራ ነው።

**የቤተ ክርስቲያን አባልነት** (107-110)

አንድ ሰው የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን አራት ነገሮች ማድረግ አለበት:

1. ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ መቀበሉን መመስከር አለበት።
2. ከናዛሪን ቤተ ክርስቲያን እምነት ጋር መስማማት አለበት።
3. የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን መመሪያዎችን እና ደንቦችን ለማክበር ቃል መግባት አለበት።
4. ቤተ ክርስቲያንን በጉዜያቸው፣ በገንዘባቸው፣ በእውቀታቸው፣ በተሳትፎዋቸው ለማገዝ ቃል መግባ አለባቸው።

የቤተ ክርስቲያን አባል አምልኮን ከምካፈል ሰው በጣም የተለየ ነው፤ የቤተ ክርስያን አባል አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ተሳትፎ ለማድረግ እና በተቻለው አቅም ሁሉ ቤተ ክርስቲያኑን ለማገዝ በአደባባይ ቃል የገባ ሰው ነው።

የቤተ ክርስቲያን አባል እንዴት መሆን ይቻላል

1. የቤተ ክርስቲያን አባል መሆን የሚፈልጉ ሰዎች ኢየሱ አዳኝ መሆኑን ማወቅ አለባቸው።
2. የቤተ ክርስቲያኗን አስተምህሮወች የሚያብራራ ትምህርት መማር ይጠበቅባቸዋል።
3. የቤተ ክርስቲያኗን ደንብ እና ክርስቲያናዊ አኗኗር ምን እንደሚመስል

የሚገገልጽ ትምህርት መማር ይጠበቅባቸዋል።

የቤተ ክርስቲያንቷ የወንጌል ስርጭት እና የአባልነት ኮሚቴ የቤተ ክርስቲያኗ አባል ለመሆን የሚፈልጉ ሰዎችን ቃለመጠይቅ ልያድርጉላቸው ይገባል። በቃለመጠይቅ መሠረት ተቀባይነት ካገኙ በመጋቢው አማካኝነት በጉባኤ ፊት የቤተ ክርስቲያንቱ አባላት እንደሆኑ ይገለጻል።

**የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ (113)**

የቤተ ክርስቲያ ስበሰባ የሚባለው የቤተ ክርስቲያኗ አባለት የአጥቢያ ቤተክርስቲያናቸውን ሁኔታ፣ እድገት እማ አስተዳደረዋዊ ሁኔታ ላይ ለመወያየት ኦፌሴላዊ ስብሰባ የሚያድርበት ነው።

መጋቢው ሰብሳቢ ይሆናል።

የቤተ ክርስቲያኒቱ ቦርድ ፀሐፊ የቤተ ክርስቲያኒቱ ስብሰባ ፀሐፊ ይሆናል። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዓመታዊ ስብሰባ ከቀጠና ስብሰባ ከሚደረግበት ሦስት ወራት በፊት መደረግ አለበት።

**የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ የሥራ ድርሻዎች**

የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ሁለት ሥራዎች አሉት:

1. ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖር መስማት
2. ምርጫችን ማከናወን

የቤተ ክርስቲያን ዓመታዊ ጉባኤ እነዚህ ሪፖርቶች ይሰማል:

1. መጋቢ (413.15)
2. ናሚዓ ፕሬዜዳንት (153.2)
3. ናወዓ ቴሬዜዳንት (151.4)
4. የሴቶች ህብረት ፕሬዜዳን
5. የወንዶች ህብረት ፕሬዜዳንት
6. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ፈቃድ ካላቸው አገልጋዮች (428.1)
7. ከቦርድ ፀሐፊ (135. 2)
8. ከገንዘብ ያዥ (136.5)
9. ከሰንበት ትምህርት እና የደቀመዝሙርነት አገልግሎት ክፍል ኃላፊ (146.6)

በአመታዊው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ላይ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መመረጥ አለባቸው:

1. ባለአደራዎች (137)
2. ገንዘብ ያዥ (141,142.1)

3. የሰንበት ትምህርት እና የደቀመዝሙርነት አገልግሎት ክፍል ኃላፊ (146)

4. የሰንበት ትምህርት አገልግሎት ቦርድ (145)

5. የሴቶች አገልግሎት ፕሬዜዳንት

6. የወንዶች አገልግሎት ፕሬዜዳንት

**የመጋቢው የሥራ ኃላፊነት**

አንድ መጋቢ የተቀባ ሽማግሌ ወይም የቀጠና የአገልግሎት ፈቃድ ያለው ልሆን ይገባል። መጋቢው የእግዚአብሔር ቃል ለመስበክ እና ሰዎችን ለመንከባከብ የተጠራ መሆንን ማወቅ አለበት፡፤ መጋቢ በጣም ብዙ የሚሠራው ሥራ አለ። ይህ በቤተ ክርስቲያኗ መመሪያ (412-420) ላይ ተገልጾዋል። አጠቃላይ የመጋቢው ተግባራት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡

1. **መስበክና የአምልኮ ስርዓቶችን ማስፈጸም**
   - መስበክ
   - ማጥመቅ፣ የጌታ እራት መስጠት፣ ማጋባት እና የቀብር ስነ-ሥርዓት ማስፈጽም ናቸው
   - የቤተ ክርስቲያንቷን የወንጌል ስርጭቶች ፕሮግራሞችን በበላይነት መምራት

2. **የቤተ ክርስቲያኒቱን አባላት መንከባከብ**
   - አባላቱን መጎብኘት
   - የታመሙትንና ድሆችን መጎብኘት
   - ያዘኑትን ማጽናናት
   - ሰዎች የክርስትና ሕይወትን እንድኖሩ ማበረታታት
   - ኃጢአተኞች ኃጢአታቸውን ተናዘው ደወ እግዚአብሔርእንድመለሱ ማበረታታት።
   - ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ እንድሞሉ እና ቅድስና የተሞላበት ሕይወት እንድኖሩ መርዳት
   - ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ላይ ባላቸው እምነት እንድጠነክሩ ማስተማር

3. **የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ሥራ ማስተባበር**
   - ሰዎችን በአባልነት መቀበል.
   - የቤተ ክርስቲያንቷን የተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎችን መቆጣጠር
   - ለአመታዊ የቤተ ክርስያኒቱ ጉባኤ እና ለቀጠና ጉባኤ ሪፖርት ማዘጋጀት

**የመጋቢነት ጥሪ (115-123)**

115. የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ወይም የአገልግሎት ፈቃድ የተሰጠው አማኝ (412) በዓመታዊ ወይም ልዩ ስብሰባ ላይ ከተገኙና ድምፅ ለመስጠት በሚያስችል ዕድሜ ውስጥ ከሚገኙ አበባላት የሁለት ሦስተኛውን ድጋፍ ካገኘ ቤተ ክርስቲያንን በመጋቢነት እንዲያገለግል ሊጠራ ይችላል፡፡ ሀም የሚሆነው ሽመግሌው ወይም ፈቃድ የተሰጠው አገልጋይ የቤተ ክርስቲያን ቦርድ ከቀጠና ኃላፊው ጋር ከተማከረ በኋላ ከአባላቱ የሁለት ሦስተኛውን ድጋፍ አግኝቶ ለቤተ ክርስቲያን በእጩነት ከቀረበው፣ እንዲሁም በእጩነት በቀጠና ኃላፊ ፀደቀ እንደሆነ ነው፡፡ የቀጠና የመማክርት ቦርድ ካላፀደቀው የቤተ ክርስቲኒቱ አባል ለመጋቢነት አይመረጥም፡፡ ይህ የመጋቢነት ጥሪ በየጊዜው የሚገመገምና በሚከተለው መንገድ የሚፈጸም ይሆናል፡፡ (119፣ 122-24፣ 129.2፣ 160.8፣ 208.10፣ 222.12)

115.1. አገልጋዩ የመጋቢነት ጥሪውን ከተመረጠበት ጊዜ አንሥቶ በ15 ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለበት፡፡

115.2. የቤተ ክርስቲያን ቦርድና መጋቢው ዓላማዎቻቸውንና ለማከናወን የሚፈልጓቸውን ነገሮች በጽሑፍ መለዋወጥ አለባቸው፡፡

115.3 መጋቢው ማገልገል እንደጀመረ፣ መጋቢውና ማህበረ ምእመኑ የጥምረት ፕሮግራም ማካሄድ ይኖርባቸዋል፡፡ የዚህ ፕሮግራም ዓላማ የእግዚአብሔር ፈቃድ አስመልክቶ የአንድነትና የምሪት በዓል ማክበር ሊሆን ይገባል፡፡ ከተቻለ፣ ፕሮግራሙን የቀጠና ኃላፊ ይመራዋል፡፡

115.4. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጥሪዋን ካስተላለፈች በኋላ የመጋቢውን ደመወዝ ትወስናለች፡፡ የደመወዙ መጠን በቤተ ክርስቲያን ቦርድ፣ ወይም የቤተ ክርስቲያን ቦር በሚሰጠው ድጋፍ የቤተ ክርስቲያን አባላት በሚሰጡት ድምፅ ሊወሰን ይችላል፡፡ ቤተክርስቲያን ወይም የቤተ ክርስቲያን ቦርድና መጋቢው በደመወዝ መጠን ላይ ከተስማሙ በኋላ፣ ቤተ ክርስቲያን ደመወዙን ሙሉ በሙሉ መክፈል ከማትችልበት ደረጃ ላ ከደረሰች፣ መጋቢው ይህንን ችግር ለወንጀል እንደሚበቃ ምክንያት ሊመለከተው አይገባም፡፡ እንዲሁም፣ በስምምነቱ ውስጥ እስካልተጠቀሰ ድረስ ቤተ ክርስቲያን በመጋቢው የአገልግሎት ዘመን ለተገኘው ገቢ ህጋዊ ተጠያቂነት አይኖራትም፡፡

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለመጋው የጉዞና የእንቅስቃሴ ወጭዎችን መሸፈን አለባት፡፡ (38-38.3፣ 129.8-29.9)

116. አጥቢያ ቤተ ክርቲያናት የወሊድ ወይም የወላጅነት ፍቃድ ለመጋቢዎችና ለረዳቶቻቸው ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ የቀጠና ኃላፊዎች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን የወሊድ/የወላጅነት ፍቃድ ፖሊስን እንዲኖራቸው ማበረታታት አለባቸው፡፡

117. አምስት ዓመት ላልሞላት፣ ወይም ቀደም ሲል በተካሄደው ዓመታዊ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ላይ ከ35 የሚያንሱ አባላት ድምፅ ለሰጠቡባት፣ ወይም በመደበኛነት ከቀጠና በሚመጣ ገንዘብ ለምትደጎም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በቀጠና የመማክርት ቦርድ ስምምነት የቀጠናው ኃላፊ መጋቢን ሊሾሚላት ይችላል፡፡ (208.17)

117.1. ቤተ ክርስቲያኒቱ ከ35 በላይ ድምፅ መስጠት የሚችሉ አባላት ስኖሯት ወይም ቢያንስ ለአምስት ዓመታት ተደራጅታ የቆጠች ከሆነች እንዲሁም

መጋቢያቸው ቢያንስ ለሁለት ዓመታት መጋቢያቸው ሆኖ ያገለገለ ከሆነ ከጋቢውን ‹‹ከተሸዋምነት ደረጃ›› የማንሳት ሂደት ልጀምር ይችላል፡፡ እንዲህ ያለው ሂደት የቤተ ክርስቲያን/የመጋቢ ግምገማን፣ ያሉትን የቤተ ክርስቲያን የቦርድ አባላትን የአብላጫ ድንፅ፣ የቀጠና ኃላፊውን ፍቀድ እና የቀጠና መማክርት ቦርድ ፍቃድን ልያካትት ይችላል፡፡ በየአራት ዓመቱ የቤተ ክርስቲያን/የመጋቢ ግምገማ ማድረግ የመጨረሻው ፍቅድ መስጫ ቀን ነው፡፡

118. መጋቢውን በመሾሙ ረገድ በቤተ ክርስቲያን ቦርድና በቀጠናው ኃላፊ መካከል አለመግባባት ከተከሰተ፣ የቤተ ክርስቲያን ቦርድ ወይም የቀጠና ኃላፊ በሥልጣን ላይ ያለው ጠቅላላ ኃላፊ በጉዳዮ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ሊጠየቅ ይችላል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ቦርድ ወይም የቀጣና ኃላፊውበተሰጠው ውሳኔ ካልረካ ለጠቅላላ ኃላፊ አቤቱታተውን ማቅረብ ይችላል፡፡ እነዙህ ሁሉ በሥልጣን ላይ ላለው ጠቅላላ ኃላፊም ሆነ ለጠቅላላ ኃለፊዎች ቦርድ የሚቀርቡ ማመልከቻቸዎች፣ ተቃውሞዎች ወይም ክርክሮቸ፣ የሁዳዮ ተሳታፊ ለሆኑት አካላት ሁሉ መላክ አለባቸው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ቦርድ ቃለ ጉባኤ የማመልከቻውን ውጤት፣ የተካሄዱትን ክርክሮች፣ እንዲሁም የተሰጠውን ድምፅ ማካተት አለበት፡፡ ለክርክሩ መንስዔ የሆነው አገልጋይ ራሱን ከጉዳዩ ካገለለ ወይም ለምርመራ የማይገኝ ከሆነ፣ ክርክሩ በፍጥነት ተቋርጦ የቀጠና ኃለላፊና የቤተ ክርስቲያን ቦርድ ለቤተ ክርስያኒቱ ሌላ መጋቢ በመሾሙ ጉዳይ ላይ ይነጋገራሉ፡፡

119. ፈቃድ የተሰጠው አገልጋይ መጋቢ ፈቃዱ ካልታደሰለት ከቀጠና ጉባኤ በኂላ አገልግሎቱ ያበቃል፡፡

120. ማንኛውም መጋቢ ለቤተ ክርስቲያን ቦርድና ለቀጠና ኃላፊ ቢያንስ ከ30 ቀናት ቀደም ብሎ በጽሑፍ ሳያሳውቅና ጥያቄውም በቤተ ክርስቲያን ቦርድ ተቀባይነት ማግኘቱንና በቀጠና ኃላፊ የጽሑፍ ምላሽ መጽደቁን ሳያረጋግጥ አገልግሎቱን ማቋረጥ አይችልም፡፡ የአገልግሎቱ መቋረጥ ተቀባይነት ካገኘ በኂላ በ30 ቀናት ውስጥ በየትኛውም ቀን በስምምነቱ መሠረት መጋቢው አገልግሎቱን ሊያቆም ይችላል፡፡

120.1. አገልግሎቱን የሚያቋርጠው መጋቢ ከቤተ ክርስቲያን የቦርድ ጸሐፊ ጋር በመሆን የቤተ ክርስቲያን አባላትን መዝገብ አድርሻቸውን ጨምሮ ያዘጋጃል፡፡ ይህ መዝገብ ለመጨረሻ ጊዜ ከታተሙት የቀጠና ቃለ ጉባኤዎች ጋር በቁጥር ሊጣጣም፣ በዚሁ ዓመት የተጨመሩትንና የተቀነሱትን አባላት በግልጽ ሊያሳይ ይገባል፡፡

121. በቤተ ክርስቲያን ቦርድ ጥቆማ መሠረትና በቀጠና ኃላፊው ፍቃድ ምእመኑ ተባባር መጋቢን ልመርጥ ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ ስከሰት እነዚህ ሕግጋቶች ተግባራዊ ይሆናሉ፡

1. ተባባሪ መጋቢው በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ልዩ እቅድ ለማዘጋጀትም ሆነ የሥራና የሥልጣን ክፍፍል ለማድረግ ከቤተ ክርስቲያን ቦርድ ጋር፣ በቀጠናው ኃላፊ አቅጣጫ ጠቋምነት ተባብሮ መሥራት አለበት፡፡

2. ምንም እንኳ የመጋቢነት ቢሮን በተመለከተ ተባባሪ መጋቢው እኩል ቢሆንም ከቤተ ክርስቲያን ቦርድ መካከል አንድ ሰው የድርጅቱ ተወካይና የቤተ ክርስቲያን ቦርድ ዋነ ጸሐፊ ሆኖ እንዲያገለግል መመደብ አለበት።

3. የመጋቢው ግምገማ በቤተ ክርስቲያኒቱ መምሪያ አንቀጽ 123 ላይ በተጠቀሰው መሠረት መከናወን አለበት።

**የመጋቢ የሥራ መልቀቂያ የማስገባት አካሄድ** (120)

ማንኛውም መጋቢ ለቤተ ክርስቲያን ቦርድና ለቀጠና ኃላፊ ቢያንስ ከ30 ቀናት ቀደም ብሎ በጽሑፍ ሳያሳውቅና ጥያቄውም በቤተ ክርስቲያን ቦርድ ተቀባይነት ማግኘቱንና በቀጠና ኃላፊ የጽሑፍ ምላሽ መጽደቁን ሳያረጋግጥ አገልግሎቱን ማቋረጥ አይችልም። የአገልግሎቱ መቋረጥ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ በ30 ቀናት ውስጥ በየትኛውም ቀን በስምምነቱ መሠረት መጋቢው አገልግሎቱን ሊያቆም ይችላል።

አገልግሎቱን የሚያቋርጠው መጋቢ ከቤተ ክርስቲያን የቦርድ ጸሐፊ ጋር በመሆን የቤተ ክርስቲያን አባላትን መዝገብ አድርሻቸውን ጨምሮ ያዘጋጃል። ይህ መዝገብ ለመጨረሻ ጊዜ ከታተሙት የቀጠና ቃለ ጉባኤዎች ጋር በቁጥር ሊጣጣም፣ በዚሁ ዓመት የተጨመሩትንና የተቀነሱትን አባላት በግልጽ ሊያሳይ ይገባል።

**የቤተ ክርስቲያን/መጋቢ ግንኙነት** (122)

በየዓመቱ መጋቢውና የቤተ ክርስቲያን ቦርድ የቤተ ክርስቲያንን ዓላማዎችና መፈጸም የሚገባቸውን ተግባራት የሚድሱ ዕቅዶችን በጋር መወጠን አለባቸው። በመጋውና በቤተ ክርስቲያን መካከል በጽሑፍ የሰፈሩ መግባባቶች፣ ዓላማዎች፣ ዕቅዶችና የተግባር መመዘኛዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ የተሻሻሉ መሄድ ይኖርባቸዋል።የቀጠና ኃላፊው በስብሰባው ላይ መገኘት እንድችል ለቀጠና ኃላፊው ስለስብሰባው አስቀድሞ ልነገረው ይገባል። የስበሰባው ዋና ዓላማ ለችግሩ እልባት ለማግኘት እና ልዩነቶችን ለማጥበብ እንዲሁም ፍቅር፣ እርስ በእርስ መቀባበል እና ይቅር የመባበል መንፈስ የሞላበት ልሆን ይገባዋል። (121)

**የቤተ ክርስቲያን./መጋቢ ግንኙነትን ማደስ** (123)

**መደበኛ የቤተ ክርስቲያን/መጋቢ ግምገማ**። የቤተ ክርስቲያን ቦርድ ከቀጠና ኃላፊው ወይም ከተሸመ አገልጋይ ወይም በቀጠና ኃላፊ ከተሾመ ምእመን ጋር በመሰባሰብ የቤተ ክርስቲያን/መጋቢ ግንኙነት መገምገም ይኖርበታል፡፤ ይህም ከመጋቢው አገልግሎት ሁለተኛው ዓመት ከሚከበርበት ቀን አንሥቶ በሚመጡት 60 ቀናት ውስጥና ከዚያ በኋላ በየአራት ዓመቱ የሚካሄድ ይሆናል። ከቤተ ክርስቲያን ቦርድ ጋር ለሚደረገው ስብሰባ የጊዜ ሠሌዳ ማውጣትና ስብሰባውን ማካሄድ የቀጠና ኃላፊ፣ ወይም የተሸመ አገልጋይ ወይም በቀጠና ኃላፊ የተሾመ ምእመን ኃላፊ ይሆናል። የዚህ ስብሰባ የጊዜ ሠለዱ የሚወጣው ከመጋቢው ጋር በመማከር ይሆናል። የግምገማ ስብሰባው በዝግ ጉባኤዎች መካሄድ አለበት።

የቤተ ክርስቲያን ቦርድና የቀጠና ኃላፊ ለመደበኛ የቤተ ክርስቲያን/መጋቢ ግምገማ ከመሰባሰባቸው ቀደም ብሎ በሚመጣው እሁድ ይህንኑ የቤተ ክርስቲያን የቦርድ ስብሰባ ዓላማ የሚገልጽ የቃልና/ወይ፣ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለምእመናን መተላለፍ አለበት።
በዚህ የግምገማ ስብሰባ ላይ የቤተ ክርስቲያን/መጋቢ ግንኙነቱን በመቀጠሉ ጥያቄ ላይ ውይይት መካሄድ አለበት። የዚህም ውይይት ዓላማ የቤተ ክርስቲያን ቦረድ መደበኛ ድምፅ መስጠት ሥነ-ሥርዓት ሳይካሄድ ከስምምነት ላይ መድረስ ነው። የቤተ ክርስቲያን ቦርድ የቤተ ክርስቲያን/መጋቢ ግንኙነት ይቀጥል ወይስ አይቀጥል? የሚለውን ጥያቄ ለአባላቱ ለማቅረብ ድምፅ ካልሰጠ፣ የቤተ ክርስያን/መጋቢ ግንኙነት ይቀጥላል።
የቤተ ክርስቲያን ቦረድ ጥያቄውን ለቤተ ክርስቲያን አባላት ለማቅረብ ድምፅ ሊሰጥ ይችላል። ውሳኔው የሚሰጠው በስብሰባው ላይ ከተገኙት አብዛኞቹ በሚስማሙበት መልኩ ይሆናል።
የቤተ ክርስቲያን ቦርድ ጥያቄውን ለቤተ ክርስቲያን አባላት ለማቅረብ ድምፅ ከሰጠ፣ ጉዳዩ ለዚሁ ተብሎ በተጠራው ስብሰባ ላይ በ30 ቀናት ውስጥ ለአባላት መቅረብ አለበት። ጥያቄው፣ ‹‹አሁን ያለው የቤተ ክርስቲያን/መጋቢ ግንኙነት ይቀጥል ወይ?›› የሚል ይሆናል። ለዚህ ጥያቄ የቤተ ክርስቲያን አባላት ድምፅ ሲሰጡና ሁለት ሦስተኛው እጅ ያገኘው ወገን በአብላጫ ድምፅ ሊያሸንፍ ይገባል። ከዚህ ውጭ የሚሆነው የአገሪቱ ሕ የሚደነግገው ደንብ ካለ ብቻ ተግባራዊ ይሆናል።
አባላቱ የቤተ ክርስቲያን/መጋቢ ግንኙነቲ እንዲቀጥል የሚያደርግ ድምፅ ከሰጡ፣ ግንኙነቱ የድምፅ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት እንዳልተካኄደ ሁሉ በመልካም ሁኔታ መቀጠል አለበት። ካልሆነ ግን የቤተ ክርስቲያን/መጋቢ ግንኙነቱ ድምፅ ከተሰጠበት ቀን አንሥቶ ከ30 በማያንሱና ከ180 በማይበልጡ ቀናት ውስጥ የቀጠና ኃላፊ በሚወስነው መሠረት ይቋረጣል። መጋው የድምፅ አሰጣጡን የማይፈልግ ከሆነ መልቀቂያ መጠየቅ አለበት፡፤ በዚህ ጊዜ፣ መጋቢው የምእመናንን ድምፅ እንደማይፈልግ ከተነገረበት ጊዜ አንሥቶ ከ30 እስከ 180 ባት ቀናት ውስጥ በቀጠና ኃላፊ ውሳኔ መሠረት የቤተ ክርስቲያን/መጋቢ ግንኙነት ይቋረጣል። የቤተ ክርስቲያኒቱ ተልዕኮ፣ ራዕይና አንኳር እሴቶችን አስመልክቶ መጋቢውና የቤተ ክርስቲያን ቦርድ ለቀጠና ኃላፊ ሪፖርት ያደርሉ። ይህ የመደበኛው ግምገማ አካል ነው።

123.1 የትኛውም ይፋዊ መግለጫ ከመሰጠቱ በፊት የድምፅ መዝጋቢዎች ቦርድ ሊቀመንር ስለተሰጠው ድምፅ ለመጋቢው ማሳወቅ አለበት።

**የቤተ ክርስቲያን ቦርድ (127)**

**እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቦርድ ልኖረው ይገባል። የቦር አባላቱም፡**

1. መጋቢው
2. የሰንበት ትምህርት ቤት እና የደቀ መዝሙርነት አገልግሎት

3. የናዛሪን ወጣቶች ዓለም ዓቀፍ
4. የናዛሪን ሚስኦን ዓለም አቀፍ
5. ባለአደራ እና ንብረት ክፍል ናቸው፡፡

**የመሰብሰቢያ ጊዜያት (128)**

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ስብሰባ ወር በገባ በአስራ አምስተኛው ቀን ልደረግ ይገባዋል፡፡

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ቦርድ የሥራ ድርሻ (129- 134)

129.1. በተለይ እስካልተጠቀሰ ድረስ ከመጋቢው ጋር ተስማምቶ የቤተ ክርስቲያነን ፍላጎቶችና ሥራ ማካሄድ፡፡ (158፣ 415)

129.2. የቀጠና ኃላፊ በሚያፀድቀው መሠረት መጋቢ ሊሆን የሚችል ሽማግሌ ዌም የአገልግሎት ፍቃድ የተሰጠው አገልጋይ ለቤተ ክርስቲያን በእጩነት ማቅረብ፡፡ (115፣ 160.8፣ 208.10፣ 222.12)

129.3. የዓላማና የአፈጻጸም መግለጫዎችን ከመጋቢው ጋር ማዘጋጀት (115.2)

129.4. ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ከመጋቢው ጋር በመሆን በልጽ የዓላማ፣ የአፈጻጸም፣ የዕቅድና ተጨባጭ የተግባር መመዘኛ አሳቦችን አሻሽሎ ለመጻፍ የሚያስችል የማቀጃ ክፍለ ጊዜ ማዘጋጀት፡፡ (122)

129.5. ቤተ ክርስቲያን መደበኛ የመጋቢ ትሪ እስክታደርግ ድረስ የቀጠና ኃላፊ በሚያፀድቀው መሠረት መጋቢን ለአገልግሎት ማቅረብ፡፡ (209፣ 422)

129.6. የቤተ ክርስያን ዓመታዊ በጀት፣ ድጋፍ ሰጭ አገልግሎቶች ኤንኤምኣ፣ ኤንዋይኣ፣ ኤስዲኤምኣ፣፣ የልጆች እንክብካቤ ገቢዎችና ወጪዎች ማዘጋጀት፡፡

129.7. ቦርዱ አንድ ኮሚቴ በማቋቋም ኮሚቴው የሚከተሉትን ተግባራ እንዲያከናውን ማድረግ፡፡ ሀ/ የቤተ ክርስያን በጀት እንዲቆጣጠር፣ ለ/ ስለ ቤተ ክርስቲያን የገንዘብ ጉዳዮችና አሳሳቢ ሁኔታዎች ለቦርዱ ሪፖርት ማድረግ፡፡

129.8. መጋቢው ሊያገኝ የሚገባውን የካሳ መጠን መወሰንና ይህንንም ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መከለስ፡፡ (115.4፣ 121)

129.9. መጋቢውን ለመደገፍ፣ የመጋቢነት አገልግሎትን ለመቀጠልና ለየትኞቹም ገንዘብ ለሚከፈላቸው የቤተ ክርስያን ሠራተኞች ተገቢውን ክፍያ ማሟላት የሚቻልባቸውም መንገዶች ማፈላለግ፡፡ በማቀድና በጀት በመመደብ የመጋቢውና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን የዕድሜ ልክ የመማር ጥረት መደገፍና ማበረታታት፡፡ (115.4)

129.10. የመጋቢውን ጤናማ የመጋቢነት አገልግሎትና የእድሜ ልክ መማርን ለማበረታታት የቤተ ክርስቲያን ቦርድ ከቀጠና ኃላፊው ጋር በመመካከር መጋቢው ለሰባት ተከታታይ ዓመታት በአንደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያገለገለ ከሆነ ከሰባት የአገልግሎት ዓመታት በኂላ ባለው ዓመት የእረፍት ዓመት ልሰጠው ይገባል፡፡ የእረፍት ጊዜው እና ርዝማኔው በመጋቢው፣ የቤተ ክርስቲያን ቦርድና በቀጠናው ኃላፊ መካከል በሚደረግ ውይይት የሚወሰን ይሆናል፡፡ የመጋቢው ደሞዝ ሙሉ ለሙሉ እንዲከፈለውና በእረፍት ዓመቱ ውስጥም የመድረክ አገልግሎት ልሰጠው እንደሚገባ በአጽኖት እንገልጣለን፡፡ ይህ ርዕሰ ጉዳይ በቀጠና ኃላፊው በቤተ ክርስቲያን/መጋቢው የግምገማ ሂደት ውስጥ የሚነሳና በስድስተኛው ዓመት በሁለት ወይም በሦስተኛው አመት የሚከሰት ነገር ነው፡፡ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ደረጃ የሰንበት እረፈትን የተመለከተ ነገርን ለመጀመር

እና በተግባር ለማዋል ፖሊስና መመሪያዎችን ለማዘጋጀት አስፈላጊዎቹ ቁሳቁሶች መዘጋቸት አለባቸው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ቦርድ እውቅና እንዲህ ያለው ፕሮግራም ከመጋቢው ጋር ለሚሠሩ ሠራተኞች ልዘጋጅ ይችላል፡፤
129.11. አንድ ወንጌላዊ ምን ያህል የገንዘብና ቤት ድጋፍ ማግኘት እንዳለበት መወሰንና ግለሰቡ በቤተ ክርስቲያን ቦርድ ተጠርቶ በሚቀርብበት ጊዜ ይህንኑ ማሳወቅ፡፡
129.12. መጋው ሀ/አጥቢያ አገልግሎት፣ ወይም ለ/ ምእመን አገልጋይነት እንዲሳተፍ ለሰጣቸው ሰዎች የአገልግሎት ፈቃድ መስጠት ወይም ማደስ፡፡ (402.3፣ 428.1፣ 428.3፣ 813.1)
129.13. ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አልፈው ለማገልገል ለሚሹና ቀደም ሲል በምእመን አገልጋይነትም ሆነ በተሹዋሚ አገልጋይነት ለቤተ ክርስቲያን ስላበረከቱት አስተዋጽኦ የድጋፍ ደብዳቤ ለሚጠይቁ ሰዎች፣ መምሪያው የድጋፍ ደብዳቤ እንዲቀርቡ የሚጠይቅ ከሆነ በመጋቢው መሪነት ለቀጠና ጉባኤ ይህንኑ ደብዳቤ መጻፍ፡፡
129.14. በመጋቢው ጥቆማ የአገልግሎት ብቃት ለማግኘት ወይም ለማሳደስ ለሚፈልግ ለማንኛውም ሰው ለቀጠና ጊባኤ የድገፋ ደብዳቤ መጻፍ፡፡ (428.5፣ 429.1)
129.15. በመጋቢው ጥቆማ የድቁና ፈቃዳቸውን ለማሳደስ ለሚፈልጉ ሰዎች ከአንቀጽ 406 ጋር በሚስማማ መልኩ ለቀጠና ጉባኤ የድጋፍ መጻፍ፡፡
129.16. የሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎቶችና የደቀመዝሙርነት አገልግሎት ዓለማቀፍ ቦርድ በሚያቀርበው ጥቆማና መጋቢው በሚያፀድቀው መሠረት የልጆች አገልግሎቶች ዳይሬክተርና የአዋቂዎች የአገልግሎቶች ዳይሬክተር መምረጥ፡፡ (145.6)
129.17. በናዛሪን ወያቶች ዓለማአቀፍ (ናወዓ) ቻርተር በተገለጸው መሠረት፣ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የናዛሪን ወጣቶች ዓለምአቀፍ ድርጅር የተካሄደው የናዛሪን ወጣቶች ኣለምአቀፍ ፕሬዚዳንት ምርጫ ማጽደቅ፡፡
129.18. የናዛሪን የልጆች ትምህርት ቤቶች ተንከባካቢዎችን አስተዳደር ምርጫ ማጽደቅ፡፡ (152፣ 160.1፣ 208.13፣ 414.10)
129.19. በመምሪያው አንቀጽ 39 ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቁ ስለሚሆኑ ምእመናን በተገለጸው መሠረት ከቤተ ክርስቲያን አባላት ፀሐፊን መምረጥ፡፡ ይህ የአዲሱ ቦርድ የመጀመሪያ ስብሰባ ላይ የሚመረጠው ፀሐፊ የቤተ ክርስቲያን ዓመት እስያበቃና ተተኪ ፀሐፊን እስኪመረጥ ድረስ የሚሠራ ይሆናል፡፡ (39፣ 113.6፣ 128፣ 135.1-35.7)
129.20. በመምሪያው አንቀጽ 39 ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቁ ስለሚሆኑ ምእመናን በተገለጸው መሠረት ከቤተ ክርስቲያን አባላት ገንዘብ ያዥ መምረጥ፡፡ ይህ የአዲሱ ቦርድ የመጀመሪያ ስብሰባ ላይ የሚመረጠው ገንዘብ ያዥ የቤተ ክርስቲያን ዓመት እስያበቃና ተተኪ ገንዘብ ያዥ እስኪመረጥ ድረስ የሚሠራ ይሆናል፡፡ የመጋቢው የቅርብ ዘመድ የሆነ ማንኛውም ሰው (ምስት፣ ልጆች፣ ወንድምና እህት፣ ወላጆች) ከቀጠናው ኃላፊ እና በቀጠና መማክርት ቦርድ ፍቃድ ሳያገኙ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ያዥ ሆነው ማገልገል አይችሉም፡፡ (128፣ 136.1-36.6)

129.21. በሳምንቱ ውስጥ የሚካሄዱትን የትምህርት ቤት ወጭዎችና የድጋፍ አገልግሎቶችን ጨምሮ፣ የቤተ ክርስቲያን ገቢና ወጪ በአግባቢ እንዲሠራ ማድረግና በመደበኛ ወርሃዊ ስብሰባዎቹ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ዓመታዊ ስብሰባ ላይ ሪፖርት ማቅረብ። (136.3-36.5)

129.22. የቤተ ክርስቲያንን ገቢዎች ሁሉ የሚቆጣጠርና ተገቢውን የሂሳብ አያያዝ የሚያከናውኑ ከሁለት ያላነሱ አባላት የሚገኙበትን ኮሚቴ ማዋቀር።

129.23. ሀገርቱ ሕግ የሚጠይቀውን መሥፈርት በትንሹ እንኳ ለሚሟላት ወይም ሌላ የሚጠይቀውን የባለሞያ መሥፈርትን ለሚሟላት ቢያንስ በዓት አንድ ጊዜ የቤተ ክርስቲያንን የገንዘብ ያዥ፣ የናዛሪን ወታቶችን ዓለም አቀፍ፣ የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎት ዓለም አቀፍ ቦርድ፣ የናዛሪን የልጆች ትምህርት ቤቶች እንክብካቤና ሌሎች ማናቸውንም የቤተ ክርስቲያን የሂሳብ መዝገቦች ኦዲት የሚያደረግ ኮሚቴ ለማቋቋም ወይም ከውጭ የሆነ አጣሪ ኮሚቴ ለማቋቋም ወይም ኦዲት ወይም ለማጣራት ብቃት ያላቸውን ሰዎችን መሾም አስፈላጊ ነው። መጋቢው የቤተ ክርስቲያን ማናቸው መዛግብቶች የመመልከት መብት አለው።

129.24. ከሦስት የማያንሱ አባላት የሚገኙበት የወንጌል ስርጭትና የቤተ ክርስቲያን አባልነት ኮሚቴ ማቋቋም። (110)

129.25። ከ75 የማይበልጡ አባላት በሚገኙበት አብያተክርስቲያናትበተገቢ የሚሆንበት ጊዜ የሰንበት ትምህርት አገልግሎቶችን ቦረድ ሚና መጫወት። (145)

129.26. በአንድ የቤተ ክርስቲያን አባል ላይ የጽሑፍ ክፍስ በሚቀርብበት ጊዜ የሚመረምር አምስት አባላት ያሉት ኮሚቴ ማቋቋም። (504)

129.27. ከቀጠና ኃላፊ የጽሑፍ ድጋፍ በሚሰጥበት ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን ገንዘብ የሚከፈላቸው ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን በመጋቢነት እንዲሠራ መምረጥ። (152፣ 160-60.1፣ 208.13)

129.28.በቀጠና ኃላፊው ዓመታዊ በጽሑፍ ድጋፍ በሚሰጥበት ጊዜ አከባቢያዊ ወይም ፈቃድ የተሰጠው አገልጋይ ደመወዝ ሳይከፈለው በረዳት መጋቢነት እንዲሠራ መምረጥ።

129.29. በመጋቢው ሊቀመንበርነት የሚመራ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የረዥም ጊዜ ዕቅድ የሚያወጣ ኮሚቴ ማቋቋ፣።

129.30. ግለሰቦች በቤተ ክርስቲያን የሥልጣን ደረጃቸው ላይ የሚያደርሱትን አደጋ የሚቀንስ ዕቅድ ማውጣትና መተግበር። የእያንዳንዱ አጥያ ቤተ ክርስያን ዕቅድ ያለችበትን ልዩ ሁኔታ ያገናዘበ ሊሆን ይገባዋል።

**የቤተ ክርስቲያን ፀሐፊ። የቤተ ክርስቲያን ቦርድ ፀሐፊ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል። (135)**

135.1. ሁሉንም የቤተ ክርስቲያንና የቤተ ክርስቲያን የቦርድ ስብሰባዎችን ቃለ ጉባኤዎችን በትክክል መጻፍና በታማኝነት መጠበቅ፣ ከቢሮው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ተግባራት ሁሉ ማከናወን። የቦርድ ስብሰባ ቃለ ጉባኤዎች ሁሉንም የቦርድ አባላት ስም የተገኙ ወይም ያልተኙ በሚል መጥስ አለበት። (120.1፣ 129.19)

135.2. በዓመታዊ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ላይ አባላትን ቁጥር ጨምሮ ስለ ዋና ዋና ተግባራት ሪፖርት ማቅረብ። (113.9)

135.3. ሕጋዊ ወረቀቶችን፣ ጽሑፎችን፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ሕጋዎ ሰነዶች፣ ስምምነቶች፣ የማጠቃለያ አሳቦች፣ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች፣ የብድር ሰነዶች፣ የቤተ ክርስቲያን ቦርድ ቃለ ጉባኤዎች የማህበረ ወረቀቶች እሳት ወይም አደጋ በማይደርስበት የአጥቢያ ቤተ ክርስያን ሕንጻ ውስጥ ወይም የሚቻል ሲሆን፣ አደጋ በማይደርስበት አከባቢያው ባንክ ወይም ተመሳሳይ ተቋማት ውስጥ መቀመጣቸውን ማረጋገጥ። ሁልጊዜም መጋቢውና የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ያዥ ወደነዚህ መረጃዎች መግባት የሚችሉ ሲሆን፣ ፀሐፊው የዚህን ንብረት እንክብካበ ለተተኪው ማስረከብ አለበት።

135.4. የሁሉም ዓመታዊና ልዩ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ፀሐፊ መሆን፣ የእንዲህ ዓይነት ዓታዊና ልዩ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎችን ቃለ ጉባኤዎችንና ሌሎች ወረቀቶችን መጠበቅ። (113.6)

135.5. መጋቢን ስለ መጥራትና የቤተ ክርስቲያን/መጋቢ ግንኙነት የተሰጠውን ድምፅ ውጤት ለቀጠና ኃላፊ በጽሑፍ መመስከር። እንዲህ ዓይነቱን ምስክርነት በድምፅ በተሰጠበት በአንድ ሳምንት ውስጥ መተላለግ አለበት።

135.6. አጥያ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ በማይኖራት ጊዜ ሁሉንም የቤተ ክርስቲያንና የቦርድ ሰብሰባዎችን ቃለ ጉባኤዎች ቅጂዎች ለቀጠና ኃላፊ መላክ።

135.7. በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የተለየ ድንጋጌ እስካልተሰጠው ድረስ፣ ከመጋቢው ጋር የንብረት፣ የባንክ ብድር፣ ጠባንክ ብድር ክፍያ፣ የውልና ሌሎችን ህጋዊ ሰነዶችን መፈረም። (102.3፣ 103-4.2)

**የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ያዥ።** የቤተ ክርስቲያን ቦርድ ገንዘብ ያዥ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው። (136)

136.1. የተለየ መግለጫ እስካልተሰጠ ድረስ ሁሉንም ገቢ መቀበልና በቤተ ክርስቲያን ቦርድ ትእዛዝ ብቻ መክፈል። (129.21)

136.2. የተለየ መግለጫ እስካልተሰጠ ድረስ ለቀጠና የተወሰነው ገንዘብ ለቀጠና ገንዘብ ያዥ፣ ለጠቅላላ የተወሰነውን ገንዘብ ለጠቅላላ ገንዘብ ያዥ ማስረከብ። (414.9)

136.3. ለተሰበሰበውና ለተከፈለው ገንዘብ ሁሉ ትክክለኛ የሂሳብ አያያዝ መጠቀም። (129.22)

136.4. ለቤተ ክርስቲያን ቦርደ ዝርዝር ወርሃዊ ሪፖርት ማቅረብ። (129.21)

136.5. ለዓመታዊ የቤተ ክርስቲያንን ስብሰባ ዓመታዊ የገንዘብ ሪፖርት ማቅረብ። (113.9፣ 129.21)

136.6. ገንዘብ ያዡ አገልግሎት በሚያቆምበት ጊዜ የተሟላ የሂሳብ መዝገብ ለቤተ ክርስቲያን ቦርድ ማስረከብ።

**መጋቢዎችና ባለአደራዎች (137-140)**

137. የመጋቢዎች ቁጥር ከሦስት ሊያንስ ወይም ከአስራ ሦስት ሊበልጥ አይገባም። መጋቢዎች በዓመታዊ ወይም ልዩ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ላይ በአብላጫ ድምፅ የሚመረጡ ሲሆን፣ እስከሚቀጥለው ድረስ ሲየገለግሉ ይቆያሉ። (39፣ 113.7፣ 113.9. 127)

138. የመጋቢዎች ኃላፊነቶች የሚከተሉት ናቸው።
138.1. የተለየ መግለጫ እስካልተሰጠ ድረስ ከመጋቢው ጋር ሊቀመንበር ሆኖ የቤተ ክርስቲያን ዕድገት ኮሚቴ ውስጥ በማገልገል፣ የወንጌል ስርጭት የማስፋፋት ኃላፊነቶችን የመወጣት። የማስፋፋት ኃላፊነቶችን አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትንና ቤተ ክርስቲያን መሳ ሚስዮኖችን መደገፍን ይጨምራል።
138.2. ለተቸገሩትና ለተጨነቁት ዕርዳታና ድጋፍ መስጠት። መጽሐፍ ቅዱሳዊ የምዕመን መሪዎች ሚና ተግባራዊ አገልግሎቶችን መስጠት ነው (ሐዋ 6፡1-3፤ ሮሜ 12፡6-8)። ስለሆነም፣ መጋቢዎች ጊዜያቸውንና መንፈሳዊ ስጦታቸውን በአገልግሎት፣ አስተዳደር፣ ማበረታቻ፣ ምህረት፣ ጉብኝትና ሌሎችም አገልግሎቶች ላይ ማዋል ይኖርባቸዋል።
138.3. በአንቀጽ 110-10.8 እንደተጠቀሰው፣ በቤተ ክርስቲያን ቦርድ ውሳኔ የወንጌል ስርጭት የቤተ ክርስቲያን አባልነት ኮሚቴ ሆኖ ማገልገል።
138.4. አባላት ሁሉ የክርስቲያን አገልግሎት ዕድሎችን ገኙ ዘንድ በማደራጀት ረገድ መጋቢውን ማገዝ። በዚህ በኩል በቅርበም ሆነ በሩቅ ባህላዊ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ሥረ-መሠረት ላላቸው ወገኖች አገልግሎቶችን ለማድረስ ልዩ ትኩረት መስጠት አለበት።
138.5. ለማህበረሰብ ክርስቲያናዊ ተግባርና አገልግሎት ድርጅቶች እንደ መገናኛ ሆነ ማገልገል።
138.6. በአምልኮ ፕሮግራሞች መጋቢውን ማገዘንና አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖችን መንከባከብ።
138.7. የቅዱስ ቁርባን ዕቃዎችን ማቅረብና መጋቢው በጠየቀው ጊዜ ቅዱስ ቁርባን በማደል ማገዝ። (34.5፣ 413.9)
139. የመጋቢዎች አገልግሎት ክፍተት በአግባቡ በተጠራ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ሊሟላ ይችላል (113.8)
140.ባለአደራዎች የሚያካትተው የባለአደራ ኮሚቴ ከመጋበዊውና ከዋና ጽ/ቤቶች የመዋለንዋይ ቢሮ የአባለአደራነት ዕድገት አገልግሎቶች ቢሮ ጋር በመተባበር በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያናዊ ባለአደራነትን የማሳደግ ተግባር ያከናውናል። (38 — 8.5)

**የንብረት አስተዳዳሪዎች (141 – 144)**

141. የቤተ ክርስቲያን የንብረት አስተዳዳሪዎች ቁጥር ከሦስት ሊያንስ ወይም ከዘጠኝ ሊበልጥ አይገባም። የንብረት ጠባቂዎች ከቤተ ክርስቲያን አባላት መካል ተመርጠው ለሚቀጥለው የቤተ ክርስቲያን ዓመትና ተተኪዎች እስኪመረጡና ሥራውን እስክለምዱ ድረስ ሲያገለግሉ ይቆያሉ። (39፣ 113.11፣ 127)
142. የሀገርቱ ሕግ የቤተ ክርስቲያን የንብረት አስተዳዳሪዎችን በተለየ መንገድ እንዲመረጡ የሚደነግግ ከሆነ፣ ይህንኑ በትክክል መከተል ያስፈልጋል። (113.4)
142.1. የሀገርቱ ሕግ የሚደነግገው ነገር ከሌለ የንብረት ባለአደራዎች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዓመታዊ ጉባኤ ላይ ወይም ለዚህ ዓላማ በተጠራ ልዩ ጉባኤ ላይ በድምፅ ብልጫ ይመረጣል። 113.7፣ 113.11)

143. የንብረት አስተዳዳሪዎች ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።
143.1. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በማህበር ሳትደራጅ ስትቀር፣ ወይም ማህበራዊ ሕግ የሚጠይቀው ሲሆን፣ ወይም ሌሎች የቀጠና ኃላፊና የቀጠና አማካሪ ቦርድ ያመነባቸው ምክንያቶች ሲኖሩ፣ የቤተ ክርስቲያን ንብረት በባለቤትነት ማስተዳዳር። ይህም በአንቀጽ 102-4.4 ምሪትና ገደቦች መሠረት የሚፈጸም ይሆናል።
143.2. የቤተ ክርስቲያን ቦርድ የተለየ አቅጣጫ እስካልተከተለ ድረስ ለቁሳዊ ንብረቶች ዕድገት መዋለንዋያዊ ዕቅዶችን ምሪትን መስጠት።
144 የንብረት አስተዳዳሪዎች ዘንድ የተከፈተ የግለሰቦች ክፍተት በአግባቡ ለዙህ ጉዳይ በተጠራ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ መሟላት አለበት (113.8)

**የሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎት (145)**

145. እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በዓመታዊ ስብሰባዋ ላይ የቤተ ክርስቲያን ቦርድ አካል ሆኖ የሚሠራ የሰንት ትምህርት ቤትና የደቀዘምሙርነት ዓለማቀፍ አገልግሎት ወይም የትምህርት ኮሚቴ ማቋቋም አለባት። ይህ ቦርድ ወይም ኮሚቴ ወይም ኮሚቴ የቤተ ክርስቲያንን የክርስቲናዊ ትምህርት አገልግሎቶች የማስፋፋት ኃላፊነት ይኖረዋል። ሳና አምስት ወይም ከዚያ የሚያንሱ አባላት በሚገኙበት ቤተ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን ቦርድ ይህንኑ ተግባር ሊያከናውን ይችላል። አባላቱም የሰንበት ትምህርት ቤት ኃላፊ (146)፣ መጋቢ፣ የናዛሪን ሚሲዮን ዓለም አቀፍ ፕሬዚዳንት፣ የናዛሪን ወጣቶች ዓለምአቀፍ ፕሬዚዳን፣ ፣ የልጆች አገልግሎት ዳይሬክተር፣ አዋቂዎች አገልግሎት ዳይሬክተርና በዓመታዊ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ላይ የሚመረጡ ከሦስት እስከ ዘጠኝ የሚደረሱ የቤተ ክርስያን አባላት ይሆናሉ። አባላት ተከታታይ ላልሆነ የሁለት ዓመታት መንፈቆች ሊመረጡና ተተኪዎቻቸው እስኪመረጡ ድረስ ለያገለግሉ ይችላሉ። አንድ የተመረጠ አባል በሚጎድልበት ጊዜ በአግባቡ በተጠራ ስብሰባ ተምርጦ ሊሟላ ይችላል። ቤተ ክርስቲያን የትምህርት ኮሚቴን የቤተ ክርስቲያን ቦርድ አካል አድርጋ ከመረጠች ለባለአደራዎችና የንብረት አስተዳዳሪዎች በመተዳዳሪያ ደንቡ የተገለጸው አነስተና ቁጥር መጠቀም ይኖርባታል። (137፣ 141)።

አጥቢያ አብያተክርስቲያኖቻችን ሁለተናዊ ቀድስናን የሚለማመዱትንና ወደ ቅድስና የሚጠራንን የእግዚአብሔር ጻጋ የሚመሰክር ሕይወት የሚመሩትን ሰዎች እንዲመርጡ እንመክራቸዋለን። ከናዛሪን ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮዎች፣ ደንቦችና ልምምዶች ጋር የሚስማሙ፣ በአምልኮው ላይ በመገኘት፣ በአሥራታቸውና በመጽዋታቸው ቤተ ክርቲያኒቱን የሚያገለግሉ ሰዎችን እንዲመረጡ እንመክራለን። (39)

የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎት ዓለማቀፍ ቦርድ ወይም የትምህርት ኮሚቴ ተግባራትና ሥልጣን የሚከተሉት ናቸው።

145.1. ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የክርስቲያናዊ ትንምህርትን አገልግሎት ማቀድ፣ ማደራጀት፣ ማስፋፋትና ማካሄድ ይህም በመጋቢው ቀጥተኛ ተንከባካቢነት፣ የሰንበት ትምርት ቤት ኃላፊ አመራርና የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቦርድ ምሪት የሚካሄድ ሲሆን፣ ከቤተ እምነታዊ ዓላማዎቹ፣ ጠቅላላ ቦርድ

ከመሠረታቸውና በሰንት ትምህርት ቤት አገልግሎት ጎን ለቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና አስተህምህሮ መሠረታዊ ጠቀሜታ አለው፡፡ ሳምንታዊና እንደ ካቢያን፣ የክረምት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶችና የላጤዎች አገልግሎቶች ያሉ ዓመታዊ/ልዩ አገልግሎቶች አማኞች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን በሕይወታቸው የሚለማመዱባቸውንና ከማህበረ ምእመናን ሕይወት ጋር የሚጣመሩባቸውን መልካም ዕድሎች ይፈጥራሉ፡፡ (415.15)

145.2. ያላመኑትን ሰዎች ወደ ክርስቶስና ወደ ቤተ ክርስቲያን ህብረት ለማምጣት፣ በፍሬያማ መልኩ የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማርማ ደህንነትን እንዲያገኙ ማገዝ፡፡ የክርስቲያናዊ ቤተሰብ አመለካከትና ልምድ እንዲያጎለብቱ መረዳት፣ ክርስቲያናዊ ቤተሰብ እንዲመሠረቱ ማገዝ፣ አማኞችን ለቤተ ክርስቲያን አባልነት ማዘጋጀት፣ እንዲሁም ለተገቢው ክርስቲያናዊ አገልግሎት ማስታጠቅ፡፡

145.3. ሁል ጊዜም በናዛሪን ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥናትና አስተምህሯዊ አተረጓጎም ላይ የተመሠረቱ የተለያዩ አገልግሎቶችን ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀት፡፡

145.4. ከሰንት ትምህርት ቤት ደንቦች ጋር የሚስማማ አጠቃላይ የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት ዓለማቀፍ አገልግሎት ለአጥያ ቤተ ክርስቲያን ማቀድና ማደራጀት፡፡ (812)

145.5. የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት ዓለማቀፍ አገልግሎት ኃላፊ ሆኖ የሚሠራ አንድ ወይም ከዚያ የሚበልጡ ሰዎችን መጋው በሚያፀድቀው መሠረት ለዓመታዊ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ መጠቆም፡፡ ጥቆማዎቹ የሚካሄዱት በሥራ ላይ ያለው ኃላፊ በሌለበት መሆን አለበት፡፡

145.6. የልጆችና የአዋቂዎች አገልግሎቶች ዳይሬክተሮችን መጋቢው ባፀደቀው መሰረት ለቤተ ክርስቲያን ቦርድ መጠቆም፡፡

145.7. የልጆችና የአዋቂዎች አገልግሎቶች ዳይሬክተሮች በሚያቀርቡት ጥቆማ መጋቢውና ሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት ዓለማቀፍ አገልግሎት ኃላፊ በሚፀድቁት መሠረት የልጆችና አዋቂዎች ካውንስሎችን መምረጥ፡፡

145.8. በናዛሪን ወጣቶች ዓለም አቀፍ ፕሬዚዳንት፣ የልጆችና አዋቂዎች አገልግሎቶች ዳይሬክተሮች ጥቆማ ከቀረቡት እጩዎች መካከል ምሳሌያዊ ሕይወት የሚመሩትንና ከናዛሪን ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮዎች ለሁሉም የዕድሜ ቡድን የሰንበት ትምህርት ቤት ተቆጣጣሪነት፣ አስተማሪነትና አገልጋይነት መምረጥ፡፡ ጥቆማው በመጋቢውና ሰንበት ትምህርት ቤት ኃላፉ መጽደቅ አለበት፡፡

145.9. ለሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት ዓለማቀፍ አገልግሎት ሠራተኞችና አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን አባላትን መደበኛ የሥልጠና ዕድሎችን የሚያደራጅ፣ የሚያስፋፋና የሚቆጣጠር ቀጣይ የምእመን ሥልጠና አጥቢያዊ ዳይሬክተር መምረጥ፣ የሰንት ትምህርት ቤት አገልግሎቶች ቦርድ ቀጣይ የምእመን ሥልጠና አጥቢያው ዳይሬክተርን ለዚህ ቦረድ በአባልነት የመሰየም አማራጭ ይኖረዋል፡፡

145.10. መደበኛ ስብሰባዎችን ማካሄድ፣ የቤተ ክርስቲያን ዓመት ጋር አንድ ዓይነት በሆነው የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት ዓለማቀፍ አገልግሎት መጀመሪያ ላይ ፀሐፊውና አስፈላጊዎች መሆናቸው የታመነባቸውን

ሌሎች አገልገጋዮች በመምረጥ ማደራጀር (114)፡፡ መጋው የታመነባቸውን ወይም የሰንት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት ዓለማቀፍ አገልግሎት ኃላፊ ልዩ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

**የናዛሪን ወጣቶች ዓለምአቀፍ/ናወዓ ካውንስል (150-151.5)**

150. የናዛሪን ወጣቶች አገልግሎት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የናዛሪን ወጣቶች ዓለም አቀፍ በሚያፀድቀውና በሚሰጠው ድጋፍ የሚካሄድ ነው፡፡ በናዛሪን ወጣቶች ዓለም አቀፍ ቻርተርና በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ቦርድ ሥልጣን አከከባቢያዊ ቡድኖች ይደራጃሉ፡፡

150.1. አከባቢያዊ የናወዓ ከናወዓ አከባቢያዊ አገልግሎት እቅድ መሠረት ራሱን ሊያደራጅ ይችላል፡፡ ይህም ከናወዓ ቻርተርና ከናዛሪን ቤተ ክርስቲያን የወጣቶች አገልግሎትን ፍላጎቶች የሚያሟላ ሆኖ የሚዘጋጅ ነው፡፡

150.2. የናወዓ ካውንስል አጥቢያዊ ናወዓን ያስተባብራል፡፡የናወዓ ካውንስል 12 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆናቸው ወጣቶች፣ ለኮሌጅ/ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና ወጣት አዋቂዎች አገልግሎትን የማቀድና የማደራጀት ኃላፊነት ያለው ሲሆን፣ በአጠቃላይ ለአጥቢያ የወጣቶች አገልግሎት ራዕይ ይኒረዋል፡፡ ከሰንበት ትምህርት/ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት/ የትንንሽ ቡድን ጋር የተያያዘ የናወዓ ካውንስል ሥራ ሁሉ የሰንበት ትምህርትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎት ዓለም አቀፍ ቦረድ በሚያጸድቁት መሠረት የሚካሄድ ነው፡፡

150.3. የናዛሪን ወጣቶቸ ዓለም አቀፍ (ናወዓ) ካውንስል አባላት ፕሬዚዳንቱ፣ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ፍላጎቶች አንጻር የሚካሄዱ የአገለግሎቶች መረዎችን፣ የወጣቶች ተወካዮችና የአግልግሎቶቹ ድይሬክተሮችን፣ የአጥቢያ ፓስተርና/ወይም የወጣቶች ፓስተር የሚገኙበት ነው፡፡ የናወዓ ካውንስል አገልጋዮች የሚያገለግሏት የናዛሪን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ይሆናሉ፡፡ ካውንስሉ ለቤተ ክርስቲያን ቦርድ ተጠሪ ይሆናል፡፡

150.4 የናዛሪን ወጣቶቸ ዓለም አቀፍ (ናወዓ) ካውንስል አባላት የሚመረጡት በናወዣ አባላት ይሆናል፡፡ የናወዓ አባላት ለናወዓ ፕሬዚዳንት ምርጫ ድምፅ ሊሰጡ የሚችሉት የናዛሪን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባላት ከሆኑ ብቻ ነው፡፡

**151 የናወዓ ፕረዘዳንት፡፡** የናዛሪን ወጣቶች ዓለም አቀፍ አጥቢያዊ ቡድን ፕሬዚዳት የሚመረጠው በናወዓ አጥቢያዊ የአገልግሎት ዕቅድ መሠረት ሲሆን፣ ምርጫው ተግባራዊ የሚሆነው በናወዓ ዓመታዊ ስብሰባ ላይ በተገኙትና የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን አባላት በሆኑት የናወዓ አባላት ነው፡፡ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መጋቢና የቤተ ክርስቲያን የተጠቆሙትን ሰዎች ያፀድቃል፡፡ የናወዓ ፕሬዚዳንት የቤተ ክርስቲያን ቦርድ (127)፣ የሰንበት ትምህርትና ደቀመዝሙርነት አገልግሎት ዓለም አቀፍ ቦርድ (145)፣ እና የቀጠና ጉባኤ (201) አባል ይሆናል፡፡ ‹‹ፕሬዚዳንት›› የሚለው ቃል ለአንድ ባህል አጥጋቢ ካልሆን አጥቢያዊ የናወዓ ካውንስል በድንፅ ብልጫ ተስማሚ ስያሜ ሊለውጥ ይችላል፡፡

**የናወዓ ፕሬዚዳንት ተግባርት የሚከተሉት ናቸው፡፡**

151.1. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የወጣቶች አገልግሎት ለማስፋፋት የናወዓን ካውንስል በሊቀመንበርነት መምራት፡፡

151.2. ለወጣቶች የሚስዮናዊነት አገልግሎት ትኩረት ለማሰፋፋት ከናዛሪን ሚስዮን ዓለም አቀፍ (ናመዓ) ፕሬዚዳንት ገር መሥራ፡፡

151.3. በአንቀጽ 147.1 -47.9 ለሁሉም የዕድሜ ኑድን ዳይሬክተሮች እንደተገለጸው እነዚህን ተግባራት ለወጣቶች የሰንበት ትምህርት ተግባራዊ ማድረግ።
151.4. ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቦርድ ወርሃዊ ሪፖርት ማድረግና ለዓመታዊ የአጥቢያ ቤተ ክርስያቲያን ጉባኤ ሪፖርት ማቅረብ። (113.9፣ 127)
151.5. በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የወጣቶች መጋቡ በሚቀጥርበት ጊዜ መጋው ከቤተ ክርስያን ቦርድና ከናዋዓ ካውንስል ጋር በመማከር የናዛሪን ወጣቶች ዓለማአቀፍ ካውንስልን ተግባር የወጣቶች መጋቢ እንዲያከናውነው ያደርጋል። ይህም የወጣቶች መጋቢ እሱ በሌለበት ጊዜ የናወዓ ፕሬዚዳንት እንዲያከናውን የተገለጹትን ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል። ይህም የናወዓ ፕሬዚዳንት የምዕመን አመራር፣ ድጋፍና የአጥቢያ የወጣቶች አግልግሎት በመወከል መሥራቱን እንዲቀጥል ያደርጋል። መጋቢው፣ የወጣቶች መጋቢና የናወዓ ካውንስል በመተባበር እነዚህ ሁለት ኃላፊዎች ለቤተ ክርስቲያኒቱ የወጣቶች አገልግሎት ፍሬያማነት እንዴት አብረው ሊሠሩ እንደሚችሉ የሚያሳዩትን የሥራ ኃላፊነቶችና ድርሻዎች ይወስናሉ። የወጣቶች መጋቡ የናዋዓ ፕሬዚዳን ሆኖ አያገለግልም። (160.4.)

## የሴቶች ህብረት እና የወንዶች ህብረት

የሴቶች እና የወንዶች ህብረት የሚል ነገር በቤተ ክርስቲያኗ መማሪያ ውስጥ አልተጠቀሰም። የናሚዓ እና ናወዓ በሚደራጅበት መንገድ ልደራጅ ይገባዋል። የናሚዓ እና የናወዓ ፕረዜዳንቶች በቤተ ክርስቲያን ቦርድ ውስጥ እንደሚታቀፉ ሁሉ የወንዶች እና የሴቶች ህብረተም ብታቀፉ ጥሩ ነው።

## የቀጠና አደረጃጀት

### የቀጠና ጉባኤ (200 – 205)

በአንድ መልካምድራዊ አቀማመጥ ያሉ የናዛሪን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት በአንድነት በመሰባሰብ ቀጠና ይመሠርታሉ። በናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሦስት ዓይነት የቀጠና አመሠራረት አለ።

### ደረጃ 1፡

የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አከባቢ ስጀመር ያ ደረጃ 1 ይባላል። የክልል ዳሬክተሩ ለአጠቃላይ ኃላፊው በዚህ አዲስ አከባቢ የቀጠና ኃላፊ ልሆን የምችል ሰውን ይጠቁማል። አጠቃላይ ኃላፊውም የቀጠና ማሪውን ይሾማል።

### ደረጃ 2:

ደረጃ ሁለት ቀጠና ቢያንስ በሥሩ ዐስር የተደራጁ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ያሉት (500 ሙሉ አባላትና 5 የተቀቡ ሽማግሌዎች እንዲሁም 50 ከሙቶ የሚሆነው ቀጠናው የገንዘብ ምንጭ የሚገኘው ከቀጠናው ውስጥ መሆን አለበት)

| | |
|---|---|
| **ደረጃ ሁለት ቀጠና** | **የቀጠና ኃላፊው ልሾም ወይም ልመረጥ ይችላል** |

| | | |
|---|---|---|
| መሥፈርተፐች | 10 የተደራጁ ቤተ ክርስቲያናት | 5 የተቀቡ ሽማሌዎች. |
| | 500 አባላት | 50% ራሱን የሚችል |

የቀጠና መማክርት ቦርድ ደረጃ ሁለት ቀጠና ሆነው ለመደራጀት ይችሉ ዘንድ መጠየቅ ይችላል። የመስክ ዳሬክተሩ፣ የክልል ዳሬክተሩ እና አጠቃላይ ኃላፊው ይህንን ጥቆማ ለአጠቃላይ ኃላፊዎች ቦረድ ያቀርባሉ። የቀጠና ኃላፊ እንድመረጥ ይደረጋል ወይም በቀጥታ ይሾማል።

**ደረጃ 3፡**

ደረጃ 3 ቀጠና ተብሎ የሚጠራው የበሰሉ መሪዎች እንዳሉት፣ ራሱን ነራሱን በገንዘብ ማስተዳደር የሚችል፣ ለቤተ ክርስቲያኒቷ አስተምህሮ ታማኝ የሆነ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለቤተ ክርስቲኒቷ እድገት ታማኝ መሆኑን ያሳየ ቀጠና ነው።

ደረጃ 2 ቀጠና ቢያን 20 የተደራጁ ቤተ ክርስቲያናት፣ 1000 አባላት፣ 10 የተቀቡ ሽማግሌዎች እና 100 እጅ የአስተዳደር ወጭውን በራሱ የሚችል ቀጠና ነው።

የቀጠና ኃላፊው በቀጠና ጉባኤ የሚመረጥ ይሆናል።

**የቀጠና ጉባኤ**

የቀጠና ጉባኤ አባላት:

- ሁሉም ሽማግሌዎች
- የቀጠና የአገልግሎት ፈቃድ ያላቸው መጋቢዎች
- የቀጠና ጸሐፊ
- የቀጠና ገንዘብ ያዥ
- የቀጠና የሰንበት ትምህርት ቤት ዳሬክተር
- የቀጠና ናወዓ ፕሬዜዳንት
- የቀጠና ናሚዓ ፕሬዜዳንት
- የእያንደንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አድስ ተመራጭ የሰንበት ትምህርት ኃላፊዎች
- የእያንደንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አድስ ተመራጭ የናወዓ ፕሬዜዳንት
- የእያንደንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አድስ ተመራጭ የናሚዓ ፕሬዜዳንት
- የቀጠና መማክርት ቦርድ አባል የሆኑ ተራ ምዕመናን
- የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች

| **የቤተ ክርስቲያን አባላት**: | **ተወካዮች**: |
| --- | --- |
| 1-50 **አባላት** | - 2 **ተወካዮች** |
| 51 – 100 **አባላት** | - 3 **ተወካዮች** |
| 101 – 150 **አባላት** | - 4 **ተወካዮች** |
| 151 - 200 **አባላት** | - 5 **ተወካዮች** |

ይህ ማለት እያንዳዱ አጥያ ቤተ ክርስቲያናት እነዚህን ሰዎች ለቀጠና ጉባኤ ይልካል ማለት መው፡፡

1. መጋቢ፣ እርሱ/እርሷ የአገልግሎት ፈቃድ ያለው ከሆነ ወይም የተቀባ ከሆነ
2. የሰንበት ትምህርት ቤት ኃላፊ
3. ናወዓ ፕሬዜዳንት
4. ናሚዓ ፕሬዜዳንት
5. በቀጠና የተመረጡ ተወካዮች 2, 3, 4, or 5 ተወካዮች ወይም ተጨማር ተወካዮች፣ ይህ የሚወሰነው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቱ ስፋት ነው፡፤

**የቀጠና ጉባኤ የሚደረግበት ጊዜ**

የቀጠና ጉባኤ የሚደረገው አጠቃላይ ኃላፊው በወሰነው ጊዜ በየዓመቱ ይሆናል፡፡

**በቀጠና ጉባኤ የሚከናወኑ ተግባራት**

የቀጠና ጉባኤ ከእነዚህ አካላት ዓመታዊ የክንውን ሪፖርት ያደምጣል፡፡

1. ከሁሉም ሽማግሌዎች እና የቀጠና አግልግሎት ፈቃድ ያላቸው አካላት
2. የቀጠና ኃላፊው
3. የቀጠና ገንዘብ ያዥ
4. የቀጠና ጉባኤ ኮሚቴ
5. የሥነ መለኮት ዳሬክተር
6. የአገልግሎት ትምህርት ቦርድ
7. የአገልግሎት ፈቃድ ሰጭ ቦርድ

የቀጠና ጉባኤ እነዚህን መሪዎች፣ ቦርዶች እና ኮሚቴዎች ይመርጣል:

- የቀጠና ኃላፊ (203.11)
- የቀጠና መማክርት ቦርድ (203.14)
- የቀጠና የአገልግሎት ፈቃድ ሰጭ ቦርድ (203.15)
- የአገልግሎት ትምህርት ቦርድ (203.16, 203.17)
- የቀጠና የሰንበት ትምህርት አገልግሎት ቦርድ (203.20, 237)

• የቀጠና ንብረት ቦርድ (203.18)

የቀጠና ጉባኤ ከዚህ በተጨማሪ እነዚህ ተግባራት ያከናውናል፡

- ለመጋቢዎች የአገልግሎት ፈቃድ ይሰጣል (203.4)
- መጋቢዎችን ለቅባት ያጸድቃል (203.6 203.7)
- ከሌላ ቤተ እምነት የመጣ መጋቢን የናዝሪን ቤተ ክርስቲያን መጋቢ እንዲሆን ፈቃድ ይሰጣል
- የቀጠናውን የመዋዕለ ነዋይ ሪፖርት በመመርመር ያጸድቃል district.

**የቀጠና ኃላፊ (206 -214.1)**

206.በቀጠና ጉባኤ የተመረጠ የቀጠና ኃላፊ የቀጠና ጉባኤው ከተጠናቀቀ 30 ቀናት በኋላ የመጀመሪያ ዙር አገልግሎቱን ይጀምራል፡፡ ይኸው አገልግሎት ለሁለት ዓመታት ከቀጠለ በኋላ በምርጫው የሁለተኛ ዓት የቀጠና ጉባኤ ፍጻሜ ላይ ይጠናቀቃል፡፡ በዚህ ጉባኤ ወቅት የቀጠና ኃላፊው እንደገና ሊመረጥ (203.11 — 3.12) ወይም ተተኪው ሊመረጥ ወይም ሊሾምና ብቁ ሊሆን ይችላል፡፡ በሥልጣን ላይ ያለው ጠቅላላ ኃላፊ የሾመው የቀጠና ኃላፊ የመጀመሪያ ዙር አገልግሎ ከተሾመበት ጊዜ የሚጀምር ሲሆን፣ የቀጠና ኃላፊው የተመረጠበትን የቤተ ክርስቲያን ዓመት ቀሪ ጊዜ ይጨምረራል፡፡ ይኸው አገልግሎት ለሁለት የቤተ ክርስቲያን ዓመታት የሚቀጥል ይሆናል፡፡ አገልግሎት ጊዜው የቀጠናው ጉባኤው ከተፈጸመ 30 ቀናት በኋላ ይጠናቀቃል፡፡ በዚህ ጊዜ የቀጠና ኃላፊው ለተጨማሪ ዙር እንደገና ሊመረጥ (203.11 — 3.11)፣ ወይም ተተኪው ሊመረጥ ወይም ሊሾምና ብቁ ሊሆን ይችላል፡፡ (203.10 — 3.12)

207. የቀጠና ጉባኤ የሚካሄድበት ጊዜ ከመድረሱ በፊት በሆነ ምክንያት ክፍተት ቢፈጠር ጠቅላላ ኃላፊዎች ከቀጠና የመማክርት ቦርድ፣ ከቀጠና የሰንበት ትምህርት አገልግሎቶች ቦርድ፣ ከቀጠና ናሚዓና ናወዓ ፕሬዚዳንቶች፣ ከቀጠና ፀሐፊና ከቀጠና ፀሐፊ የተውጣጡ አባላት ከሚገኙበት ኮሚቴ ጋር በመተባበር ክፍተቱን ሊሞሉት ይችላሉ፡፡ (307.8)
207.1. የደረጃ 1 እና ደረጃ 2 ቀጠናዎች የቀጠና ኃላፊ እንደሌላቸው ልወሰን የሚችለው በሥራ ላይ ባሉት ጠቅላላ ኃላፊ ጥቆማ ነው፡፡ የደረጃ 3 ቀጠናዎች የቀጠና ኃላፊ እንደሌለው የሚገለጸው በቀጠና መማክርት ቦርድ፣ በቀጠና የሰንበት ትምህርትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎት ሊቀመንበር እና በናዛሪን ሚሲዮን ዓለምአቀፍ እና በናዛሪን ወጣቶች ዓለምአቀፍ፣ በቀጠና ፀሐፊ እና በቀጠና ገንዘብ ያዥ ሁለት ሦስተኛ ድምጽ ስያገኝ ነው፡፡ (321)
207.2. የቀጠና ኃላፊው ጊዜያዊ ብቃት ጉድለት ካለበት፣ የሥልጣን ላይ ያለው ጠቅላላ ኃላፉ ከቀጠና የመማክርት ቦርድ ጋር በመመካከር ብቃት ያለው ሽማግሌ ጊዜያዊ የቀጠና ኃላፊ ሆኖ እንዲያገለግል ሊሾም ይችላል፡፤ የብቃት ጉድለት ጥያቄ በሥልጣን ላይ ባለው ጠቅላላ ኃላፊና ቀጠና መማክርት ቦርድ ይወሰናል፡፡ (307.8)
207.3. የቀጠና ኃላፊው የመልቀቂያ ደብዳቤ በሚስገባበት ወይም ሥራው

በሚያቋርጥበት ጊዜ የቀጠና ቢሮ ሠራተኞች፣ የሥራ አስፈጻሚ ዋና አለቃ ወይም በቀጠናው የሚደጎም ማንኛም ሥራ፣ ተከፋይም ይሁን የማይከፈለው፣ ይህ ረዳተ የቀጠና መሪውን እና የቢሮ ጸሐፊን ያካትታል ከቀጠናው መሪ የመልቀቂያ ደብዳቤውን ባስገበበት ቀን እነርሱ ማስገባት አለባቸው። ይኹንና በሥራ ላይ ባሉት የጠቅላላ ኃላፊውና በቀጠናው አማካሪ ቦር የጽሑፍ ፍቃድ መሠረት በቢሮ ውስጥ ካሉት ሰዎች መካከል አንዱ ልቀር ይችላል። ነገር ግን ይህም ሰው ቢሆን በዚያ ቢሮ ውስጥ የሚቆየው አዲሱ የቀጠና መሪ ሥራው እስከሚጀምርበት ቀን ድረስ ይሆናል። (241.3)

207.4. ከቀጠና መማክርት ቦርድና ከተመካከረ በኋላና በሥራ ላይ ባሉት ጠቅላላ ኃላፊው ፍቃድ አዲሱ ተመራጭ ወይም ተሻዋሚ የቀጠና ኃላፊ የቀድሞዎቹን ሠራተኞች ተቀጣሪዎች እንዲሆኑ ልጠቁም ይችላል። (241.3)

208. **የቀጠና ኃላፊ ተግራት የሚከተሉት ናቸው።**

**208.1.**በሥልጣን ላይ ያለው ጠቅላላ ኃላፊ በሚያፀድቁት መሠረት በቀጠና ጉባኤ ውስጥ የሚገኙትን አጥቢያ አብያተክርስቲያናት ማደራጀት፣ እውቅና መስጠትና መቆጣጠር። (110፣ 435.12)

208.2. በቀጠና ጉባኤ ውስጥ የሚገኙ አጥቢያ አብያተክርስያናት በሚፈልጉት ጊዜ ከመካከላቸው መገኘትና ስለ መንፈሳዊ፣ መዋለንዋያዊና መጋቢያዊ ጉዳዮች ከቤተ ክርስቲያን ቦርድ ጋር መማከር።

208.3. የቀጠና ኃላፊ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ጤናማ ባልሆ ውቅድቀት ውስጥ እንደመምትገኝና በአገልግሎት መቀጠሏ ለህልውናዋ ለወንጌል ስርጭት ውጤታማነት አስጊ እንደሆነ በሚገነዘብበት ጊዜ ሁኔታዎቹን ለመገምገም ከመጋቢው ወይም ከመጋውና ከቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ ውጤታማነት ለሚያደናቅፉ ችግሮች መፍትሔ ለማፈላለግ ከመጋውና ከቤተ ክርስቲያን ቦርድ ጋር ከፍተኛ ጥረት ሊያደረግ ይገባል።

የቀጠና ኃላፊው ከመጋቢው/ወይም ቦርዱ ጋር ከሠራ በኋላ ተጨማሪ ምርመራ ያስፈልጋል ከሚል ድምደሜ ላይ ከደረሰ፣ ቀጠና መማክርት ቦርድና በሥልጣን ላይ ያለው ጠቅላላ ኃላፊ በሚያፀድቁት መሠረት ለሁኔታው እልባት ለመስጠት ተገቢውን እርምጃ ሊወስድ ይችላል። እነዚህ እርምጃዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ። (1) መጋቢውን ማንሣት፣ (2) የቤተ ክርስቲኒቱን ቦርድ ማፍረስ፣ (3) የቤተ ክርስቲያኒቱን ጤንነትና የተልዕኮን ውጤታማነት ለመመለስ የሚያስችሊ ልዩ እርምጃዎችን መውሰድ።

208.4. በአንቀጽ 124.1 መሠርት በቀጠና ኃላፊው አመለካከት አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ችግር ውስጥ ከተገለጸ በኋላ ጣልቃ ለመግባት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ ተሟልተው መደበኛው አገልግሎት መቀጠል አለበት፤ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከገባችበት ችግር ውስጥ ወጣች በማለት ማጽደቅ የሚችለው በሥራ ላይ በለው የጠቅላላው ኃላፊው ማረጋገጫ የቀጠና መማክርት ቦርድ ነው።

208.5. በአንቀጽ 124.1 መሠረት ከእያንዳንዱ የአጥቢቤተ ክርስቲያን ቦርድ ጋር መደበኛ የቤተ ክርስቲያን/መጋቢ ክለሳ የሚካሄድበት ጊዜ ሰሌዳ ማውጣትና ይህንኑ ተግባር ማከናወን።

208.6. በቀጠና ጉባኤው ክልል በናዛሪን ቤተ ክርስቲያውን ውስጥ ለሚገኙት ሁሉም አዲስ ጅምር አብያተክርስቲያናት ልዩ ቁጥጥር ማድረግ።

208.7. የቀጠና ፀሐፊ ቢሮ አገልጋይ ባይኖረው ለቀጠና መማክርት ቦርድ አንድ ሰው መጠቆም። (216.1)
208.8. የቀጠና ገንዘብ ያዥ ቢሮ አገልጋይ ባይኖረው ለቀጠና የመማክርት ቦርድ አንድ ሰው መጠቆም። (219.1)
208.9. በልዩ የቻፕሊዮንሲ አገልግሎት የቅድስና የወንጌል ስርጭት እንዲስፋፋና እንዲያሳድግ ቀጠና ቻፕሊዮንስ ዳይሬክር መሾም። (236)
208.10. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን በመጋቢነት ስለሚያገለግል ሽማግሌ ወይም ፈቃድ ያለው አገልጋይ ጥቆማ ከቤተ ክርስቲያን ቦርድ ጋር መመካከርና ጥቆማውን መጽደቅ ወይም አለማጽደቅ። (115፣ 129.2፣ 160.8፣ 222.12)
208.11. የቤተ ክርስቲያንን/ከጋቢ ግንኙነት ስለ መከለስ ከቤተ ክርስቲያን ቦረድ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ በ90 ቀናት ውስጥ ልዩ የቤተ ክርስቲያን/መጋቢ ክለሳ (124( የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት።
208.12. አንድ የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን አባል ሽማግሌ መጋቢ ካልሆነባት አጥቢ ቤተ ክርስቲያን ቦርድ የአጥቢያ አገልግሎትን ፈቃድ ለማግኘት ወይም ለማሳደስ በጠየቀ ጊዜ ጥያቄውን ማጽደቅ ወይም አለማጽደቅ። (428.1፣ 428.3)
208.13. ከመጋቢና ከቤተ ክርስቲያን ቦርድ ማናቸውም ደመወዝ የሚከፈላቸውና የአጥቢያ ረዳቶች (እንደ ረዳት መጋቢዎች፣ የክርስቲያናዊ ትምህርት፣ የልች፣ የወጣቶች፣ የአዋቂዎች፣ የመዝሙር፣ የአዘቦት ትምህርት ቤቶች፣ ወዘተ. አገልጋዮች ወይም ዳይሬክተሮች ያሉትን) ለመቅጠር ጥያቄ ባቀረቡ ጊዜ ማጽደቅ ወይም አለማጽደቅ። የቀጠና ኃላፊ ደመወዝ የሚከፈላቸውን ሠራተኞችን ቅጥር የሚያጸድቀው ወይም የማያጸድቀው በወዳሚነት ቤተ ክርስቲያኒቱ የአጥያ፣ የቀጠናና ጠቅላላ ኃላፊነቶችን ለመወጣት ነፍቀዷንና መቻሏን በማገናዘብ ነው። ረዳት መጋቢዎች ለይቶ መምረጡ የመጋቢውን ኃላፊነት ሲሆን የቀጠና ሃላፊ ተመራጩን ያለመቀበል መብት አለው። (129.27፣ 260 -60.8)
208.14. ከቀጠና የማመክርት ቦርድ ጋር አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ክርስቲያናዊ የቀን ትምህርት ቤቶች ለማካሄድ የሚቀርባቸውን ጥያቄዎች ማጽደቅ ወይም አለማጽደቅ። (152፣ 222.11፣ 415)
208.15. ከቀጠና የመማክርት ፀሐፊ ጋር የቀጠናውን ሕጋዊ ሰነዶች ማስፈጸምና መፈረም። (222.5)
208.16. ማናቸውንም ደመወዝ የሚከፈላቸውን የቀጠና ሠራተኞች ለቀጠና የመማክርት ጉባኤ መጠቆምና የሥራ አፈጻጸማቸውን መቆጣጠር። (241)
208.17. ከአንቀጽ 117 ጋር ተስማሚ በሆነ መልኩ መጋቢዎች መሾም።
208.18. የቀጠና መማክርት ቦርድ በሚያፀድቀው መሠረት፣ የቀጠና ኃላፊ የቤተ ክርስቲያ ቦርድ አባላት (ባለአደራዎች፣ ንብረት አስተዳዳሪዎች)፣ የሰንት ትምህርት አገልግሎቶችን ቦርድ ሊቀመንበር፣ እንዲሁም ሌሎች የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ሊሾም ይችላል። ይህም የሚሆነው ቤተ ክርስቲያኒቱ ከተመሠረተች አምስት ዓመት ካልሞላት፣ ወይም ወደም ሲል በተካሄደው ዓመታዊ ስብሰባ ላይ ድምፅ የሰጡ አባላት ቁጥር ከ35 ካነሰ፣ ወይም ከቀጠናው መደበኛ የገንዘብ ድጋፍ የማታገን ከሆነ፣ ወይም በችግሩ ውስጥ መሆኗ ከተገለጸ ነው። የእንዲህ ዓይነት ቦርድ አባላት ጠቅላላ ቁትር ከሦስት ሊበልጥ አይችልም። (117፣ 125)
208.19. በአንቀጽ 505 -5.3 ፣ሠረት በጉባኤው ቀጠናው ውስጥ በነበሩት

አገልጋዮች ላይ የሚቀርበውን የጽሑፍ ወቀሳ ማስመርመር።
208.20. በአንቀጽ 408.4 መሠረት ከቋሚ ወንጌላዊ ጋር በመመካከር የግል ግምገማና ክለሳ የጊዜ ሰሌዳ ማውጣትና ማካሄድ ይቻላል።
209. የቀጠና ኃላፊ በቤተ ክርስቲያን ቦርድ ስምምነት፣ እስከ ቀጣዩ የቀጠና ጉባኤ ድረስ የሚፈጠር ክፍተት ለመሙላት መጋ ሊሾም ይችላል። የተሾመው መጋቡ አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያን ቦርድ ወይም ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አጥጋቢ በማይሆንት ጊዜ የቀጠና ኃላፊው ሊያነሣው ይችላል። (129.5፣ 422፣ 428.6)
209.1. የቀጠና ኃላፊ በቤተ ክርስቲያን ቦርድና በቀጠና አማካር ቦርድ የመጋበውን ቦት ለመሸፍ የሽግግር መጋቢ ወይም ቋም መጋቢ እስኪኖራቸው ድረስ ሊሾም ይችላል። የቀጠና ኃላፊው ከቤተ ክርስቲያኒቱ ቦርድ ጋር በመመካከት የሽግግር ጊዜ መጋቢውን የአገልግሎት እንደ አስፈላጊነቱ ሊያስዝም ይችላል። የሽግግር ጊዜ መጋቢው የመጋቢውን ኃላፊነቶች የመወጣት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፤ የሽግግር ጊዜ መጋቢው የቤተ ክርስቲያኒቱ ተወካይ የመሆን ስልጣን ተሰጥቶታል።
እንዲህ ያለው የሽግግር ጊዜ መጋቢ ኃላፊነት ሁል ጊዜ በቀጠና ኃላፊውና የቀጠና መማክር ቦርድ ቁጥጥር ስር መሆን አለበት። የሽግግር ጊዜ መጋበው አስፈላጊ ሆኖ ስገኝ የቀጠናው ኃላፊ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ቦርድ ጋር በመማከር ከኃላፊነቱ ልያነሳው ይችላል። (423)
210. የቀጠና ኃላፊ በጉባኤ ቀጠናው ውስጥ ያለች ቤተ ክርስቲያን መጋቢ በማይኖራት ጊዜ የመጋቢውን አገልግሎቶች ሁሉ የማካሄድ ሥልጣን አለው። (412)
210.1. የቀጠና ኃላፊ በዓመታዊ ወይም ልዩ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ላይ በሊቀመንበርነት ይመራል ወይም ለዚሁ ኃላፊነት ሌላ ሰው ይሰይማል። (113.5)
211. በሥራ ላይ ያለው ጠቅላላ ኃላፊ በሆነ ምክንያት በቀጠና ጉባኤ ላይ ለመገኘት ካልቻለ ወይም እርሱን የሚወክል ሌላ ሰው ካልወከ የቀጠና ጉባኤውን የቀጠና ኃላፊው በጉባኤተኞቹ ሌላ ሰው ጉባኤውን እንደሚመራ እስኪመረጥ ድረስ ጉባኤው ይመራል፡፤
212. የቀጠና ኃላፊ በቀጠና ጉባኤ የመዋለንዋይ ኮሚቴ (203.21)፣ በቀጠና ኦዲቲንግ ኮሚቴ (203.25)፣ በቀጠና የአገልግሎት ጥናቶች ቦርድ (229.1)፣ በቀጠና የወንጌል ስርጭት ቦርድ ወይም በቀጠና የወንጌል ስርጭት ዳይሬክር (232)፣ በቀጠና የቤተ ክርስቲያኖች ቦርድ (234)፣ በቀጠና የሰንበት ትምህርትና የደቀ መዝሙርነት አገልግሎት ቦርድ (239)፣ እንዲሁም በቀጠና የችሎት (509) ውስጥ ሰው በሚጎድልበት ገዚ ሊተካ ይችላል። (509)
212.1. የቀጠባ ኃላፊ የቀጠና ቦርዶችንና ኮሚቴዎችን ሊቀመንበሮችና ፀሐፊዎች ይሾማል። ይህም የሚሆነው እነዚህ ደንቦች በመምሪያው ወይም በጉባኤው ተግባር ውስጥ ያልተካተተ እንደሆነ ነው።
212.2. የቀጠና ኃላፊ ከቀጠና የመማክርት ቦርድ ጋር በመማከር ከቀጠና ጉባኤ አስቀድሞ ለተለመዱ ኮሚቴዎችና አገልግሎቶች ግለሰቦችን የሚያውቁ ጠቋሙ ኮሚቴ ይሰይማል። (202.1)
213. የቀጠና ኃላፊ በአገልግሎት ደረጃው የቀጠና የመማክርት ቦርድ (221.2)፣ እንዲሁም የቀጠና የአገልግሎት ብቃቶች ማረጋገጫ ቦርድ ሊቀመንበር ይሆናል። (227.1)

213.1. የቀጠና ኃላፊ በአገልግሎት ደረጃው የሚያገለግለው ቀጠና የሚያቅፋቸው ተመራጭ፣ እንዲሁም ቋሚ ቦርዶችና ኮሚቴዎች አባል ይሆናል፡፡ (203.20 — 3.21፣ 233፣ 237፣ 810፣ 811)

214. የቀጠና ጉባኤ የቀጠና ኃላፊ ይፋዊ ተግባራት በሙሉ የመከለስ መብት ሲኖረው፣ ይግባኝ መጠየቅ ይችላል፡፡

214.1. የቀጠና ኃላፊ መጋቢዎችን ስለመሾምና ስለሌሎች ከቀጠና ኃላፊ ቦሮ ጋር ስለሚዛመዱ ጉዳዮች ሁልጊዜም በሥልጣን ላይ ላለው ጠቅላላ ኃላፊ ለጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ ምክር አክብቶት መስጠት ይኖርባታል፡፡

**የቀጠና ፀሐፊ (216-218)**

216. በቀጠና የመማልርት ቦርድ የሚመረጠው የቀጠና ፀሐፊ ተተኪው ተመርጦ ብዙ እስኪሆን ከአንድ እስከ ሥስት ዓመት ያገለግላል፡፡ (222.17)

216.1. የቀጠና ጉባኤ ከመድረሱ በፊት የቀጠባ ፀሐፊ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ቢያቋርጥ፣ በቀጠና ኃላፊ ጥቆማ የቀጠና የመማከርት ቦርድ ተተኪ ፀሐፊ ይመርጣል፡፡ (208.7)

216.2. የቀጠና ፀሐፊ በአገልግሎት ደረጃው ምክንያት የቀጠና ጉባኤ አባል ይሆናል፡፡ (201)

**217. የቀጠና ፀሐፊ ተግራት የሚከተሉት ናቸው፡፡**

217.21. የቀጠና ጉባኤውን ቃለ ጉባኤዎችን ሁሉ በትክክል መመዝገብና በታማኝነት መጠበቅ፡፡

217.2. የቀጠናውን አሀዛዊ መረጃዎች በሙሉ በትክክል መመዝገብና መጠበቅ፡፡

217.3. አሃዛዊ ሠንጠረዦች በይፋዊ ጆርናል ውስጥ ከመመዝገባቸው በፊት ኦዲት እንዲደረጉ ለጠቅላላ ፀሐፊ መካል፡፡ (320.6)

217.4. የቀጠናውን ጉባኤ ሰነዶች በሙሉ መጠበቅና ለተተኪው በአግባቡ ማስረከብ፡፡

217.5. ለእያንዳንዱ የአራት ዓመታት ጊዜ ሙሉ ይፋዊ ጆርናል ማዘጋጀትና ማስቀመጥ፡፡ (205.4.)

217.6. በናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ቦርዶችና ጠቅላላ አገልጋዮች መካከል ይሰራጭ የእያንዳንዱን ቀጠና ጊባኤ የታተመ ጆርናል በቂ ቅጂ ለጠቅላላ ዋና ጽ/ቤቶች ማስተላለፍ፡፡

217.7. በጠቅላላ ጉባኤ ዘንድ ተጠብቆ እንዲኖር ያለፉትን አራት ዓመታት በሙሉ ይፋዊ ጆርናል ለጠቅላላ ጉባኤ ማቅረብ፡፤ (203.26፣ 205.3 — 5.4)

217.8. ከአገልግሎት ጋር የሚዛመዱትን ሌሎች ተግባራት ሁሉ መፈጸም፡፡

217.9. የሚመጡትን ጉዳዮች ሁሉ ወደ ትክክለኛው የጉባኤ ኮሚቴ ወይም ቋሚ ቦርድ ማስተላለፍ፡፡

218. የቀጠና ፀሐፊ የቀጠና ጉባኤ የሚመርጣቸው ያህል ረዳቶች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡

**የቀጠና ገንዘብ ያዥ** (219-220.2)

219. በቀጠና የመማክርት ቦርድ የሚመረጠው ቀጠና ገንዘብ ያዥ እስከ ቀጣዩ የቀጠና ጉባኤ ማብቂያና ተከታዩ ተመር ብቁ እስኪሆን ድረስ ያገለግላል፡፡ (222.16)

219.1. የቀጠና ገንዘብ ያዥ በሆነ ምክንያት የቀጠና ጉባኤ የሚሰባሰብበት ጊዜ ሳይደርስ አገልግሎቱም ቢያቋርጥ፣ የቀጠና ኃላፊ በሚቀርበው ጥቆማ መሠረት የቀጠና የመማክርት ቦርድ ተተኪውን ይመርጣል፡፤ (208.8)

219.2. የቀጠና ገንዘብ ያዥ በአገልግሎት ደረጃው የቀጠና ጉባኤ አባል ይሆናል፡፡ (201)

220. **የቀጠና ገንዘብ ያዥ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡፡**

**220.1.** ጠቅላላ ጉባኤ ወይም የቀጠና ጉባኤ ወይም የቀጠና የመማክርት ቦርድ በወሰኑት ወይም የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ፍላጎቶች በሚጠይቋቸው መሠረት ከቀጠናው ገንዘብ መሰብሰብና በቀጠና ጉባኤና/ወይ፣ በቀጠና የመማክርት ቦርድ መመሪያ ፖሊሲዎች መሠረት ማከፋል፡፤

220.2. ለተቀበላቸውና ለከፈላቸው ገንዘቦች ሁሉ ትክክለኛ መዝገብ መጠቀም፣ ለቀጠና የመማክርት ቦርድ የሚደርሰው ወርሃዊ ሪፖርት ለቀጠና ኃላፊ ማስተላለፍና ተጠያቂ ለሆኑበት የቀጠና ጉባኤ ዓታዊ ሪፖርት ማቅረብ፡፡

**የቀጠና የመማክርት ቦርድ** (221-225)

221. የቀጠና የመማክርት ቦርድ የቀጠና ኃላፊ፣ ቀጠና ጉባኤ በየዓመቱ ወይም ከአራት ዓመታት ላልበለጠ ጊዜ እንዲያገለግሉ በአብላጫ ድምፅ የመረጣቻ ምእመን አገልጋዮችና የተሾሙ አገልጋየፐች የሚገኙበት ነው፡፡ ቀጠና የመማክርት ቦርድ አባላት ቀጣዩ የቀጠና ጉባኤ እስኪያበቃ ተተኪዎቻቸው ተመርጠው ብቁ እስኪሆኑ ድረስ ያገለግላሉ፡፡ ነገር ግን በየዓመቱ የተወሰኑ አባላትን በመምረጥ የአገልግሎት ዘመናቸውን ማሰባጠር ይቻላል፡፡

የአንድ ቀጠና አባላት ጠቅላላ ቁጥር ከ5000 በሚበልጥበት ጊዜ አንድ ተጨማሪ የተሾመ አገልጋይና አንድ ምእመን አገልጋይ ለ2500 አባላት ወይም ለመጨረሻው ዓቢይ 2500 አባላት ሊመርጥ ይችላል፡፡ (203.14)

221.1. የቀጠና የመማክርት ቦርድ ውስጥ አባላት ቢጎድሉ በተቀሩት አባላት ይካካሳሉ፡፡

221.2. የቀጠና ኃላፊ በአገልግሎት ደረጃው የቀጠና የመማክርት ቦርድ ሊቀመንር ይሆናል፡፡

221.3. የቦርዱን ተግባራት በመመዝገብ በጥንቃቄ ለተተኪው የሚያስረክብ ከአባላቱ መካከል ፀሐፊ ይመርጣሉ፡፡

221.4. የቀጠና የመማክርት ቦርድ ምእመን አባላት በአገልግሎት ደረጃቸው የቀጠና ጉባኤ፣ የቀጠና የሰንት ትምህርት ቤት አገልግሎቶች ኮንቬንሽን አባላት ይሆናሉ፡፡ (201፣ 221)

**222. የቀጠና የመማክርት ቦርድ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡፡**

222.1. ከአንቀጽ 114.1 ጋር በሚስማማ መልኩ፣ የቤተ ክርስቲያን ስታቲስቲካል ዓት የሚጀመርበትንና የሚፈጸምበትን ጊዜ ይወስናል፡፡ 222.2. ስለ ጉባኤው ቀጠና አገልጋዮችና አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ለቀጠና ኃለፊ መረጃና ምክር

መስጠት። (417)
222.3. በአንድ የክህነት አገልጋይ ላይ ወቀሳ ከቀረበ ሁኔታውን የሚመረምር ሦስት ወይም ከዚያ የሚበልጡ የተሾሙ አገልጋዮች ያሉበትን ኮሚቴ መሰየም። (505 — 5.3)
222.4. በክህነት አገልግሎት ላይ ክስ ከቀረበ የምርመራ ችሎት መሰየም። (505.5 - 5.6)
222.5. ማህበራዊ ሕግ በሚፈቅድበት ስፍራ የቀጠና ጉባኤ ሥልጣን ከሰጠ በኢንኮርፖሬሽን መደራጀት። ከኢንኮርፖሬሽን በኋላ የቀጠና ኃላፊ የቀጠና የመማርት ቦርድ ፀሐፊ፣ ወየም ሌሎች ኢንኮፐሬትድ የሆነ ወይም ያልሆነ የቀጠና የመማክርት ቦርድ ሥልጣን የሚሰጣቸው ሰዎች የሀብት፣ ንብረት የማስያዝ፣ የማስለቀቅ፣ ውሎች፣ እንዲሁም ሌሎች የቀጠና የመማክርት ቦርድ ህጋዊ ሰነዶችን ያስፈጽማሉ። ይፈርማሉ። (204)
222.6. ማህበራዊ ሕግ እንዲህ ዓይነቱን ኢንኮርፐሬሽን በማይፈቅድባቸው አገሮች፣ የቀጠና ጉባኤ የቀጠና የመማክርት ቦርድን እንደ ንብረት አስተዳዳሪ ሊመርጠው ይችላል። ይህም በራሱ ውሳኔ የመግዛት፣ በባሌቤትነት የመያዝ፣ የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ በዕዳ በማስያዝ፣ በአደራ የማስተዳደር፣ ባለቤትነተን ያለማዘዋወር፣ የሊዝና የቀጠና ተግባሩን ለማከናወን አስፈላጊ ወይም አመቺ በሆነ መልኩ ማንኛውንም ንብረት የማስተላለፍ ሥልጣን ይጨምራል። (102.6፣ 106.2፣ 222.5)
222.7. አጥቢያ አብያተክርስቲያናት በኢንኮርፖሬሽን ሊደራጁ በሚችሉባቸው አገሮች የቀጠና የመማክርት ቦርድ በብቁ ሕጋዊ ምክር ለቀጠናው መንግሥት ወይም መንግሥታት የሚስማሙ ምሳሌዊ የኢንኮርፖሬሽን ቅጾችን ያቀርባል። ይህ ምሳሌያዊ ኢንኮርፖሬሽን ቅጽ ሁል ጊዜም በአንቀጽ 102 -2.5 የተገለጹትን ደንቦች ማካተት አለበት።
222.8. የቀጠና ኃላፊ የቀጠናውን የአገልግሎት ክፈፍሎች፣ ቦርዶችና ኮሚቴዎች በመቆጣጠር የሚያከናውነውን ተግባር ማማከር።
222.9. ለቀጠና ማዕከል ምሥረታ የተወጠኑት ዕቅዶች ለጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ ማቅረብ። እንዲህ ዓይነቱን ዕቅዶች ሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት በጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ የጽሑፍ ድጋፍ መጽደቅ ይኖርባቸዋል። (319)
222.10. በመጋቢነት የሚገለግል ፈቃድ ያለው አገልጋይ ፈቃድ እንዲታደስ ድጋፍ መስጠት። (429.5)
222.11. አጥቢያ አብየጠክርስቲያናት ክርስቲያናዊ የቀን ትምህርት ቤቶችን ለማካሄድ የሚያቀርቧቸውን ጥያቄዎች ማጽደቅ ወይም አለማጽደቅ። የቀጠና ኃላፊና የቀጠና የመማክርት ቦርድ በሚሰጡት ውሳኔ የቀን ትምህርት ቤቶች ኮሚቴ ሊመሠረት ይችላል። የዞህ ኮሚቴ ተግባር ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የቀን ትምህርት ቤት የሚያገለግሉ ፖሊሲዎችን፣ የአሠራር ሂደቶችንና ፍልስፋና ለቀጠና የመማክርት ቦርድ ማቅረብና እንዲህ ዓይነት የቀን ትምህርት ቤቶች መሥረታ ማገገዝ፣ መደገፍና መቆጣጠር ነው። (152፣ 208.14፣ 415)
222.12. አንድ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ እንዲሆን የተጠቆመን የተቀባ ሽማግሌ ወይም የአገልግሎት ፈቃድ ያለው አገልጋይ እንዲሁም ተከፋይ ረዳት መጋቢ ሆኖ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ይሠራ የነበረና የዚያች ቤተ ክርስቲያን

አባል የሆነን አገልጋይ መቀበል ወይም አለመቀበል። እንዲህ አይነቱ ውሳኔ የሚወሰነው ከቀጠናው ኃላፊ ጋር በመመካከር ይሆናል። (115፣ 129.2፣ 160.8፣ 208.10)

222.13. ማንኛውንም በደመወዝ የሚሠራ የቀጠና ሠራተኞችን መምረጥ ወይም ከሥራው ማንሣት። (241-41.1)

222.14. ከቀጠና ኃላፊ ጋር በመመካከር በጉባኤው መካል እደ መዋለንዋይ ኮሚቴ ማገልገልና እንደ አስፈላጊነቱ የሥራ ባጀቶችን ማስተካከል። (220.1)

222.15. የዕዳ ክሶች ጨምሮ ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይንቀሳቀሱ የቀጠና ንብረት ከናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ውስጭ ለየትኛውም የኮርፖሬት ወይም ግለሰብ ጥቅም አልፎ እንዳይሰጥ መጠበቅ። (102.4፣ 106.5፣ 204)

222.16. በየዓመቱ የቀጠና ፀሐፊ ለአንድ ዓመት እንዲያገለግልና ተተኪው ተመርጦ ብቁ እስኪሆን ድረስ እንዲያገለግል መምረጥ። (216)

222.17. ተተኪው ተመርጢ ብቁ እስኪሆን ድረስ ከአንድ እስከ ሦስት ዓመታት የሚሠራ የቀጠና ፀሐፊ መምረጥ። (216)

222.18. በአንቀጽ 106.2 መሠረት ማንኛውም የናዛሪን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከናዛሪን ቤተ ክርስቲያን መልቀቅን በተመለከተ ውሳኔ መስጠት።

222.19. በአንቀጽ 203.5 መሠረት አስፈላጊ ሆኖ ስገኘት የቀጠና ኦዲትንግ ኮሚቴ በመምረጥ እስከ ቀጣዩ የቀጠና ጉባኤ እንዲያገለግሉ ማድረግ። (203.5)

222.20. ለቀጠናው ጉባኤ የተደረጉትን ስብሰባዎች ቁጥር ያካተተ አጠቃላይ የሥራ ሪፖርት ማቅረብ።

223. የቀጠና የመማክርት ቦርድ ወደ ሌላ የቀጠና ጉባኤ ለመሄድ የሚፈልጉትን የክህነት አገልጋዮች፣ የክርስቲያናዊ ትምህርት አገልጋዮች (409)፣ ወይም ዲያቆናት (406) አባልነት አባል የሆነበት ቀጠና ጉባኤ ከመሰብሰቡ በፊት ሊያስተለላልፍ ይችላል። ተቀባዩ ቀጠና ለነዚህ አገልጋዮች ሙሉ የአባልነት መብቶችና ጥቅሞች በመስጠት ሊቀበላቸው ይችላል። ተቀባዩ ቀጠና የመማክርት ቦርድ ስላስተላለፋቸው አገልጋዮች ከአገልግሎት ብቃቶች ማረጋገጫ ቦርድ የመጨረሻ ድጋፍ ያገኛል። (203.8 — 3.9፣ 228.9 — 28.10፣ 434 — 34.2)

223.1. የቀጠና የመማክርት ቦርድ የቀጠና ኃላፊ በሚያፀድቀው መሠረት፣ ወደ ሌላ ቤተ እምነት ለመሄድ ለሚፈልግ ሰው የድጋፍ የምስክር ወረቀት ሊሰጥ ይችላል።

224. የቀጠና የመማክርት ቦርድ የቀጠና ኃላፊ በሚያፀድቀው መሠረት ለቤተ ክርስቲያኒቱ በጎነት ሲባል ፈቃድ ያላትን ዲያቆን ከአገልግሎት ሊያግድ ይችላል። ይህም የሚሆነው ዲያቆኗ አባል ከሆነችበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቦርድ ጋር ከተነጋገረና በፍትሃዊ መንገድ ጉዳይዋን ከመረመረ በኋላ ይሆናል።

225. የሌላ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን የብቃት ማረጋገጫ የያዘ ፈቃድ ያለው ወይም የተሾመ አገልጋይ የቀጠና ጉባኤ ከመሰብሰቡ በፊት ከናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ጋ ለመተባበር ካመለከተ፣ የቀጠና የመማክርት ቦርድ የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫዎቹን ይመረምራል። እንዲህ ዓይነቱን አመልካች የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ሊሆን የሚችለው የቀጠና የመማክርት ቦርድ በሚሰጠው ድጋፍ ይሆናል። (417፣ 429.2፣ 432)

**የአገግሎት ብቃቶች ማረጋገጫ ቦርድ (226-228.10)**

226. የቀጠና የአገልግሎት ብቃቶች ማረጋገገጫ ቦርድ ከ5 የማያንሱና ከ15 የማይልጡ የተሾሙ አገልጋዮች በአባላነት የሚያቅፍ ሲሆን፣ ከእነዚህ አንዱ የቀጠና ኃላፊ ይሆናል። የቦርድ አባላት ተተኪዎቻቸው ተመርጠው ብቁ እስኪሆኑ ድረስ ለአራት ዓመታት ያገለግላሉ። ነገር ግን አንዳንድ አባላትን ቤዓመቱ በመተካት የአገልግሎት ጊዜያቸውን ማሰባጠር ይቻላል። (203.15)

226.1. የቀጠና ጉባኤ ከመሰብሰቡ በፊት ከአገልግሎት ብቃቶች ማረጋገጫ ቦርድ አባላት ሰው ቢጎድል፣ የቀጠና ኃላፊው የሚሾመው ሰው ክፍተቱን ይሞላል። (212)

227. የአገልግሎት ብቃቶች ማረጋገጫ ቦርድ ከተመረጠ በኂላ የቀጠና ኃላፊ እንደሚከተለው ቦርዱን የሚያደራጅ ስብሰባ ይጠራል።

227.1 የቀጠና ኃላፊ በአገልግሎት ደረጃው ቦርዱን ሊቀመንር ይሆናል። ነገር ግን በቀጠናው ኃላፊ ጥያቄ ቦርዱ እስከሚቀጥለው የቀጠና ጉባኤ ፍጻሜ ድረስ የሚሠራ ተጠባባቂ ሊቀመንር ሊመርጥ ይችላል። (213)

227.2. ቦርዱ ከአባላቱ መካል አንድ ፀሐፊ ይመርጣል። ፀሐፊው በቀጠና ጉባኤው ወጪ የቀጠና ጉባኤውን የሪከርድ ሥርዓት ያዘጋጃል። ይህም ሪከርድ የቀጠና ጉባኤው ንብረት ይሆናል። ፀሐፊው ከቦርዱ ተጋራት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ተግባራት በጥንቃቄ የመመዝገብ፣ በታማኛነት የመጠበቅና ለተተኪው አገላጋይ የማስተላለፍ ኃላፊነት አለበት።

**228. የአገልግሎት ብቃቶች ማረጋገጫ ቦርድ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።**

228.1. የሽምግልና፣ የድቁናና ለአገልግሎት ፈቃድ ምርጫ ወደ ቀጠና ጉባኤ የተላለፉትን ሰዎች በጥንቃቄ መመርመርና መገምገም።

228.2. ለየትኞቹም ምድብ የአገልግሎት ተግራት የምስክር ወረቀት የሚፈልጉትን ሰዎች በጥንቃዌ መመርመርና መገምገም። ይህም ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በሲቲያና በመምሪያው ውስጥ የተገለጹትን ሌሎች ልዩ ግንኙነቶች አገልግሎቶች እውቅና የሚፈልጉትን ምእመናን አገልጋይ እጮዎች የሚያጠቃልል ነው።

228.3. ስለ እያንዳንዱ አገልጋይ ግላዊ የደህንነትና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሁለንተናዊ ቅድስና ልምምድ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች እውቀት፣ ጠቅላላ ደንቦችን፣ የክርስቲያናዊ ባሕርይ ቃል ኪዳንና የቤተ ክርስቲያን ፖሊሲ ሙሉ በሙሉ መቀበሉና፣ በሕይወቱም ውስጥ ጸጋዎች፣ ስጦታዎች፣ የአእምሮ፣ ሥነ ምግባርና መንፈሳዊ ብቃቶች መኖራቸውንና እጩው ለተጠራበት አገልግሎት ብቁ መሆኑን በጠንቃቄ መርምሮ ማረጋገጥ።

228.4. እየቀጠለ ከሄደ እጩው አገልጋይ ከጠየቀው አገልግሎት ጋር የማይዛመዱ ባሕርይ እንዳለው ወይም እንደሌለው ለማረጋገጥ፣ የእያንዳንዱ እጩ አገልጋይ ባሕርይ መመርመር።

228.5. ማንኛውም በተጠባበቂ መጋቢነት የተሾመ የአጥቢያ አገልጋይ ከሹመቱ በኂላ ከሚካሄደው የቀጠና ጉባኤ በኂላ አገልግሎቱ እንዲቀጥል ከተፈለገ የዳግም ሹመቱን ጉዳይ መከለስ። (426.6)

228.6. የተሾመ አገልጋይ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ለቀጠና ጉባኤው ሪፖርት በማያደርግት ጊዜ ጉዳዩን ከመረመረና ከከለሰ በኂላ፣ ለቀጠና ጉባኤ አስተያየት መስጠት።

228.7. የቤተ ክርስቲያን አባልነቱን እንደቀየረ ወይም ከሌላ ቤተ እምነት ወይም ቡድን አገልግሎት ጋር እንደተባበረ ወይም በአግባቡ ፈቃድ ሳይሰጠው የግል ተግራትን እንደሚያካሂድ የሚያመለክቱ ሪፖርቶች በቀረቡ ጊዜ፣ ጉዳዩን መመርመረርና በድቁና ወይም በሽምግልና አገልግሎት መቀጠል እንዳለበት ወይም እንደሌለበት በቀጠና ጉባኤ አስተያየት መስጠጥ። (112፣ 435.11)
228.8. ጥያቄ በማቅረቡ ወይም በቦርድ ግምት በአካል ጉዳተኝነቱ (203.9፣ 434-34.2) ወይም በዕድሜው ምክንያት ንቁ አገልግሎት ሊሰጥ እንደማይችል ቦርድ ስለገመተው አገልጋይ ጉዳይ ለቀጠና ጉባኤ የጡረታ ግንኙነት አስተያየት መስጠጥ።
228.9. የክህነት አገልጋዮችና የአገልግሎት ተግባራት ፈቃድ ያላቸው ሰዎች ወደ ሌላ ቀጠና ለመዘዋወር በሚፈልጉበት ጊዜ ለቀጠናው ጉባኤ የድጋፍ ደብዳቤ መጻፍ። ይህም በቀጠና የመማክርት ጉባኤ የፀደቀውብ ጊዜጣዊ ዝውውር ይጨምራል። (203.9፣ 432-34.2)
228.10. የአገልግሎት ብቃቶች ማረጋገጫ ያላቸው የክህነት አገለልጋዮች፣ እንዲሁም ለቀጣይ የአገልግሎት ተግባራት ፈቃድ የተሰጣቸው ሰዎች ወደ ሌሎች ቀጠናዎች ይዛወሩ ዘንድ ለቀጠና ጉባኤ የድጋፍ ደብዳቤ መጻፍ። ይህም በቀጠና የመማክርት ጉባኤ የፀደቀውን ጊዜያዊ ዝውውር ይጨምራል። (203.7፣ 432 — 32.2)

**የቀጠና የአገልግሎት ጥናቶች ቦርድ (229-231.4)**

229. የቀጠና የአገልግሎት ጥናች ቦርድ ተተኪዎች ተመርጠው ብቁ እስኪሆኑ ድረስ ለአራት ዓመታት እንዲያገለግሉ በቀጠና ጉባኤ የተመረጡትን አምስት ወይም ከዚያ በሚበልጡ የተሾሙ አገልጋዮች ያካትታል። ነገር ግን ከአባላቱ የተወሰኑት በየዓመቱ በመተካት የአገልግሎት ጊዜያቸውን መሰባጠር ይቻላል። (203.16)
229.1. የቀጠና ጉባኤ ከመሰባሰቡ በፊት ከቀጠና አገልግሎት ጥናቶች ቦርድ አባላት ሰው ከጎደለ፣ የቀጠና ኃላፊ የሚሾመው ግለሰብ ክፍተቱን ይመላዋል። (212)
230. ቦርድ የተመረጠበት የቀጠና ጉባኤ ከመዘጋቱ በፊት የቀጠና ኃላፊ ወይም የቀጠና ፀሐፊ የቦርዱን አባላት በሙሉ አሰባስቦ የአደረጃጀት ተግባራት እንዲያከናውኑና የአገልግሎት ድርሻቸውን እንዲይዙ ያደርጋል።
230.1. ቦርድ ከአባላቱ መካከል ሊቀመንበር ይመርጣል። በፀሐፊነት የሚመረጠው ግለሰብ የተሾመ አገልጋይ መሆን ይኖርባታል። ጸሐፊፊው ከሌሎች የቦርድ አባላት ጋር በመሆን እጬ አገልጋዮችን መርምሮና በትምህርት ብቁ አድርጎ ለሹመት የማዘጋጀት ኃላፊነት አለው። ለሁሉም ተማሮዎች ቋሙ መዝገብ መያዝ አስፈላጊ ነው። (230.5፣ 426. 1-26.3)
230.2. ሉቀመንበሩ ሌሎች የቦርድ አባላት ለአገልግሎት ዝግጅት ትምህርት የተመዘገቡትን ሰዎች በመከታተሉ ተግር ላይ ድርሻ እንዲኖራቸው ይመድባል። ሌላ የጋራ ስምምነት እስካልተደረሰ ድረስ፣ እንዲህ ዓይነቱ ምዝገባ እጬዎች በኮሚቴ አባሉ የአገልግሎት ገጊዜ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ከሆነ ሳይቋረጥ መቀጠል አለበት።

230.3. ሊቀመንበሩ ከአቅም በላ እስካልሆበት ጊዜ ድረስ በቦርድ ስብሰባዎች ሁሉ ላይ ይገኛለረ፡፡ በየዓቱ የቦርድ ሥራ ይገመግማል፡፡ ሊቀመንሩ ለመቅረት በሚገደድበት ጊዜ ፀሐፊው ሥራውን ይሸፍንለታል፡፡
230.4. ፀሐፊው በቀጠና ጉባኤ ውጪ ለአገልግሎት ጥናቶች ተስማሚ መዝገብ ይገዛል፡፡ ይህም የቀጠና ጉባኤ ንብረት በመሆን፣ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት አገልግሎት ይሰጣል፡፡
239.5. ሌሎች የቦረድ አባላት የቦረድ ስብሰባዎች ላይ በታማኝነት ሊገኙና ለሁሉም እጩዎች (1) ወንድማዊ ማበረታች፣ ምክርና ምሪት በመስጠት፣ (2) በምሳሌያዊነት በማሠልጠንና ስለ ክህነት አገልጋዮች ሥነ ምግባር፣ በተለዩም ወሲባዊ ኃጢአትን እንዴት ሊያስወግዱ እንደሚችሉ ትኩረት ሰጥተው በመወያየት ሊመሯቸውና ሊቆጣጠሯቸው ይገባል፡፡ (230.1.)
230.6 ቦርድ በናዛረሪን ኮሌጅ/ዩኒቨርስቲ ወይም ሰሚናሪ ለመማር የሚፈልጉትን ሰዎች ለማበረታታት፣ ለማገዝና ለመምራት ከቀጠና ኃላፊና ከክህነት አገልግሎት ቢሮ ጋር መተባበር ይኖርበታል፡፡
231. በተለያዩ ትምህርቶች ለመከታተል የሚፈልጉትን ፈቃድ ያላቸውን አገልጋዮች ወይም ሌሎች እጩዎች ለማገዝ ቦረድ የክፍል ውስጥ ትምህርቶችን ወይም ሰሚናረቶችን ሊሰጥ ይችላል፡፡ የቀጠና የመዋለንዋይ ድጋፍ ከተደረገለት፣ አስፈላ በበሚሆንበት ጊዜ በውሰት የሚያገለግል መጽሀፍጽ መክፈት ይችላል፡፡
231.1. የቀጠና የአግልግሎት ጥናቶች ቦረድ ሊቀመንበርና ፀሐፊ ከቀጠና ኃላፊ ጋር በመመካከር ተማሪዎችና ለአገልግሎት ትምህርት የመመዝገብ ሥልጣን አላቸው፡፡ (230.1 — 30.2፣ 426. 1 — 26.3)
231.2. ቦርድ ይፋዊ Source book for ministerial development ጋር በሚስማማ መልኩ ኃላፊነቱን መወጣት አለበት፡፡
231.3. ቦርድ ስለ እያንዳንዱ እጩ የትምህርት ክትትል ለውጥ አስፈላጊ የሆነውን መረጃ ለቀጠና አገገልግሎት ብቃቶች ማረጋገጫ ቦረድ መላክ አለበት፡፡ የመላኪያው ጊዜ ቦረድ ከቀጠና ጉባኤው በፊት መረጃውን እንዲገመግም የሚያስችል መሆን አለበት፡፡ የቀጠና የአገልግሎት ጥናተቶች ቦርድ ስለ ተማሪዎቹ ምደባ፣ ለልቀትና ምረቃ ለቀጠና ጉባኤው ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡ እንዲህ ዓይነት ምደና ፣ ልቀትና ምረቃ በክህነት አገልገልግሎት ቢሮ ከሚሰጠው መምሪያ ጋር መጣጣም አለበት፡፡
231.4. የቀጠና የአግልግሎት ጥናቶች ቦረድ ከክልላዊ ኮሌጅ/ዩንቨርስቲና ይክህነት አገልግሎት ቢሮ ጋር በመተባበር፣ እንዲሁም የቀጠና ኃላፊ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት፣ ለተሾሙ አገልጋዮችና በቀጠናው ውስጥ ለሚገኙ ሌሎች አገልጋዮች እንዴት ከወሲብ ኃጢአት እንደሚርቁ የሚያስገነዝቡ ትምህረቶችን ያካትታል፡፡

**የቀጠና የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙር አገልግሎት ዓለም አቀፍ ቦርድ (237-238.3)**

237. የቀጠና የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙር አገልግሎት ዓለም አቀፍ ቦርድ የቀጠና ናሚዓ ፕሬዚዳንት፣ የቀጠና ናዋዓ ፕሬዚዳንትና የቀጠና ሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎት ቦርድን የቀጠና የሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎቶች

ቦርድ ያካትታል። የቀጠና የሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎች ቦርድ አንድ አሰፈጻሚ ኮሚቴና ቢያንስ ሦስት ተጨማሪ አባላት ይኖሩታል። ተጨማሪ አባላት በቀጠና ጉባኤ ወይም በቀጠና የሰንበት ትምህርት ቤት አገልገግሎቶች ኮንቬንሽን ተመርጠው ተተኪዎቻቸውን ብቁ እስኪሆኑ ድረስ ለተሰባጠሩ የሦስት ተጨማሪ ዓመታት ጊዜ ጣገለግላሉ። የሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎቶች ቦረድ መጀመሪያ በሚያደራጁበት ጊዜ፣ ከስድስት ተጠቋሚዎች ሦስት ተጨማሪ አባላት ይመርጣሉ። ከነዚህ ሦስቱ አንዱ ለአንድ ዓመት ይመረጣል። ነገር ግን የቀጠና አባላት ቁጥር ከ5000 በሚበልጥበት ጊዜ የሚጠቁሙና የሚመረጡ ሰዎች ቁጥር በእጥፍ ሊጨምር ይችላል። ከተቻለ፣ ከአሥሩ የቦርድ አባላት አራቱ ምእመናን መሆን አለባቸው። የቀጠና ጉባኤ የሚሰበሰብበት ጊዜ ከመድረሱ በፊት የሰንበት ትምህርት ቤት አገልጋዮች ቦረድ ውስጥ ክፍተት ቢፈጠር የቀጠና ኃላፊ የሚሾማቸው ሰዎች ክፍተቱን ይሞላሉ። (212)

የቀጠና የሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎቶች ቦር የሚከተሉት ተግባራት ያከናውናል።

237.1. የቦርድ አባላት በተመረጡ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ተሰባስበው ፀሐፊ፣ ገንዘብ ያዥ፣ የአዋቂዎች አገልግሎቶች፣ የልጆች አገልግሎቶችና ተከታታይ የምእመናን ሥልጣና የቀጠና ዳይሬክተሮችን በመምረጥ መደረጃት። እነዚህ ተመራጮች በአገልግሎታቸው ደረጃቸው የሰንበት ትምህርት ቤቶች አገልግሎቶች ቦረድ አባላት ይሆናሉ። ሌሎች የቀጠና ዳይሬክተሮችም እንደ አስፈላጊነቱ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ታጭተው በቦርድ ሊመረጡ ይችላሉ።

237.2. የቀጠና የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎት ጉዳዮችን በሙሉ መቆጣጠር።

237.3. የልጆች አገልግሎቶችን ካውንስል* መምረጥ የዚህ ካውንስል ሊቀመንር የልጆች አገልግሎቶች የቀጠና ዳይሬክተር ሲሆን፣ አባላቱም የልጃገረዶችና የወንዶች ወጣቶች ካምፖች፣ የካሪቢያን፣ ይክረምት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች፣ ይልጆች ቤተ ክርስቲያን፣ Cradll roll parents እና የሌሎችም አስፈላጊ ክፍሎች የቀጠና ዳይሬክተሮች ይሆናሉ።

237.4. የአዋቂዎች አገልግሎቶች ካውንስል* መምረጥ። የዚህ ካውንስል ሊቀመንበር የአዋቂዎች አገልግሎቶች የቀጠና ዳይሬክተር ሲሆን፣ አባላቱ የጋብቻና ቤተሰባዊ ሕይወት፣ ቀዳሚ የአዋቂዎች አገልግሎቶች፣ የላጤ አዋቂዎች አገልግሎቶች፣ የምእመናን መዝናኛ፣ አነስተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች፣ የሴቶች አገልግሎቶች፣ የወንዶች አገልግሎቶችና አስፈላጊ የሆነው አገልግሎት ሁሉ የቀጠና ዳይሬክተሮች ይሆናሉ።

237.5. ለዓመታዊ የቀጠና የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎቶች ኮንቬንሽን ሁኔታዎችን ማመቻቸት። (237)

---

* ስለ ልጆችና አዋቂዎች የአገልግሎቶች ካውንስሎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎቶችን መምሪያ (Sunday school ministries handbook) አንብብ።

* ዚኒ ከማሁ

237.6. የቀጠና ኃላፊ ጋር በመመካከር የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎቶች ቦርድ ሊቀመንበርና አባላት በቀጠና ጉባኤ ወይም በቀጠና የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎቶች ኮንቬንሽን መመረጥ እንዳለባቸው መወሰን።
237.7. የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎቶች ሊቀመነብርትና የዕድሜ ምድብ አገልግሎቶች ዳይሬክተሮች/ የናወዓ ፕረዚዳንቶች በቀጠና የሰንበት ትምህርት ቤትናየደቀመዝሙርነት አገልግሎቶች ኮንቬንሽን ላይ በመገኘት የሚሰጡዋቸውን ተግባራት እንዲያከናውኑ ማበረታታት።
237.8. ቀጠናዎችን በዞኖች ማደራጀትና ቦርድ በቀጠናው ውስጥ የሰንበት ትምህርት ቤትናየደቀመዝሙርነት አገልግሎቶች ለማካሄድ የሚያደርገውን ጥረት የሚያግዙ ሊቀመናብርትን መሾም።
237.9. የቀጠና ወይም የዞን ተከታታይ የምእመናን ሥልጠናዎችን ማቀድና ተግባራዊ ማድረግ።
237.10. የቀጠናና የአጥቢያ የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎቶች ጉዳዮች የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎቶች ክፍል ማገዝ።
237.11. ስለ ቀጠናው የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎቶች ቦረድ ዓመታዊ በጀት ለቀጠና ጉባኤ የመዋለንዋይ ኮሚቴ የድጋፍ አስተያየት መስጠት።
237.12. ለቀጠና የምእመናን መዝናኛ ኃላፊነት መውሰድ። የቀጠና አዋቂዎች አገልግሎቶች ዳይሬክተር በአገልግሎት ደረጃው የቀጠና የምእመናን መዝናኛ ኮሚቴ አባል ይሆናል።
237.13. የሊቀመንበሩ ሪፖርት ለቀጠና ጉባኤ እንዲቀርብ ማጽደቅ።
237.14. የቀጠና ኃላፊው ወይም የቀጠን የሰንበት ትምህርት ቤትናየደቀመዝሙርነት አገልግሎቶች ቦርድ ሊቀመንበር አስፈላጊ ነው ተብሎ በሚያስበው መሠረት የቦርዱን ኃላፊነቶች ለማቀድና ተግባራዊ ለማድረግ መሰባሰብ።
238. የቀጠና የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎቶች ሊቀመንበር። የቀጠና ጉባኤ ወይም የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎቶች ኮንሸንሽን የቀጠና ጠቋሙ ኮሚቴ ከሚያቀርባቸው ሁለት ወይም አንድ እጩዎች አንዱን የቀጠና የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎቶች ቦርድ ሊቀመንበር ሆኖ ለአንድ ወይም ለሁት ዓመታት እንዲሠራ ይመርጠዋል። አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ ሊቀመንር የቀጠና ኃላፊ በሚያፀድቀው መሠረት ‹‹አዎ›› ወይም ‹‹አይደለም›› በሚል ድምፅ እንደገና ሊመረጥ ይችላል። የቀጠና ጉባኤ የሚሰበሰብበት ጊዜ ከመድረሱ በፊት የሚፈጠር ክፍተት በአንቀጽ 212 መሠረት ይሞላል። (237.6)
የቀጠና የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎቶች ሊቀመንበር የሚከተሉት ተግባራትና ሥልጣናት ይኖሩታል።
238.1. የሰዎችን የምዝገባና የክትትል ዕድገት በመጨመር፣ የልጆችና የአዋቂዎች አገልግሎቶችን ፕሮግራሞች ሁሉ በማስተባበር የወጣቶችን የሰንበት ትምህርት ቤት ለማስተባበር ከናወዓ ጋር በመተባበር ለቀጠናው የሰንበት ትምህርት ኃላፊነት

የሚስማው አመራር መስጠት።
238.2. በአገልግሎት ደረጃው የቀጠና ጉባኤና የቀጠና የሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎቶች ቦረድ አባል መሆን።
238.3. በየወሩ ለጠቅላላ ቦረድ የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎቶች ክፍል ትክክለኛ የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት አገልግሎቶች አሃዛዊ መረጃ መስጠትና ለቀጠና የሰንበት ትምህርት ቤትናየደቀመዝሙርነት አገልግሎቶች ቦርድ ለዓመታዊ ጉባኤ ጆርናል የጽሑፍ ሪፖርት ማዘጋጀት።

## General Assembly

The General Assembly is the most important meeting of the Church of the Nazarene. It has authority to formulate doctrine and make laws governing the church world - wide. The General Superintendents are the chairmen of the General Assembly.
The members of the General Assembly are (301):

1. The delegates elected by the regular districts (Phase 3), half, will be laymen and half will be elders.

| Membership | Elders | Laymen |
|---|---|---|
| 1 - 2000 | 1 (DS) | 1 |
| 2001 - 5500 | DS + 1 | 2 |
| 5501 – 9000 | DS + 2 | 3 |

2. A Phase 2 district may send the district superintendent and one layman to the General Assembly.
3. A Phase 1 district may send the district superintendent to General Assembly but the district superintendent will not have a vote.
4. All general superintendents.
5. The general secretary.
6. The general treasurer.
7. The editor of Holiness Today.
8. General NYI president,
9. General NMI president.
10. Regional directors.

## Time of Meeting (302)

The General Assembly will be held in June every four years, for

example, 2009, 2013, 2017 etc.

**The Work of the General Assembly (305)**

1. Elect 6 general superintendents by a 2/3 vote.
2. Elect the members of the General Board.

Districts may send in resolutions concerning changes they want made to the Manual or constitution. These resolutions will be sent to committees of the General Assembly for discussion. These committees will then make recommendations either for or against which will be sent to the General Assembly, which will then discuss it further and then vote on it. This is the way in which the Manual of the church can be changed or modified.

**ጠቅላላ ኃላፊዎች (306-307.14)**

306.ጠቅላላ ጉባኤ የሚመርጣቸው ጠቅላላ ኃላፊዎች የሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤ ከሚያበቃበት ጊዜ በኋላ እስከ 30 ቀናትና ተተኪዎቻቸው ተመርጠው ብቁ እስኪሆኑ ድረስ ያገለግላሉ። (305.2)

3006.1. አንድ ጠቅላላ ኃላፊ ይህንን አገልግሎት እያካሄደ ባለበት ወቅት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሌላ የጠቅላላ አገልግሎት ሊይዝ አይችልም። (307.11)

306.2. የጠቅላላ ኃላፊዎች በአገልግሎት ደረጃቸው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ይሆናሉ።

307. **የጠቅላላ ኃላፊዎች ተግባራትና ሥልጣናት የሚከተሉት ናቸው።**

307.1. የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ራዕይ በግልጽ መንደፍ።

307.2. ጠቅላላ ጉባኤ በሚደነግገው ሕግና ደንብ መሠረት የናዛሪንን ቤተ ክርስተቲያን በአጠቃላይ መቆጣጠር።

307.3. በናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባኤና ጠቅላላ ቦርድ ላይ በጋራና በህብረት በሊቀመንበርነት ማገልገል። (300.1፣ 333.5)

307.4. ለሽምግልና ወይም ነድቁና በአግባቡ የተመረጡትን ሰዎች መሾም ወይም ካሉት የተሾሙ አገልጋዮች ጋር በተያየዘ ሌሎች እንዲሾሚቸው ማድረግ። (433.5-33.6)

307.5. በእያንዳንዱ ደረጃ 3 የቀጠና ጉባኤ ላይ በሊቀመንበርነት ማገልገል፣ ወይም ይህንን ከማድረግ ከተከለኩት ለዚህ ተግባር ሁኔታዎች ማመቻቸት። (202፣ 211)

307.6. በቀጠና ጉባኤ በቀጠና ኃላፊና በቀጠና የመማክርት ጉባኤ ላይ ከአጥቢያ አብያተክርስቲያናት ልዑካን ጋር በአመራርነት የሚሠራ ጠቅላላ ኃላፊ፣ መጋቢዎችን ላልጠሩት አብያተ ክርስቲያን መጋቢዎች ይሾማል። (214.1)

307.7. የቀጠና ጉባኤ የሚካሄድት ወቅት ከመድረሱ በፊት ክፍተቶች በሚፈጠሩበት ጊዜ ከቀጠና የመማክርት ቦርድ፣ ከቀጠና የሰንበት ትምህርት አገልግሎቶች ሊቀመንበር፣ ከቀጠና የናሚዓና የናወዓ ፕሬዜዳቶች፣ ከቀጠና ጸሐፊና ከቀጠና ገንዘብ ያዥ የተወጣጡ አባላት ከሚገኙበት ኮሚቴ ጋር በመመካከር፣ የቀጠና ኃላፊዎች መሾም። (207)

307.8. የቀጠና ኃላፉ ለጊዜው በሚታገደብት ጊዜ፣ በሥልጣን ላይ ያለው ቅላላ ኃላፉ ከቀጠና የመማክርት ቦርድ ጋር በመመካከር ብቃት ያለው ጊዜያዊ የቀጠና ኃላፊ ይሾማል። እገዳው ተግባራዊ የሚሆነው በሥልጣን ላይ ባለው ጠቅላላ ኃላፊና በቀጠና የመማካርት ቦርድ ውሳኔ ይሆናል። (207.2)

307.9. በሥልጣን ላይ ያለው ጠቅላላ ለጠቅላላ ቦርድ ደረጃ 3 ላይ ያለ ቀጠና

ችግር ውስጥ መሆኑን መግለጽ ይችላል (200.2፣ 322)
307.10. በሥልጣን ላይ ያለው ጠቅላላ ኃላፉ በዓመታዊ ወይም በበልዩ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ላይ በሊቀመንበርነት ያገለግላል ወይም ይህንኑ ተግር የሚያከናውን ተወካይ ይሾማል፡፡ (113.5)
307.11. ጠቅላላ ኃላፊቶች የየትኛውም የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ቦርዶች አባላት ሊሆኑ አይችሉም፡፡ (306.1)
307.12. ጠቅላላ ጉባኤ የጠቅላላ ኃላፊዎች ይፋዊ ተግባራት በሙሉ ይከከልሳል፡፡
307.13. የየትኛው የጠቅላላ ኃላፊ ይፋዊ ተግባር በበተቀሩት የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ አባላት አንድ ዓይነት ድምጽ ውድቅ ሊሆን ይችላል፡፡
307.14. የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦረድ አባላት አንድ ዓይነት ድምጽ ከሰጡና የደረጃ 3 እና የደረጃ 2 የቀጠና ኃላፊዎች በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ከጸሸማሙ፣ ማንኛም ጠቅላላ ኃላፊ ከሥልጣኑ ሊነሣ ይችላል፡፡

**የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ (315-324)**
315. ጠቅላላ ኃላፊዎች እንደ ቦረድ የተደራጅተው አባላቱ ልዩ ኃላፊነት የሚያከናውኑባቸው ሥራዎችን ይመድባሉ፡፡
316. **ክፍተት፡፡** በጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ ውስጥ ቦትም ሆነ በሌሎች ምክንያቶች ክፍተት ከተፈጠረ፣ ክፍተቱን ለመሙላት የሚያስችል ምርጫ የማካሄዱ ጥያቄ በጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ ይወሰናል፡፡ የምርጫ ጥሪ በሚደረገግበት ጊዜ፣ የጠቅላላ ቦረድ ኃላፊዎች በሁለት ሦስጣነ ድምጽ የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ የሆነ ሰው መርጦ ክፍተቱን ይሞላል፡፡ የተመረጠው ጠቅላላ ኃላፊ ቀጣዩ ጠቅላላ ጉባኤ እስሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ ሲያገልግል ይቆያል፡፡ (31.5፣ 305.2)
316.1. ጠቅላላ ጸሐፊ የምርጫውን ውጤት ለጠቅላላ ኃላፊዎች ቦረድ ሪፖርት ያደርጋል፡፡ ቦረዱም ይህንኑ ውጤት በቅድስና ዛሬ (Holiness Today) አማካኝነት ለናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ያሳውቃል፡፡
317. **የጠቅላላ ኃላፊዎች ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡**
317.1. ዓምአቀፋዊት የናዛሪን ቤተ ክርስቲያንን መቆጣጠር፡፡ የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦረድ የአብያተ ክርስቲያናትን አመራር፣ ምሪት፣ መነሣሣትና ወደ ደረጃ 3 ቀጠናዎች ማለፍ በትኩረት ይከታተላል፡፡
317.2. ከዓለም ሚሲዮን/ወንጌል ስርጭት ክፍል ዳይሬክተር፣ ከአገሩ ብሄራዊ የአስተዳደር ዳይሬክተሮች እና/ወይም ክልላዊ ዳይሬክተሮች ጋር በመመካር፣ አገልጋዮችን በተለያዩ መልከዓ ምድራዊ አከባቢዎች እንዲሠሩ ድጋፍ መስጠት፡፡ ይህም የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦረድና ጠቅላላ ቦረድ በሚያጸድቀው መሠረት ተግባራዊ ይሆናል፡፡
317.3. ጠቅላላ ቦረዶችን የጠቅላላ ቦረድ ኮሚቴዎች መቆጣጠር፡፡ አንድ ቦርድ ወይም ኮሚቴ የሚያወጣቸውን ዕቅዶች ፖሊሲዎች በጠቅላላ ኃላፊዎች ቦረድ መጽደቅ አለባቸው፡፡ የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦረድ ለጠቅላላ ቦረድና ለኮሚቴዎች ጠቃሚ የሆኑ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡ የዓልም የሚሲዮን/የወንጌል ስርጨችት ኮሚቴ የናዛሪን ቤ ክርስያን ጠቅላላ ቦረድ ሚሲዮናዊያንን እንዲሾምየሚያቀርበውን ጥያቄ ሊያጸድቅ ወይም ውድቅ ሊያደረግ ይችላል፡፡
317.4 ከጠቅላላ ቦርድ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጋ በመተባበር እንደ እጩ

አቅራቢ ኮሚቴ ያገለግላል። በዚህ ለጠቅላላ ጸሐፊነትና ለጠቅላላ ገንዘብ ያዥነት የሚመረጡትን ሰዎች በእጩነት ያቀርባል።
317.5. ከአባላቱ በሁለት ሦስተኛው ድምጽ የጠቅላላ ጸሐፊን፣ የጠቅላላ ገንዘብ ያዥን፣ የቅድስና ዛሬን አዘጋጅ፣ የናዛሪን አሳታሚ ድርጅት ፕሬዜዳንትን ወይም የአገልግሎት ክፍል ዳይሬክተርን ከአገልግሎት መነሣት ያሳውቃል።
317.6. ጠቅላላ ጉባኤ ከመካሄዱ በፊት ከጠቅላላ ችሎት ውስጥ የሚጎድሉትን አባላት ማሟላት፣ ይችሎትን ሊቀመንበርና ጸሐፊ መምረጥ። (305.7፣ 511፣ 901.2)
317.7. ጠቅላላ ጉባኤ ወይም ጠቅላላ ቦረድ የሚሰባሰብበት ጊዜ ከመድረሱ በፊት በየትኛውም ልዩ ኮሚሽን ወይም ኮሚቴ ውስጥ የሚፈጠረውን ክፍተት መሙላት።
317.8. የናዛሪን ቤተ ክርስቲያ ቦርድ ከአባላቱ መካል የጎደሉትን ለመተካት የሚያካሂዳቸውን ሹመቶችና ምርጫዎች ማጽደቅ።
317.9. ቀሪ አባላቱ በሚያቀርቡት ጥቆማ መሠረት በናዛሪን አሳታሚ ድርጅት ኮርፖሬት ቦረድ ውስጥ የሚከሰተውን ክፍተት መሙላት። (338)
317.10. ከዓለምአቀፍ የትምህርት ቦርድ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የከፍተኛ ትምህት ተቋማት በማማከርና የጠቅላላ ቦረድ የአገልግሎት ክፍሎች ሁሉ ተጠሪ ጠቅላላ ኃላፊዎች ሆነው የሚያገለግሉትን ጠቅላላ ኃላፊዎች መሾም። (901.5)
317.11. ከክህነት አገልግሎቶች ጋር በመተባበር ለአጥያ አገልጋዮች፣ ፈቃድ ላላቸው አገልጋዮችና በምእመን ሆነ የአገልግሎት ብቃትን በሚጠይቁ የአገልግሎት ተግባራት ላይ ለሚሳተፉ ሰዎች የትምህርት ዕድሎችን ማመቻቸት። (426 — 27)
317.12. ዓለምአቀፍ የሚሲዮን አገልግሎቶችንን ለማቀድ፣ ለመጠበቅና ለማስፋፋት፣ የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦረድ ከጠቅላላ ቦረድ ጋር በመተባበር የዓለም የወንጌል ስርጭት መወለንዋይ ለአያሌ የጉባኤ ቀጠናዎች የማደላደል ሥልጣን አለው። (38.5፣ 130፣ 335.8)
317.13. ቀደም ሲል በሽምግልና ወይም በድቁና ያገለግል ለነበረ ሰው የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫዎቹ መመለሳቸውን በጽሑፍ ማረጋገጥ። (436.7፣ 4337.2)
318. የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ የናዛሪን ቤተ ክርስቲያንን ሕግና አስተምህሮ እንዲሁም የመምሪያውን ደንቦች ፍችና ኃይል የመተርጎም ሥልጣን አለው። ይህ ሥልጣን በጠቅላላ ጉባኤ ይግበባኝ ማለትን አይከለክልም።
319. የጠቅላላ ኃላፊቸ ቦርድ የቀጠና ማዕከላትን ዕቅዶች ገምግሞ ያስተላልፋል። ዝነዚህ ዕቅዶች ከጠቅላላ ኃላፊዎች ቦረድ የጽሑፍ ድጋፍ እስካልተሰጣቸው ድረስ ተግባራዊ ሊሆኑ አይችሉም። (222.9)
320. የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ ከትዳር የተፋቱትን ሰዎች በናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሽምግልና ወይም ለድቁና ለመሾም ሊወስን ይችላል። (35.1-35.3፣ 430.3፣ 431.3)
321. የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ ሥልጣን ያለው ጠቅላላ ኃላፊ በሚሰጠው ድጋፍ መሠረት ማንኛውንም የደረጃ 1 ወይም ደረጃ 2 የቀጠና ኃላፊ ከአገልግሎት ሊቀመንበሮች፣ የቀጠና ናወዓ፣ የቀጠና ናሚዓ፣ የቀጠና ፀሐፊና የቀጠና ገንዘብ

ያኸ በሚሰጡት ሁለት ሦስተኛ ድምፅ ደረጃ 3 የቀጠና ኃላፊ ከአገልግሎቱ ሊያነሣ ይችላል፡፡ (207.2)
322. የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ ደረጃ 3 ላይቸ ያለ ቀጠና ችግር ውስጥ እንደሆነ ልያውጅ ይችላል፡፡ (200.2፣ 307.9)
323. ከእያንዳንዱ የጠቅላላ ጉባኤ በኋላ የተሻሻለው የናዛሪን ቤተ ክርስቲያ መመሪያ በሁሉም ቋንቋዎች ተግባራዊ የሚሆነው የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ Holiness Today በተባለው መጽሔት ላይ ኦፌሴላዊ የሕትመት ማስታወቂያ ስያወጡና በናዛሪን ኮሚንኬሽን የዜና ላይ ስወጣ ነው፡፡
324. የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦረድ ሌላ መግለጫ እስካልተሰጠው ድረስ፣ ከአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓ ጋር በመስማማትና ለቤተ ክርስቲያን የመተዳደሪያ ደንብ በበመግዛት በናዛሪን ቤተ ክርስቲያ ውስጥ ማንኛውንም ተግባር የመፈጸም ሥልጣን አለው፡፡

**ጠቅላላ ፀሐፊ (325-328.1)**
325. የጠቅላላ ቦርድ ደንቦች በሚፈቅዱት መሠረት በጠቅላላ ቦረድ የተመረጠው ጠቅላላ ፀሐፊ እስከሚቀጥለው የጠቅላላ ጉባኤ ፍጻሜ፣ ተተኪው ተመርጦ ብቁ እስኪሆን ወይም በአንቀጽ 317.5 መሠረት ከአገልግሎት እስከሚነሣበት ጊዜ ድረስ ይሠራል፡፡ (900.23)
325.1. የጠቅላላ ፀሐፊ በአገልግሎት ደረጃው የጠቅላላ ጉባኤ አባል ይሆናል፡፡ (301)
325.2. ጠቅላላ ጉባኤ የሚካሄድበት ጊዜ ከመድረሱ በፊት በማንኛውም ምክንያት ጠቅላላ ፀሐፊ ከአገልግሎቱ ቢነሣ፣ በአንቀጽ 317.4 በተገለጸው መሠረት እጩዎቹን የማቅረብ ሂደት በጠቅላላ ቦርድ ይሟላል፡፡ (335.22)
325.3. ጠቅላላ ኃላፊ ለጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድና ለጠቅላላ ቦርድ ተጠያቂ ይሆናል፡፡
326. **የጠቅላላ ፀሐፊ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡**
326.1. የጠቅላላ ጉባኤንና የጠቅላላ ቦርድን ስብሰባዎች ጆርናል በትክክል መመዝገብና መጠበቅ፡፡
326.2. የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን አሃዛዊ መረጃዎች ሁሉ በትክክል መመዝገብ መጠበቅ፡፡
326.3. የጠቅላላ ጉባኤ ሰነዶች ሁሉ መጠበቅና ለተተኪው በአግባቡ ማስተላለፍ፡፡
326.4. በጠቅላላ ችሎት የተሰጡትን ውሳኔዎች ሁሉ በጥንቃቄ ጠብቆ ማቆየት፡፡ (513)
326.5. ፋይል የተደረጉ፣ የተተው፣ የተነሡና የለቀቁ አገልጋዮችን የአገልግሎት ብቃት በማረጋገጫዎች ማስቀመጥና መጠበቅ፣ የተገኙበት የቀጠና ጉባኤ በሚሰጠው ተገቢ ትእዛዝ ብቻ መመለስ፡፡ (436-36.1፣ 436.6)
326.6. የቀጠና ጉባኤ የአሀዛዊ መረጃ ሠንጠረዦችን ለህትመት ኦዲት ማድረግ፡፡ (217.3)
326.7. የቀጠና የአገልግሎት ፈቃድ የተሰጣቸው አገልጋዮች ቋሚ ሰነድ መጠበቅ፡፡
326.8. የጠቅላላ ጉባኤውን ቃለ ጉባኤ ማዘጋጀትና በሚያስፈልግ ጊዜ በቀጠና፣

በዓላም አቀፍ ሚሲዮን የአከባቢ፣ የክልል ቢሮ ስጠየቅ ማቅረብ፡፡ ይህ በዲጂታል መንገድ ልሠራ ይችላል፡፡

326.9. የቤተ ክርስቲያኒቱን የተሻሻለ መምሪያ http://www.nazarene.org ሰዎች ማግኘት የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት፡፡

326.10. ተግባሩን በአግባቡ ለማከናወን አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ በታማኝነት መፈጸም፡፡

327. ጠቅላላ ፀሐፊ የጠቅላላ ንብረት የሆኑ ሰነዶችን በባለአደራተን ይጠብቃል፡፡

327.1. ጠቅላላ ፀሐፊ ከቤተ እምነታቸችን አካሄስን አስተዳዳግ ጋር የተያያዙትን ታሪካዊ ጽሑፎች የመሰብሰብና በባለአደራነት የመጠበቅ ሥልጣን አለው፡፡

327.2. ጠቅላላ ፀሐፊ በአንቀጽ 902.10 መሠረት ታሪካዊ ቦታዎችንና አከባቢዎችን መመዝገብ በመመዝገብ ይጠብቃል፡፡

328. ጠቅላላ ፀሐፊ ከጠቅላላ ኃላፊዎች ጋር በመተባበር ጠቅላላ ጉባኤ ከመከፈቱ በፊት አስፈላጊ የሆኑትን ቅጾችን በሙሉ ያዘጋጃል፡፡ ከነዚህ መካል ‹‹መመሪያው›› ለክለሳ አጠር ብሎ የሚቀርብላቸው የሥርዓት ደንቦች (Rules of Order #Manual$ Abridgment) እና ጠቅላላ ጉባኤውን ተግባር ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች ይገኙበቸዋል፡፡ ለዚህ ሥራ የሚወጣው ወጪ ከጠቅላላ ጉባኤ የወጪ ገንዘብ ይወሰዳል፡፡

328.1. ጠቅላላ ፀሐፊ ጠቅላላ ጉባኤ በሚመርጠው ወይም ጉባኤው ከመሰብሰቡ በፊት የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦረድ በሚሾመው መሠረት ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ረዳቶች ይኖሩታል፡፡

**ጠቅላላ ገንዘብ ያዥ (329-330.7)**

329. ጠቅላላ ገንዘብ ያዥ በጠቅላላ ቦረድ የጠቅላላ ቦርድ ደንብ በሚፈቅደው መሠረት በመመረጥ እስከሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤ ድረስ ያገለግላል እንዲሁም ተተኪው ብቁ እስኪሆን ወይም በአንቀጽ 317.5 መሠረት ከአገልግሎቱ እስክነሳ ድረስ ያገለግላል፡፡ (900.3)

329.1. ጠቅላላ ገንዘብ ያዥ በአገልግሎት ደረጃው የጠቅላላ ጉባኤ አባል ይሆናል፡፡ (301)

329.2. ጠቅላላ ገንዘብ ያዥ ለዋና ጽ/ቤት የመዋለንዋይ ቢሮ ጠቅላላ ኃላፊ፣ ለጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድና ለጠቅላላ ቦረድ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

330. **የጠቅላላ ገንዘብ ያዥ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡**

330.የናዛሪን ቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ በባለአደረራነት መጠበቅ፡፡

330.2. የዓለምአቀፍ ሚሲዮን/የወንጌል ስርጭት ኮሚቴ፣ የመዋለንዋይ ኮሚቴ፣ የሰንበት ትምህርት ቤትና የደቀመዝሙርነት አገልገግሎቶች ኮሚቴ፣ የዓልም ሚሲዮን/የወንጌል ስርጭት ኮሚቴና ሌሎች የጠቅላላ ቦርድ ወይም የየትኞቹም የአግልግሎት ክፍሎች ንብረት የሆነውን ገንዘብ በትእዛዝ መቀበልና መክፈል፡፡ ይህም የጠቅላላ ኃላፊፊን፣ የድንገተኛ የጠቅላላ ጉባኤን ወጭ፣ ሌሎች የቤተ ክርስቲያን የርዳታ ገንዘቦችና ጠቅላላ ናዛሪን ሚሲዮን ዓለምአቀፍ ገንዘቦችን ይጨምራል፡፡ (331.3.)

330.3. ጠቅላላ ቦርድ በሚመራው መሠረት ተግባረራቸውን በታማኝነት ለሚፈጽሙ አገልጋዮች በመልካም የኢንሹራንስ ካምፓኒ አማካኝነት በቂ ገንዘብ

መክፈል፡፡
330.4. ገንዘባቸውን  በአደራ እንዲጠብቁ የሰጡት ቦርዶችና የአገልግሎት ክፍሎች በሚጠይቁት ጊዜ ሪፖርቶችን ማቅረብ፡፡
330.5. ኢንቨስትመንቶችን ጨምሮ ስለ ሁሉም የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ለጠቅላላ ጉባኤ ዓመታዊ ሪፖርት ማቅረብ፡፡ (335.13)
330.6. በትክክለኛው የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች ለቋሚ ሀብት የዋለውን መዋለንዋይ መጠበቅና፣ ፖሊሲዎች እንዳይጣሱ መከላከል፡፡

330.7. ከሁሉም የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤቶች፣ ዕጓለማውታዎች፣ የእንክብካቤ ቦታዎችና ሌሎች ተቋማት ወርሃዊ የገቢና ወጪ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት፡፡

**ጠቅላላ ቦርድ (331-336)**

331. በሚዞሪ ማህበራት ማደራጃ ደንቦች መሠረት በካንሳስ ዩኤስኤ ሃይማኖታዊና ለእርዳታ ድርጅት ሆነ የተቋቋመው የናዛሪን ቤተ ክርስቲያም ጠቅላላ ቦርድ በአንቀጽ 332.1 — 33.4 መሠረት ከቀረቡት እጩወች ጠቅላላ ጉባኤ በድምፅ ብልጫ የሚመርጣቸው አባላት የሚካተቱበት ነው፡፡ አንድ ሰው የቤተ ክርስቲያን ክልል ወኪል ሆነ በጠቅላላ ቦርድ አባልነት ሊመረጥ የሚችለው የዚያው ክልል ነዋሪና በክልሉ ውስጥ የምትገኝ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ሲሆን ነው፡፡ (305.6፣ 334)

331.1. የጠቅላላ ቦርድ ወይም አካላት (ጠቅላላ ቦርድ የሚቆጣጠራቸው የትምህርት ተቋማት ጨምሮ) ሠረተኛ የሆነ ማንኛውም ግለሰብ የጠቅላላ ቦርድ አባል ሆኖ ሊረጥ ወይም የጠቅላላ ቦርድ አባል ሆኖ ማገልገሉን ሊቀጥል አይችልም፡፡ ከጠቅላላ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ማስኪያጃ ገንዘብ የሚቀበሉ የቀጠና ወይም የሌሎች አካላት ግለሰቦች ለዚህ ምርጫ ብቁዎች ሊሆኑ አይችሉም፡፡

331.2. **ጠቅላላ ፀሐፊ በአገልግሎት ደረጃው የጠቅላላ ቦርድ ፀሐፊ ይሆናል፡፡**

331.3. የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ገንዘብ ያዥ በአገልግሎት ደረጃው የቤተ ክርስቲያን ቦርድና የአገልግሎት ክፍሎች ገንዘብ ያዥ ይሆናል፡፡ (330.2)

**332. አባላት ለጠቅላላ ቦረድ በእጩነት የሚቀርቡት በሚከተሉት መንገድ ይሆናል፡፡**

332.1. በጠቅላላ ጉባኤ ላይ የሚገኙ ልዑካም ከተመረጡ በኋላ እያንዳነንዱ ደረጃ 3 ቀጠና ልዑካንን ለጠቅላላ ቦረድ እጩነት ለመምረጥ በሚከተሉት ሁኔታ ይሰበሰባል፡፡ እያንዳንዱ ደረጃ 3 ቀጠና የሦስት የተሾሙ አገልጋዮችንና የሁለት ምእመናንን ስም ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ሰዎችን ለእጩነት በመምረጡ ረገድ የመራጭ ቀጠና ብዝሃ ባህላዊ ስብጥር ከግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት፡፡ ክልላዊ የመማክርት ካውንስል ላላቸው አገሮች፣ የነዚህ እጩዎች ስም መጀመሪያ ወደ ብሔራዊ ቦርድ ከዚያም ወደ ክልላዎ የመማክርት ካውንስል ላላቸው ይላካል፡፡ ክልላዊ የመማክርት ካውንስል የመሪዎች ጉባኤ ድምፅ መስጠት ሳለበት ለእያንዳንዱ አባል የስሞቹን ቁጥር ወደ ሦስት ሊቀንስ ይችላል፡፡ ከዚያ በኋላ ስሞቹ ከእያንዳንዱን ክልል ለመጡ የጠቅላላ ጉባኤ ልዑካን በሚቀርቡበት የምርጫ ወረቀት ውስጥ ይካተቱ ዘንድ በአስቸኳይ ለጠቅላላ ፀሐፊ ይልካሉ፡፡

(203.23)

323.2. ከነዚህ እጩዎች ዝርዝር የጠቅላላ ጉባኤ ልዑካን በሚከተለው ሁኔታ ለጠቅላላ ጉባኤ እጩዎችን ያቀርባሉ፡፡

100,000 ወይም ከዚያ የሚያንስ ሙሉ አባላት ያሉበት ክልል አንድ የተሾመ አገልጋይና አንድ ምእመን በእጩነት ያቀርባሉ፡፡ ከ100,000 እስከ 200,000 ሙሉ አባላት ያሉት ክልል አንድ የተሾመ አገልጋይ፣ አንድ የቀጠና ኃላፊና አንድ መጋቢ ወይም ወንጌላዊ እንዲሁም ሁለት ምእመናን በእጩነት ያቀርባል፡፡ ከ200,000 በላይ ሙሉ አባላት ያሉት ክልል በሚከተለው ሁኔታ አንድ ተጨማሪ ምእመንና አንድ ተጨማሪ የተሾመ አገልጋይ በእጩነት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

1.ከ200,000 በላይ ሙሉ አባላት ያሉባቸው ክልለሎቸ ከሚያቀርቧቸው እጩዎች መካከል አንድ የተሾመ አገልጋይ መጋቢ ወይም ወንጌላዊ ወይም የቀጠና ኃላፊ ሊሆን ይችላል፡፡

2.ማንኛውም ቀጠና በጠቅላላ ቦርድ ውስጥ ከሁለት የሚበልጡ አባላት ሊሰየም አይችልም፡፡ የትኛውም ክልል ከስድስት የሚበልጡ አባላት (የተቋማት ተወካዮችን ረዳት አባላት ሳይጨምር) ሊሰይም አይችልም፡፡ ከአንድ ቀጠና ውስጥ ከሁለት የሚበልጡ እጩዎች በተመሳሳይ ክልል ውስጥ ከሚገኘው ሌላ ቀጠና የበለጠ ድምፅ በሚያገኙበት ጊዜ በሁለተኛ ደረጃ ከፍተኛውን ድምፅ የሚያገኛው ቀጠና እጩዎች የክልሉ እጩዎች ሆነው የይመረጣሉ፡፡ (305.6፣ 901.1)

3.በእያንዳንዱ ቀጠና በየምድባቸው የበለጠ ድምፅ የሚያገኙ ምእመናን መጋቢ ወይም ወንጌላዊ እና/ወይም የቀጠና ኃላፊ በአብላጫ ድምፅ ለጠቅላላ ጉባኤ ይታጫሉ፡፡ ስድስት አባላት በሚመረጡባቸው ታላላቅ ክልሎች፣ በሁለተኛ ደረጃ ከፍተኛ ድምፅ የሚያገኘው ምእመንና የተሾ አገልጋይ ተጨማሪ እጩዎች ይሆናሉ፡፡ (902.8)

4. የክልል አማካሪ ካውንስል ተመረጭ ተወካዮች ጠቅላላ ጉባኤውን ለመካፈል የማይችሉ መሆን አስቀድሞ ካወቀ ጠቅላላ ጉባኤው ከመጀመሩ ከስድስት ወራት በፊት ድምፅ በፖስታ ወይም በኢንተርነት አማካኝነት ደምፅ መስጠት ይችላሉ፡፡ ይህ በፖስታ ወይም በኢንትርነት አማካኝተት የሚደረግ ለጠቅላላ ጉባኤ ጠቅላላ ቦርድ የመምረጥ ስርዓት በመጀመሪያ በክልል አማካሪ ቦርድ በኩል ለጠቅላላ ፀሐፊ ቀርቦ በመጀመሪያ መጽደቅ አለበት፡፡

332.3. ዓለምአቀፍ የትምህርት ቦርድ (ዓትቦ) ሁለት የተሾሙ አገልጋዮችንና ሁል ምእመናንን ለጠቅላላ ጉባኤ በእጩነት ያቀርባል፡፡ (331.1)

332.4. የናዛሪን ወጣቶች ዓለምአቀፍ ዓለምአቀፋዊ ካውንስል ለጠቅላላ ጉባኤ ሁ፤ት የዓለምአቀፍ የናወዓ ካውንስል አባላትን በእጩበት ያቀርባል፡፡ (342.4)

332.5. የናዛሪን ሚሲዮን ዓለምአቀፍ ጠቅላላ ካውንስል ለጠቅላላ ጉባኤ ሁለት አባላትን በእጩነት ያቀርባል፡፡ (343.3)

**333. የጠቅላላ ቦርድ አባላት በሚከተለው ሁኔታ ይመረጣሉ፡፡**

333.1. ከተለያዩ ክልሎች የቀረቡት እጩዎች ‹‹አዎን›› በሚል አብላጫ ድምፅ

ይመረጣሉ። (902.8)
333.2. ዓለምአቀፍ የትምህርት ቦርድ ካቀረባቸው እጩዎች ጠቅላላ ጉባኤ አንድ የተሾመ አገልጋይና አንድ ምእመን ይመርጣል።
333.3. የናዛሬን ወጣቶች ዓለምአቀፍ ካውንስል ካቀረባቸው እጩዎች ጠቅላላ ጉባኤ አንዱን ይመርጣል። (342.4፣ 901.3)
333.4. የናዛሬን ሚሲዮን ዓለምአቀፍ ጠቅላላ ካውንስል ካቀረባቸው እጩዎች ጉባኤው አንዱን ይመርጣል። (343.3፣ 901.3)
334. የጠቅላላ ቦርድ አባላት የሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤ እስከሚጠናቀቅና ተተኪዎቻቸው ተመርጠው ብቁ እስከሚሆኑ ድረስ ሲያገለግሉ ይቆያሉ። አንድ የጠቅላላ ቦርድ አባል ከሚወክለው ክልል ቢለቅ ወይም የቤተ ክርስቲያን አባልነቱን ቢቀይር ወይም ከቀጣዩ የጠቅላላ ጉባኤ በፊት የተመረጡትን የአገልግሎት ምድብ ቢቀይር የጠቅላላ ጉባኤ አባልነቱ ወዲያውኑ ይቋረጣል። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ የተከሰተ ክፍተት በተገቡው መንገድ ይሟላል። (331)
334.1. የጠቅላላ ቦርድና ኮሚቴዎች አባላት በሚጓደሉበት ጊዜ የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦረድ ከሚያቀርቧቸው እጩዎች የሚመረጡት አገልጋዮች ክፍተቱን ይሞላሉ። ክፍተት በሚፈጠርበት ጊዜ የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦረድ በተቻለ ፍጥናት የሁለት ሰዎች ስም ለጠቅላላ ፀሐፊ ያቀርባል። ከነዚህ ሰዎች መካከል አንዱ የውክልና ክፍተቱ የተፈጠረበት ክልል ቀጠናዎች የመማክርት ቦርዶች በፖታ ቤት በኩል በደምፅ ብልጫ የሚመርጡት ይሆናል። ለዚህ ምርጫ እያንዳንዱ የቀጠና የመማክርት ቦረድ አንድ ድምፅ ብቻ ይሰጣል። ለትምህርት ውክልና፣ ጠቅላላ ቦርድ በፖስታ ቤት በኩል በአብላጫ ድምፅ አንዱን ይመርጡ ዘንድ የእጩዎች የስም ዝርዝር ይላክላታል። ለናሚዓ ውክልና፣ ጠቅላላ የናሚዓ ካውንስል ጉዳዩ ከሚመለከተው ጠቅላላ ኃላፊ ጋር በመመካከር የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ በሚያፀድቀው መሠረት እጩዎች በፖስታ ቤት በኩል አንዱን በአብላጫ ድምፅ ይመርጣል። (331)

**በ. የጠቅላላ ቦርድ ተግባራት**

335. ጠቅላላ ቦርድ የናዛሬንን ቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ፣ ማለትም በዌስልያን ትውፊት ክርስቲያናዊ ቅድስና የማስፋፋት ዓላም ለማሳካት ሁሉንም ብሄራዊ፣ ክልላዊ፣ የቀጠናና አጥቢያዊ ቦርዶች ማበረታታትና መቆጠጠር፣ እንዲሁም በእያንዳንዱ አገር እና/ወይም ክልል ዓለምአቀፋዊት ቤተ ክርስቲያን ለማስፋፋት መጣር አለበት። ጠቅላላ ቦረድ ጠቅላላ ጉባኤ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የናዛሪን ቤተ ክርስቲያ ኮሚቴዎች መዋለንዋያዊና ቁሳቁሳዊ ጉዳዮች ማሳደግ አለበት። በናዛሪን ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴዎች ውስጥ አንድ ዓይነት ፖሊሲ ይመሠረት አንድ የአያኬ ተመራጭ ኮሚቴዎች ዕቅዶችና ተግባራት ማስተባበር፣ ማዛመድና ማጣመር ይኖርበታል። ከናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ጋር የሚተባበሩትን ወይም ግንኙነት ያላቸውን ተቋማትና የአገልግሎት ክፍሎችና የሂሳብ መዝገቦች ሁሉ ኦዲት የማድረግ ሥልጣን አለው። ይህም እጅግ ውጤታማ የሚሆንየአሠራር ዘዴ አንድ ዓይነትና የቅርጽ ምልዕነት በሚያረጋግጥ መልኩ የሚካሄድ ይሆናል። ጠቅላላ ቦረድ ለአያሌ አገልግሎት ክፍሎችና ከናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ጋር ግንኙነት ላላቸው ወይም ህብረት ለሚያደርጉ ድርጅቶችና ተቋማት አስተዳዳዊና የሥራ እንቅስቃሴዎች አማካሪ አካል በመሆን ያገለግላል።

እነዚህ የአገልግሎት ክፍሎች፣ ድርጅቶችና ተቋማት ለጠቅላላ ቦርድ ምክሮችና አስተያየቶች ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

335.1. ጠቅላላ ቦርድ በግዥ፣ በተወጠና ዕቅድ፣ በውርስ፣ በልገሳ፣ ወይም በማንኛውም ህጋዊ መንገድ ያገኛውን ቋሚና ንቀሳቃሽ ንብረት የመሸጥ፣ በንብረትነት የመያዝ፣ የማስተዳደር፣ በብድር የማስያዝ፣ የመሸጥ፣ አሳልፎ የመስት፣ የመለገስ ወይም በውርስ የመውሰድና በዕዳ የመያዝና የመሸጥ፣ ለህጋዊ ዓላማዎች ማሳኪያ ገንዘብ የማበደር ሥልጣን አለው፡፡

335.2. ጠቅላላ ቦርድ የጠቅላላ ጉባኤ ከመጠናቀቁ በፊት ወይም ወዲያውኑ እንደተጠናቀቀ ተሰባስቦ በመደራጀት ጽሑፎቹን በህግጋቱ እንደተደነገገው፣ በሥራ ኃላፊዎችን፣ ኮቴዎችንና የኮሚቴ አባላት ይመርጣል፡፡ ከነዚህ አገልጋዮች ተተኪዎቻቸው ተመርጠው ብቁ እስኪሆኑ ድረስ ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት ይሠራሉ፡፡ ጠቅላላ ኃላፊዎች የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎቸ በጋራ ይመራሉ፡፡

335.4. **ስብሰባዎች**፡፡ ጠቅላላ ቦርደ በአራት ዓመታት ውስጥ የተጠቀሰው ቦርደ ህግጋት በሚወስነው ጊዜ ቢያንስ ሦስት ጊዜ በካንሳስ ከተማ ይሰበሰባል፡፡ ነገር ግን የመደበኛ ስብሰባ ሰዓት፣ ቀንና ቦታ የጠቅላላ ቦርዱንና የኮሚቴዎቹን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ በየትኛውም መደበኛ ወይም ልዩ ስብሰባ ላይ በሚሰጡ የሙሉ ድምፅ ውሳኔ ሊቀየር ይችላል፡፡

335.5. ልዩ ስብሰባዎች፡ ልዩ የጠቅላላ ቦረድ ስበሰባዎችን ሊቀመንበሩ፣ ፕሬዜዳንቱ ወይም ፀሐፊው ሊጠራ ይችላል፡፡

335.6. **ዓለምአቀፍ አስተዳደርና የመዋለንዋይ ኮሚቴ**፡፡ በጠቅላላ ቦርድ የተመረጠው የዓለምአቀፍ አስተዳደርና የመዋለንዋይ ኮሚቴ በባለአደራነት የያዘውን ገንዘብ በአግባቡ ኢንቨስት የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ ጠቅላላ ቦርድ አያሌ የአገልግሎት ክፍሎችና የጠቅላላ ዋና ጽ/ቤት ቢሮዎች ለመጭው ዓመት ያቀረቡትን የበጀት ጥያቄ መጀመሪያ ለዚህ ኮሚቴ ከመራ በኂላ፣ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሰጣቸውን ድጋፎች የሚያመለክት ሪፖርት ከዚሁ ኮሚቴ ይቀበላል፡፡ ይህ ኮሚቴ ጠቅላላ ቦርድ የሚሰጠውን ሌላ ማንኛውንም ተግባር ያከናውናል፡፡ የሚያካሂዷቸውን የማንኛውንም ስብሰባዎች ትክክለኛ ቃለ ጉባኤዎቸን ጠቅላላ ቦርድ እንዲያፀድቅለት ያቀርባል፡፡

335.7. የዓለም የወንጌል ስርጭት መዋለንዋይ የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ለአገልግሎት ክፍሎች እንቅስቃሴዎች ድጋፍ፣ ጥገናና መስፋፋት የምታሰባስበው በጀት አጠቃላይ ድምር ነው፡፡ የተለያዩ የአገልግሎት ክፍሎችና የቤተ ክርስቲያን ድርጅቶች፣ እንዲሁም የጠቅላላ ገንዘብ ያዥ የሚያቀርበው የበጀጽ ጥያቄ ከተመለከተው በኂላ፣ ጠቅላላ ቦርድ ከዓለም የወንጌል ስርጭት መዋለንዋይ ለያንዳንዱ የአገልግሎት ክፍልና መዋለንዋይ ምን ያህል ገንዘብ መመደብ እንዳለበት ይወስናል፡፧ የዓለም የወንጌል ስርጭት መዋለንዋይ በበጀት ምደባው ከተስማማ በኂላ ጠቅላላ ቦርድ ውሳኔውን ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ እንዲገመግሙት፣ አስተያየት እንዲሰጥበት፣ ወይም እንዲያሻሽለው ይደረጋል፡፡

335.8. ጠቅላላ ቦርድ የቀጣዩን የበጀት ዓመት የዓም የወንጌል ስስርጭት መዋለንዋይ ጠቅላላ ድምር ከወሰነ በኂላ፣ ጠቅላላ ቦርድማ የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ የዓለም የወንጌል ስርጭት መዋለንዋይ ድርሻ ለአያሌ የቀጠናዎች ጉባኤ

የማከፋፈል ሥልጣን ይኖራቸዋል። ይህም ክፍፍል አጠቃላይ ፍላጎቶች ላይ የተመሠረተ ይሆናል። (130፣ 317.12)

335.9. ጠቅላላ ቦርድ የትኛውም የአገልግሎት ክፍል ወይም መዋለንዋይ የጠየቀውን የገንዘብ መጠን የመጨመር ወይም የመቀነስ ሥልጣን አለው። ጠቅላላ ጉባኤ የወሰናቸው የገንዘብ ጉዳዮች ለጠቅላላ ቦርድ ይመራሉ። ጠቅላላ ቦርድ የትኛውንም ቤተ ክርስቲያን ወይም ተቋም ዓመታዊ የበጀት ድርሻ ከወቅቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ የማስተካከል ሥልጣን ይኖረዋል። ይህም ከጠቅላላ ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ የመዋለንዋይ አሠራት ጋር በሚጣጣም ምልኩ የሚከናወን ይሆናል።

335.10. ጠቅላላ ቦርድ ከዓለም የወንጌል ስርጭት መዋለንዋይ ለናዛሪን የሥነ መለኮት ሰሚናር (ዩ.ኤስ.ኤ) እና ለናዛሪን የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ (ዩ.ኤስ.ኤ) የሚቀርበውን የበጀጽ ድርሻ ጥያቄ ካለው ገንዘብ አንጻር አመዛዝኖ ያጸድቃል።

335.11. ጠቅላላ ቦርድ እስከሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤ ድረስ ባ፤ው ጊዜ ውስጥ የጠቅላላ ኃላፊዎችን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞችን እየከለሰ በየዓቱ አስፈላጊውን ማሻሻያ ያደርጋል።

335.12. ***ሪፖርቶች*።** ጠቅላላ ቦርድ በመደበኛ ስብሰባው የአገልግሎት ዘርፎች ባለፈው ዓመት ያካሄዳቸው ተግባራት በዝርዝር የሚጣስረዳ ሪፖርት ይቀርባል። ይህም የመዋለንዋይ ለጭው ዓመት ምን ያህል በጀት እንደሚፈልግም በሪፖርቱ ውስጥ ማቀፍ አለበት።

335.13. ጠቅላላ ገንዘብ ያዥ ያለፈውን ዓመት የገቢና የወጭ ደረሰኞች ዝርዝር ሪፖርት ለጠቅላላ ቦርድ ማቅረብ አለበት። ይህ፣ የባለአደራነት መዋለንዋይንና ኢንቨስትመንቶችን፣ እንዲሁም ለመጭው ዓመት የሚያስልገውን የገንዘብ መጠን (በጠቅላላ ቦርድ የአገልግሎት ዘርፍ በጀት ውስጥ ያልተካተተ) ማጠቃለል ይኖርባትል። ጠቅላላ ገንዘብ ያዥ ይፋዊ ተግባራት በአግባቡ በመወጣቱ ረገድ ለጠቅላላ ቦርድ ተጠያ ይሆናል። (330.5)

335.14. ጠቅላላ ቦርድ ጠቅላላ ጉባኤ ከመጠናቀቁ በፊት ወይም ወዲያውኑ እንደተጠናቀቀ ተሰብስቦ ጠቅላላ ፀሐፊ፣ ጠቅላላ ገንዘብ ያዥ፣ የቅድስና ዛሬ አዘጋጅ (አዘጋጆች) መምረጥ አለበት። ምርጫው በጠቅላላ ቦርድ ህግጋት መሠረት የሚከናወን ሲሆን፣ ተመራጮቹ እስከሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤና ተተኪዎቻቸው ተመርጠው ብቁ እስኪሆኑ ድረስ ያገለግላሉ።

335.15. ጠቅላላ ቦርድ የቅድስና ዛሬ የተመሳሳይ እትሞች አዘጋጅ (አዘጋጆች) ራሱ በወሰነው የእጩ አቅራቢነት ሂደት ይመረጣል። እንዲህ ዓይነት የእጩ አቀራቢነት በጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ መጽደቅ አለበት።

335.16. ጠቅላላ ቦርድ ከያንዳንዱ የጠቅላላ ጉባኤ በኋላ የናዛሪን አሳታሚ ድርጅት ቦርድ ይመርጣል። ይህ ቦርድ እስከሚቀጥለው የተቅላላ ጉባኤ ማብቂያና ተተኪዎች ተመርጠው ብቁ እስኪሆኑ ድረስ ይሠራል። (338)

335.17. ጠቅላላ ቦርድ በአንቀጽ 335.20 እና በጠቅላላ ቦርድ ሕግጋት በተደነገገው መሠረት የናዛሪን አሳታሚዎች ድርጅት ፕሬዚዳንት ይመርጣል።

335.18. አንድ ክልል/አገር የሚመለከት የጠቅላላ ቦርድ አጀንዳ የጠቅላላ ቦርድ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና የጠቅላላ ኃላፊዎች ቦርድ በሚያፀድቁት መሠረት፣ ለተጠቀሰው ክልል.አገር የጠቅላላ ቦርድ አባላት ጉባኤ የመራል።

335.19. ጠቅላላ ቦርድ ጠቅላላ ጉባኤ ወይም ጠቅላላ ቦርድ ለሆነ አገልግሎት ዘርፍ ወይም ዘርፎች ወይም ለጠቅላላው ቦርድ ሥልጣን ከሰጠው ኮሚቴ ወይም ከፐሚሽን ጋር ተገቢውም ግንኙነት በማድረግ ሥራውን ኃላፊነቱንና በጀትን ይወስናል፡፡

335.20. **የአገልግሎት ዘርፍ ዳይሬክተሮች**፡፡ ጠቅላላ ቦርድ ለእያንዳንዱ የአገልግሎት ዘርፍ የአገልግሎት ዳይሬክተሮች በድምፅ መስጫ ወረቀት ይመርጣል፡፡ ተመራጭ በአንቀጽ 317.5 እንደተጠቀሰው ከአገልግሎታቸው ካልተነሡ በቀር እስከቀጥለው የጠቅላላ ጉባኤ ማብቂያና ተተኪዎቻቸው ተመርጠው ብቁ እንሲሆኑ ድረስ ይሠራሉ፡፡ እነዚህ አገልጋዮች በሚከተሉት ሂደት ለእጩነት ይቀርባሉ፡፡ በጣም ጠቃሚ የሆነ ዳይሬክተር ካለ እጩ አቅራቢው ኮሚቴ የ‹‹አዎ›› ወይም ‹‹አይደለም›› ድምፅ ሊሰጥ ወይም ብዙ እጩዎች ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ለነዚህ አገልግሎቶች ብቁ ዳይሬክተሮች ላማግኘት በጠቅላላ ቦርድ ህግጋት ውስጥ እንደተመለከተው አሳሽ ኮሚቴ ተሰይሞ ክለሳ ማካሄድ አለበት፡፡ ይህ ኮሚቴ ሁለት ወይም ሦስት ስሞችን ለእጩ አቅራቢ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡ የተመለመሉባቸውንም ምክንያቶች ያብራራል፡፡

ስድስት ጠቅላላ ኃላፊዎችና የሠራቶች አስተዳደር ኮሚቴ የሚገኙት እጩ አቅራቢ ኮሚቴ አንድ ወይም ሁለት ስሞችን ለጠቅላላ ቦርድ ያቀርባል፡፡ ቦርዱም ምርጫውን አበብላጫ ድምፅ ያከናውናል፡፡

335.21. **የሥራ አስፈጻሚዎች ደመወዝ**፡፡ ጠቅላላ ቦርድ ‹‹የአፈጻጸም ግምገማ›› እና የደመወዝ አስተዳደር ፕሮግራም መመሥራትና በሰነድነት መያዝ ይኖርበታል፡፡ ይህም አገልግሎት ዘርፍ ዳይሬክተርንና የአገልግሎር ዳይሬክተሮችን የሚያካትት እንዲሁም የኃላፊነት ደረጃዎችንና ብቃትን የሚገናዘብ የደመወዝ መዋቅርን የሚያጠቃልል መሆን ይኖርበታል፡፡ ጠቅላላ ቦርድ የአገልግሎት ዘርፍ ዳይሬክተሮችን፣ የናዛሪን አሳታሚ ድርጅት ፕሬዚንትንና በጠቅላላ ቦርድ የሚመረጡትንና ሥልጣን የሚሰጣቸውን ሌሎች የሥራ ኃላፊዎችን ደመወዝ በየዓመቱ ይከልሳል፡፡ ያጸድቃል፡፡

335.22. ጠቅላላ ቦርድ ጠቅላላ ጉባኤ እና/ወይም ጠቅላላ ቦድ የሚሰባበሰብበት ጊዜ ከመድረሱ በፊት በአንቀጽ 335.14 ላይ ጠቅላላ ቦርድ ወይም እነሱ የመረጡዋቸው ኮሚቴዎች የሥራ አስፈጻሚ ቢሮዎች ውስጥ ክፍተት ቢፈጠረ በጠቅላላ ቦርድ ሕግጋትና በአንቀጽ 317.4 በተገለጸው መሠረት ተተኪዎችን ይመርጣል፡፡

336. ሁሉም የሥራ ኃላፊዎች በአንቀጽ 335.14 እና 335.20 የተዘረዘረ ማንኛውም ሌላ ዳሬክተር የጠቅላላ ጉባኤ ወይም የተመራጭ ኮሚሽኖች፣ የጠቅላላ ቦርድና የአገልግሎት ዘርፎች ሠራተኞች የሆነ የትኛውም ድርጅት ኃላፊ ከ70ኛው የልደት ዓመት ቀጥሎ በሚመጣው የጠቅላላ ቦርድ ስብሰባ ላይ ጡረታ ይወያል፡፡ ክፍተት በሚኖርበት ጊዜ መምሪያው በሚያዘው መሠረት ይሠራል፡፡

የአጠቃላይ ቦርድ አባላት

| **የአህጉር መጠን** | **ተራ አባላት** | **መሪዎች** |
|---|---|---|
| እስከ 100,000 | 1 | 1 |
| 100,001 – 200,000 | 2 | 2 |
| 200,000 በላይ | 3 | 3 |

ዓለም አቀፍ ተወካዮች

| | | |
|---|---|---|
| የናወዓ አጠቃላይ | 1 አባል | |
| የናሚዓ አጠቃላይ | | 1 አባል |
| የናዛሪን ኮሌክ | 1 | 1 |

**የአጠቃላይ ቦርድ ተግባራት**

የአጠቃላይ ቦርድ የዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴን ይቆጣጠራል፡፡ እያንዳንዱ የአገልግሎት ክፍል እርሱ እርሱ ቁርኝነት እንድኖረው ይሠራል፡፡

አጠቃላይ ቦርድ በዓለም አቀፍ የወንጌል ስርጭት በኩል የተዋጣው ገንዘብ በምን መንገድ ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡ ለተለያዩ የአገልግሎት ክፍሎች እና በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ላሉ ተቋማት ያከፋፍላል፡፡ አጠቃላይ ቦርድ ከሁሉም የአገልግሎት ክፍሎች የአፈጻጸም ሪፖርቶችን ያደምጣል፡፡

**በናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ የአገልግሎት ክፍሎች**

በናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሦስት የአገልግሎት ደረጃዎች አሉ፡ እርሱም፡

1. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ፈቃድ የተሰጠው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ፡፡
2. በቀጠና ጉባኤ የቀጠና የአገልግሎት ፈቃድ የተሰጠው አገልጋይ፡፡
3. በቀጠና ጉባኤ ፈቃጅነት እና በአጠቃላይ ኃላፊ እና በሌሎች ሽማግላች ቀብነት የተቀባይ ሽማግሌ ወይም ዲያቆን፡፡

**የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ** (428)

1. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን አለበት፡፡ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቦርድ የሚቀባና በመጋቢው በታች ሆኖ የሚሠራ ነው፡፡ ይህ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዩ ያለውን የአገልግሎት ጸጋ እንድጠቀምበት እና እንዲያሳድግ ያድርገዋል፡፡ አገልጋዩ ወደሕይወት ዘመን ሁሉ የመማር ዓለም ውስጥ ገባ ማለት ነው፡፡
2. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ መጋቢ ከሽናግሌዎቹ ውጭ ከሆነ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቦርድ በቤተ ክርስቲያኒቱ ፀሐፊ እና መጋቢ

የተፈረመበትን ፈቃድ ልሰጥ ይችላል።

3. መጋቢው የተቀባ ካልሆነ የመጋው እና የቤተ ክርስቲያንቷ ቦርድ በእጩነት ያቀረቡት ሰው በቀጠና መማክር ቦርድ እና በቀጠና ኃላፊው አማካኝነት መጽደቅ ይኖርበታል።
5. የእጩ ደንነት፣ የመጸሐፍ ቅዱስ እና የቤተ ክርስቲያን መመሪያ ያለው እውቀት በሚገባ መጤን አለበት። እጩው መንፈሳዊ ስጦታ እና ብስለት እንዳለው በተግባር ማሳየት ይጠበቅበታል።
6. የአገልግሎት ፈቃዱ የሚያገለግለው ለአንድ አመት ብቻ ይሆናል።
7. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዩ ለአገልግሎት የሚያበቃውን ትምህርት መውሰድ ይጠበቅበታል። ከሁለት ዓመታት በኋላ አገልጋዩ ትምህርቱን ያለጠናቀቀ ከሆነ የአገልግሎት ፈቃዱ አይታደስለትም።
8. የአገልግሎት ፈቃዱ በመጋቢው አጽዳቅነት በቤተ ክርስቲያን ቦርድ አማካኝነት ልታደስለት ይችላል። የቤተ ክርስቲያኗ መጋቢ የተቀባ ሽማግሌ ካልሆነ መጋቢውና የቤተ ክርስቲያኗ ቦርድ የአገልጋዩ ፈቃድ እንድታደስ ይጠይቃሉ እንዲሁም የቀጠና ኃላፊው ፈቃዱ እንድታደስ ልፈቅድ ይችላል።
9. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የጌታ እራት የማቅረብ እና ሰዎችን የማጥመቅ ስልጣን የለውም እንዲሁም ማጋባትም አይችልም።

**የቀጠና አገልግሎት ፈቃድ** (429)

1. አመልካቹ የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን አለበት እንዲሁም በሕይወቱ ሁሉ እግዚአብሔርን ለማገልገል የተጠራ መሆኑን ጠንቅቆ ማወቅ አለበት።
2. አመልካቹ ቢያን ለአንድ ዓመት ያህል የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ፈቃድ ልኖረው ይገባል።
3. አመልካቹ አባል ከሆነበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቦርድ ፈቃድ ልያገኝ ይገባዋል። አመልካቹ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ከሆነ ፈቃድ ልሰጠው የሚገባው የቀጠና መማክርት ቦርድ ነው።
4. አመልካቹ የአንድ ዓመት ሙሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰልጠና መውሰድ አለበት ወይም ስምንት የአገልግሎት ፈቃድ ትምህርቶችን መውሰድ ይጠበቅበታል።
5. አመልካቹ በጥንቃቄ የአገልግሎት ፈቃድ ቅጹን መሙላትና ለአገልግሎት ፈቃድ ሰጭ ቦርድ ማቅረብ ይጠበቅበታል።
6. አመልካቹ በቀጠና ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የሚሰጠውን የአአገልግሎት ትምህርት መከታተል ይኖርበታል።
7. አመልካቹ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ከሆነ ለቀጠናው ኃላፊ ወህራዊ ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

8. የአመልካቹ መንፈሳዊ ሕይወት፣ የትምህርት ሁኔታ እና ለአገልግሎት ብቁ መሆን ወይም አለመሆንንን የአገልግሎት ፈቃድ ሰጭ ቦርድ ቃለ መጠይቅ ያደርግለታል፡፡
9. እጩው ከቀጠና ጉባኤ በቂ የሆነ የድጋፍ ድምጽ ሊያገኝ ይገባዋል፡፡
10. የአገልግሎት ፈቃዱ በእያንዳንዱ ዓመት መጨረሻ ላይ የሚያበቃ ይሆናል፡፡
11. እንደ መጋቢ ሆነው የሚያገለግሉ እና ትምህርቱን በሚገባ ተከታትለው ያለፉ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ መስበክና የቤተ ክርስቲያን ስርዓቶችን መፈጸም ይችላሉ፡፡
12. ከሌላ ቤተ እምነት የመጣ አገልጋይ ከመጣበት ቤተ ክርስቲያን ያገኘውን የአገልግሎት ፈቃድ ማሳየት አለበት እንዲሁም በናዝሪን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልጋዮችን ለአገልግሎት ብቁ ለማድረግ የሚሰጠውን ትምህርት ጋር ተመጣጣኝ ትምህርት መውሰዱን ማረጋገጥ አለበት እንዲሁም ለቀጠና የአገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት አስፈላጊ የሆኑ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ሁሉ ማሟላት አለበት፡፡

አንድ ጊዜ የአገልግሎት ፈቃድ ከተሰጠ በኂላ መጋቢው የአገልግሎት ፈቃዱ እንዲታደስለት እነዚህ ነገሮች ማሟላት አለበት፡

1. መጋቢው በያዓመቱ የአገልግሎት ፈቃድ ማደሻ ቅጹን መሙላ አለበት፡፡
2. የመጋቢው ጉዳይ በቀጠና መማክርት ቦርድ ቀርቦ መጽደቅ አለበት፡፡
3. መጋቢው ለአገልጋዮች ከሚሰጡ ትምህርቶች መካከል ቢያንስ ሁለቱን መፈጸም አለበት፡፡
4. የአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መጋ ከሆነ መጋው በየወሩ የአገልግሎቱን ሪፖርት ለቀጠና ኃላፊው ማቅረብ አለበት፡፡
5. መጋቢው የአገልግሎት ጸጋ፣ ስጦታ እና ጠቃሚ ሥራዎችን እየሸራ መሆኑን በተግባር ማሳየት አለበት፡፡
6. መጋቢው ለአግልገሎት ፈቃድ ሰጭ ቦርድ እና በቀጠና ጉባኤ ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኝ ይባዋል፡፡
7. መጋቢው በናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተቀባ ሽማግሌ ወይም ዲያቆን ለመሆን ግብ ማድረግ ይኖርባል፡፡ አንድ የአገልግሎት ፈቃድ ያገኘሰው ከአስር ዓመታት በኂላ ልዩ ሁኔታ ካልኖረ በስተቀር ፈቃዱ ሊታደስለት አይገባም፡፡

**ዲያቆን** (430)
ዲያቆን ለክርስቲያናዊ አገልግሎት በሙሉ ጊዜ የተጠራ ሰው ነው ነገር ግን አገልግሎቱ ለመስበክ አይደለም፡፡ አንዳንድ ዲያቆናት የተጠሩት ለሕጻናት አገልግሎት፣ አንዳንዶች በሆስፒታል ውስጥ መንፈሳዊ ሥራ ለመስራት፣

አንዳንዶች ደግሞ ትልቅ ቁጥር ባለው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎች በየቤታቸው ሄደው ለመነብኘት ወይም በቤተ ክርስቲያነው ውስጥ በሚሰጡ የሙሉ ጊዜ የርኅራሄ አገልግሎት ውስጥ ለመሳተፍ ተጠርተዋል።
ለዲያቆናት የቤተ ክርስቲያን ስርዓቶችን ለማስፈጸም ሙሉ ስልጣን የተሰጣቸው ሲሆን አልፎ አልፎም የአምልኮ ስርዓትን መምራትና መስበክ ይችላሉ።
ዲያቆን ሆኖ ለመቀባት አስፈላጊ የሆኑ ቅደም ተከተሎች የተቀባ ሽማግሌ ለመሆን የሚያስፈልገውን ዓይነት ሲሆን ልዩነት የሚወስዱት የትምህርት ኣይነት ብቻ ነው።

**የተቀባ ሽማግሌ** (431)

የተቀባ ሽማግሌ የመሆን ዕድል የእግዚብሔር ቃል ለመስበክ ግልጽ ጥሪ ላላቸው ሰዎች ብቻ ነው። እጩው ለአገልግሎት ማዘጋጃ ተብሎ የተዘጋጀውን ትምህርት ማጠናቀቅ አለበት። እጩው መንፈሳዊ ብስለት፣ ስጦታ እና በአገልግሎቱ ፍሬያማ እንሆነ በተገግባር ማሳየት አለበት። የተቀባው ሽማግሌ ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ሙሉ ጥሪት እያደረገ መሆኑን ማሳየት ይጠበቅበታል። ይህ ቋሚ ነገር ሲሆን ቅባቱም በየዓመቱ የሚታደስ አይደለም።
የአገልግሎት ፈቃድ ያለው አንድ አገልጋይ ሽማግሌ ሆኖ ለመቀባት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነገሮች ማሟላት አለበት።

1. ለመቀባት እየተዘጋጁ ላሉት ሰዎች የሚሰጠውን ትምህርት ሙሉ ለሙሉ ማጠናቀቅ አለበት።
2. ለሁለት ተከታታይ ዓመታት የሙሉ ጊዜ ፈቃድ ያለው አገልጋይ ሆኖ ማገልገል ይኖርበታል ወይም በተባባር መጋቢነት ለሦስት ዓመታት መገልገል አለበት።
3. እጩው በቤተ ክርስቲያን ቦርድ ወይም በቀጠና መማክርት ቦርድ የአገልግሎት ፈቃዱ እንድታደስለት የተፈቀደለት መሆን አለበት።
4. እጩዎቹ በአገልግሎት ፈቃድ ሰጭ ቦርድ በጥንቃቄ መመረጥና ብቃታቸው መረጋገጥ አለበት።
5. እጩው አግብቶ የፈታ ከሆነ የአጠቃላይ ኃላፊዎች ቦርድ የዚህን ሰው መቀባት ልወስኑበት ይገባል።
6. እጩውን ለመቀባት በቀጠና ጉባኤ 2/3 ድምጽ ማግኘት ይኖርበታል።
7. የመቀባት ሥርዓቱ በቀጠና ጉባኤ ወቅት በአጠቃላይ ኃላፊው በኩል የሚደረግ ልዩ የሆነ ሥርዓት ነው። አጠቃላይ ኃላፊው ከሌሎች ከተቀቡ አገልጋዮች ጋር በመሆን በአገልጋዩ ላይ እጃቸውን በማኖር የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን የተቀባ አገልጋይ አድርገው ይሾሙታል።

**የአገልግሎት ፈቃድ እውቅና** (432)

ወደ ናዛሪን ቤተ ክርስቲያን መምጣት የፈለገ የሌላ ቤተ እምነት የተቀባ ወንጌላዊ ከዚህ በታች ያሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት።

1. የቤተ ክርስቲያኒቱን መምሪያ እና ታሪክ የተመለከተ ፈተና ማለፍ
2. ለእጩዎች የሚቀርበውን ጥያቄ ሞልቶ ማጠናቀቅ
3. ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ሁሉ ማሟላት አለበት።

የአጠቃላይ ኃላፊው የአገልግሎት ፈቃድ እውቅናውን ይሰጣል፡፡

**ከአገልግሎት በራስ ፍቃድ መልቀቅ ወይም መነሳት**

የሽምግልና ቢሮ ቋም ስለሆነ በየዓመቱ መታደስ የለበትም ነገር ግን የተቀባው ሽማግሌ በየዓመቱ ለቀጠና ጉባኤ ሪፖርት ማድርግ አለበት፡፡ የቅባት ምስክር ወረቀቱ በቤተ እምነቱ እና በአገልጋዩ መካከል ያለ ውል ሆኖ ያገለግላል፡፡ ይህ ጥቅም ልኖረው የሚችለው የአገልጋዩ ሕይወትና አስተምህሮ ከቤተ ክርስቲያኒቱ አስተምህሮ እና ልምምድ ጋር እስከተስማም ጊዜ ብቻ ነው፡፡

የተቀባው አገልጋይ ከቀጠና መማክርት ቦርድ የጽሑፍ ፈቃድ ሳያገኝ በግሉ ምንም ዓይነት ተግባራትን ማከናወን አይችልም፡፡ የተቀባው አገልጋይ ከሌላ ቤተ እምነት ጋር ህብረት ከፈጠረ የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌለነቱ ያከትማል፡፡ (433.10)

አገልጋዩ የአገልጋይ ፈቃዱን ለቀጠና በመመለሰ ቀጠናው ለአጠቃላይ ጸሐፋ ልልክ ይችላል፡፡ (435.10)

ምንም ዓይነት አገልግሎት ላይ ሳይመደብ ለአራት አመታት የቆየ አንድ አገልጋይ በቀጠና ጉባኤ በራሱ ፈቃድ አገልግሎቱን ካቋረጡት ሰዎች መካከል ልመደብ ይችላል፡፡ (436.2)

ትክክለኛ ተግባር ያላከናወነ የቀተባ አገልጋይንት ለመቅጣት መኬድ ያለባቸውን መንገዶች የሚያመለክተው በመመሪያው 505-507.2 ላይ ተጠቅሷል፡፡

**ለመጋቢው እና ለመሪዎች ማበረታቻ የእግዚብሔር ቃል**

**[28]መንፈስ ቅዱስ እናንተን ኤጲስ ቆጶሳት አድርጎ ሾሞአችኋል፤ እንግዲህ ለራሳችሁና ለመንጋው ተጠንቀቁ፤ እግዚአብሔር በገዛ ልጁ ደም የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን ጠብቁ። ሐዋ 20፥28**

***[3]እንዲሁም በእናንተ ኀላፊነት ሥር ያሉትን ጨቍኖ በመግዛት ሳይሆን ለመንጋው መልካም ምሳሌነትን በማሳየት ይሁን። [4]ይህን ብታደርጉ ዋናው እረኛ በሚገለጥበት ጊዜ የማይበላሸውን የክብር አክሊል ትቀበላላችሁ።***

1 ጴጥ 5፡3-4

ANP

Africa Nazarene Publications